አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የኮንሶ ሃገረሰባዊ አልባሳት እና ጌጣጌጦች፦ ገላጭ-ተንታኝ ጥናት

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

በ

አፀደ ያረጋል

ለኤም. ኤ ዲግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት

አዲስ አበባ

ሰኔ 2003 ዓ.ም

# የኮንሶ ሃገረሰባዊ አልባሳት እና ጌጣጌጦች፦

## ገላጭ-ተንታኝ ጥናት


በ

አፀደ ያረጋል ፈንቴ


ለኤም. ኤ ዲግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት


ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY



አማካሪ

አብርሃም አለሙ

በሰብአዊ ሳይንሶች ፋኩልቲ

የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት


አዲስ አበባ

ሰኔ 2003 ዓ.ም

# የኮንሶ ሃገረሰባዊ አልባሳት እና ጌጣጌጦች፡- ገላጭ-ተንታኝ ጥናት

በአፀደ ያረጋል ፈንቴ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሰብአዊ ሣይንሶች ፋኩልቲ
ለኢትዮጵያ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ድኅረ ምረቃ ፕሮግራም
ለኤም.ኤ ዲግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

| ስም | ፊርማ | ቀን |
| --- | --- | --- |
| [illegible] | [illegible] | 18/07/[illegible] |
| አማካሪ | | |
| [illegible] | [illegible] | 10/11/2003 |
| ፈታኝ | | |

# ምስጋና

በጥናቴ ሂደት በማማከር ላገዙኝ ለአማካሪዬ ለአቶ አብርሃም አለሙ ከፍ ያለ ምስጋናን አቀርባለሁ፤ መንገዱን አሳይተውኛልና:: ለመስክ ስራ ወደ ኮንሶ በሄድኩበት ወቅት የመስክ ቆይታዬን ላቀለለልኝ፣ መረጃ በመስጠት እና ልዩ ልዩ ድጋፎችን በማድረግ ትብብር ላደረገልኝ የኮንሶ ልዩ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ እና የመስሪያቤቱ ባልደረቦች ምስጋናዬ ይድረስ:: ለጥናቴ የጀርባ አጥንት የሆነውን መረጃ ሳይሰስቱ በመስጠት ለተባበሩኝ መረጃ አቀባዮቼ በሙሉ ከልብ አመሰግናለሁ:: በተለይ ደግሞ የባህል እና ቱሪዝም ቢሮ ባልደረባ የሆኑት አቶ ከበደ ካላቸው ጊዜ ላይ ቀንሰው እንደረዳቴ በመሆን ያደረጉልኝ ትብብር ከሁሉም የላቀ ነውና አመሰግናለሁ::

ቤተሰቦቼ በተለይ እማማ እና አባባ ያደረጋችሁልኝ የሞራል እና የቁሳቁስ ድጋፍ ብርታት ሆኖኛልና እድሜና ጤና ይስጥልኝ እላለሁ:: በጥናቴ ወቅት በማንኛውም መልኩ ለደገፋችሁኝና ላበረታታችሁኝ ጓደኞቼ በተለይ ታሪክ፣ ማህሌት፣ ታደሰ፣ መቅደስ፣ ዮሃንስ፣ ሻምበል እና ሄለን እጅግ በጣም አመሰግናለሁ፤ ውለታችሁ ትልቅ ነውና::

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ማውጫ


ምስጋና ........................................ I

ማውጫ ........................................ II

አጠቃሎ ........................................ V

1. መግቢያ ........................................ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ........................................ 1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........................................ 2

1.3 የጥናቱ ዓላማ ........................................ 3

1.4 የምርምር ጥያቄዎች ........................................ 3

1.5 የመረጃ ምንጭና መሰብሰቢያ ዘዴ ........................................ 3

*1.5.1. ቃለ መጠይቅ ........................................ 4*

*1.5.2. ምልከታ ........................................ 4*

1.6 የጥናቱ ጠቀሜታ ........................................ 5

1.7 የጥናቱ ወሰን ........................................ 5

1.8 ያጋጠሙ ችግሮች ........................................ 6

1.9 የመስክ ቆይታ ........................................ 6

1.10 የጥናቱ አደረጃጀት ........................................ 8

2. ክለሳ ድርሳናት ........................................ 10

2.1 ቁሳዊ ባህል፦ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት ........................................ 10

*2.1.1 ሃገረሰባዊ አልባሳት ........................................ 11*

*2.1.2 አልባሳትና ማንነት ........................................ 12*

*2.1.3 የአልባሳት ተግባር ........................................ 13*

*2.1.4 የቁሳዊ ባህል ጥናት ........................................ 14*

2.2 የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት ........................................ 17

3. ኮንሶ፦ማህበረ_ባህላዊ ዳራ ........................................ 24

3.1 መልክዓ_ምድራዊ አቀማመጥ ........................................ 24

3.2 ባህላዊ አስተዳደር ........................................ 26

3.3 ባህላዊ የጋብቻ ሥነስርዓት ........................................ 28


ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ILS LIBRARY


3.4 ባህላዊ የለቅሶ ሥነስርዓት ....................................................30

3.5 የእጅ ባለሞያዎች ህይወት ....................................................31

**4. የኮንሶ ሄገረሰባዊ አልባሳት:የቁሳዊ እና ጥበባዊ ገፅታዎች ትንተና ....................34**

4.1 አልባሳት ....................................................34

*4.1.1 ኡዋ ....................................................34*

*4.1.2. ኮራ ....................................................36*

*4.1.3 ፓሮታ ....................................................37*

*4.1.4 ኮንፍ፣ ጨርፉ እና ባሪቴታ ....................................................38*

4.2 ጌጣጌጦች ....................................................40

*4.2.1 የራስ ጌጦች ....................................................40*

*4.2.2 የማንባር ጌጦች ....................................................42*

*4.2.3 የአንገት ጌጦች ....................................................45*

*4.2.4 የእጅ ጌጦች ....................................................47*

*4.2.5 የእግር ጌጥ ....................................................47*

4.3 የፀጉር አሰራር ....................................................49

*4.3.1 ዳፓ ....................................................49*

*4.3.2 ሌሃያ ....................................................50*

*4.3.3 ካሳራ ....................................................51*

**5. የኮንሶ ሄገረሰባዊ አልባሳት ማህበራዊ ፋይዳ ....................................................53**

5.1 ዕድሜን መግለፅ ....................................................53

5.2 ማህበራዊ ደረጃን ማሳየት ....................................................55

5.3 ክፉ መንፈስን መከላከል ....................................................57

5.4 እናትነትን ማሳየት ....................................................58

5.5 ማህበራዊ ሁነቶችን መጠቆም ....................................................59

**6. ማጠቃለያ ....................................................61**

# የምስል ማውጫ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ምስል 1: ለኡዋ መስሪያነት የተዘጋጁ ከክር የተሰሩ ብትን ጨርቆች....36
ምስል 2: ኮራ....37
ምስል 3: ኮንፋ....38
ምስል 4: ጨርፋ....39
ምስል 5: ፓላ....41
ምስል 6: ያጋታቲማ....43
ምስል 7: ሻላ....44
ምስል 8: ሃላሻ....45
ምስል 9: ጭርዋና....46
ምስል 10: ወንድ ልጅ ብቻ ያላት እናት የምታደርገው ሄሮዳ....48
ምስል 11: ሃላሻን ያደረጉ የጎሳ መሪ....56
ምስል 12: ወንድና ሴት ልጆች ያሏት እናት የምታደርገው ሄሮዳ....59

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት በኮንሶ ሃገረሰባዊ አልባሳት እና ጌጣጌጦች ቁሳዊ ባህርያትና ማህበረ-ጥበባዊ ፋይዳ ትንተና ላይ የሚያተኩር ነው:: ዐበይት ዓላማዎቹም የባህላዊ አልባሳቱን፣ ጌጣጌጦቹን እና የማህበረሰቡን የፀጉር አሰራር አካላዊ ገፅታ ማሳየት፤ የአለባበስ ስርዓቱን እና አጋጣሚዎቹን መግለፅ፤ እንዲሁም የአልባሳቱን እና የጌጣጌጦቹን ማህበረ-ጥበባዊ ፋይዳ ማሳየት ናቸው:: ከዚህ በተጨማሪም አልባሳቱ የማህበረሰቡን አባላት ማንነት እና እሴቶች እንዴት እንደሚገልፁ እና በቁሶቹ ዙሪያ እየተደረጉ ያሉ ለውጦች ከነምክንያቶቻቸው ያሳያል:: በዚህም የተመረጡ ሶስት የፀጉር አሰራር፣ ሰባት የአልባሳት እና አስራ ሁለት የጌጣጌጥ አይነቶች ተተንትነዋል::

ይህ ጥናት የተነሳበትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በቃለ መጠይቅ እና በምልከታ በተሰበሰቡ ቀዳማይ መረጃዎች የተመሰረተ ነው:: ጥናቱ አይነታዊ የምርምር አይነት እንደመሆኑ መጠን በታላሚ የናሙና አወሳሰድ ዘዴ ከተመረጡ እና ባህሉን ጠንቅቀው ያውቃሉ ከተባሉ ግለሰቦች፣ ከባህል ቢሮ ሰራተኞችና የእጅ ባለሞያዎች በቃለመጠይቅ እንዲሁም ከመኖሪያ መንደሮች እና ከገበያ ቦታዎች በምልከታ በተወሰዱ መረጃዎች የተገነባ ነው:: ከእነዚህ ቀዳማይ ምንጮች ከተገኙ መረጃዎች በተጨማሪ ከጥናቱ ጉዳይ ጋር ከተያያዙ የጥናት ውጤቶች እንዲሁም መፃህፍት የተገኙ ሃሳቦችንም ያካትታል:: እነዚህ መረጃዎች ገላጭ በሆነ መንገድ ቀርበዋል::

የኮንሶ ሃገረሰባዊ አልባሳት ከጊዜ ወደ ጊዜ በመለወጥ ላይ ናቸው:: ለዚህም ዋነኞቹ ምክንያቶች የንግድ እንቅስቃሴ መስፋፋት፤ የክርስትና በተለይ የፕሮቴስታንት እምነት መስፋፋት እንዲሁም የዘመናዊ ትምህርት ቤቶች መስፋፋት ናቸው:: የአካባቢው ሃገረሰባዊ አልባሳት ከቁሳዊ ፋይዳቸው በተጨማሪ በባህሉ ባላቤቶች ዘንድ የሚታወቁ ተምሳሌታዊ ፋይዳዎች ያሏቸው ከመሆናቸውም በላይ የባለቤቶቹን የእድሜ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ደረጃዎችን የሚያመለክቱ ትዕምርቶች ሆነው ያገለግላሉ:: በሚያስተላልፉት መልዕክት አማካይነትም እድሜን የማሳወቅ፣ ማህበራዊ ደረጃዎች የማሳየት፤ ከክፉ መናፍስት የመጠበቅ፤ እናትነትን እና ሁነቶችን የማሳወቅ ፋይዳ አላቸው::

# 1. መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ቁሳዊ ባህል ከፎክሎር ቅርፆች አንዱ ሲሆን አንድ ማህበረሰብ ለመገልገያነት የሚሰራቸው፣ በአይን የሚታዩ፣ የሚዳሰሱ እና በተጨባጭ የሚገኙ ልዩ ልዩ ቁሶችን ያመለክታል::ይህ የፎክሎር ቅርፅ ስለማህበረሰቡ አጠቃላይ ጉዳይ በተጨባጭ የሚያሳውቅ መሆኑን የተለያዩ የዘርፉ ምሁራን ይጠቅሳሉ::(Prown; 1, Woodward; 3, Sims & Stephen; 13, Michael; 540, Glassie; 41) ቁሳዊ ባህል ከሌሎቹ በተለይም ከቃላዊው ዘርፍ አንፃር ሲታይ አዝጋሚ የለውጥ ሂደት የሚታይበት መሆኑ ለዚህ ጉዳይ እንደ ምክንያትነት ይነሳል:: የማህበረሰቡን የዕለት ተዕለት ህይወት ማለትም እምነቱን፣ አስተሳሰቡን፣ አመለካከቱን ያንፀባርቃሉ:: ይህ የሚሆንበት ዋነኛ መንገድም ማህበረሰቡ ጉልበቱን፣ ጊዜውን፣ ሃብቱንና እውቀቱን አፍስሶ በሚሰራቸው ቁሶቹ አማካይነት ነው:: በመሆኑም ቁሳዊ ባህል ብሄረሰቡ ይህን ሃብቱን ለማስተላለፍ፣ ለማስቀመጥና ለመጠበቅ የሚጠቀምበት አይነተኛ መንገድ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም ባህላዊ ገፅታውን ከሚያሳውቁት ጉዳዮች በተሻለ መልኩ ማህበረሰቡን የመግለፅ ሃይል አለው::(Tilley; 70)

የሰው ልጅ በዕለት ተዕለት ኑሮው ከሚጠቀምባቸው ቁሳቁሶች መሀከል አልባሳት ዋነኞቹ ናቸው:: ባህላዊ አልባሳት ከቁሳዊ ፋይዳቸው ባሻገር የባለቤቶቹን የማህበረሰቡን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ደረጃ በመግለፅ ረገድ ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው ቁሳዊ የባህል ሃብቶች ናቸው:: Twigg የተባሉ ምሁር Tseelonን በመጥቀስ ይህን ሃሳብ ሲያፀኑም “clothes are expressions of identity, one of the pennial means whereby we signal to the social world who and what we are: they are part of our repertoire of social technology, a means whereby ideas of identity are grounded in the visual” (291) ብለዋል:: ስለዚህም የአንድን ማህበረሰብ ማንነት ከመግለፅ እና ከማሳየት አንፃር ባህላዊ አልባሳት ትልቁን ቦታ ይወስዳሉ:: ይህን የሚፈጥረውም አንድም በሃገረሰባዊ አልባሳት እና በተጠቃሚው ማህበረሰብ መካከል የሚኖረው ትስስርና መስተጋብር ነው:: አንድ የማህበረሰብ አባል ከለበሰው ልብስና ከአጠቃላይ የአለባበስ ገፅታው አንፃር ማንነቱንና ምንነቱን መገመት ይችላል:: በመሆኑም በአልባሳቱ ተጠቃሚና በተመልካቹ መካከል ተግባቦትን ይፈጥራል:: ሃገረሰባዊ አልባሳትን ስናነሳ ተያይዞው

የሚመጡ ሌሎች ቁሳዊ ሃብቶችን አሉ:: ይህም ማህበረሰቡ ከአልባሳቱ ጋር በተጓዳኝ የሚያጌጥባቸው ጌጣጌጦች እና የፀጉር አሰራርን ያጠቃልላል::

የአንድን ማህበረሰብ ሃገረሰባዊ አልባሳትና ጌጣጌጦች ማጥናት ማህበረሰቡ ለህይወት ያለውን አመለካከት፣ አስተሳሰብ፣ እምነት እና የመሳሰሉትን ጉዳዮች ለመረዳት ያስችላል:: Judith L. Sebesta የተባሉ ምሁር እንደሚሉት የአልባሳት ጥናት የባህሉን ባለቤቶች ብቻ ሳይሆን መላው የሰው ዘርና ባህሎቹ ምን ያህል የተሳሰሩ መሆናቸውን ያሳያል:: ይህንም "the study of costume illustrates how interwoven the humanities are. . . '(Sebasta; 1) በማለት ይገልፃሉ:: በመሆኑም የኮንሶን ሃገረሰባዊ አልባሳት እና ጌጣጌጦች ማጥናት ለኢትዮጵያ ፎክሎር ጥናት አንዳች አስተዋፅኦ ያበረክት ይሆናል ተብሎ ይታመናል::

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ሃገረሰባዊ አልባሳት የማህበረሰቡን ታሪክ፣ እምነት፣ ስለ ሞትና ህይወት እንዲሁም ስለዓለም ያለውን አመለካከት በመግለፅ ረገድ ላቅ ያለ ፋይዳ አላቸው:: ይህ በመሆኑም ከቋንቋ ጋር የሚመሳሰሉ ትዕምርቶች መሆናቸውን Entwistle እና Wilson የተባሉ ምሁራን ያስረዳሉ:: ማህበረሰቡም የሚተዳደርባቸውን ደንቦች፣ ስርዓቶች፣ እምነቶች፣ ፍልስፍና እና የመሳሰሉትን ሁሉ በእነዚህ ትዕምርቶች አማካይነት ይገልፃል:: አልባሳትና ጌጣጌጦች በሰው ልጅ የዕለት ተዕለት ህይወት ውስጥ ሁሌም የምናገኛቸው ናቸው፤ ለዚህም ነው እንደሁለተኛ የሰውነት ቆዳ የሚታዩት::( Entwistle & Wilson, 45) በመሆኑም የማህበረሰቡን ባህል በሰፊው መግለፅ ይችላሉ:: ይህን ማጥናትም የማህበረሰቡን እውቀት፣ ፍልስፍና፣ አመለካከት እና የመሳሰሉት ለማወቅ በእጅጉ ይረዳል፤ ቁሶችን ማጥናት የሰራውን ማህበረሰብ እንደማጥናት ይወሰዳል። በሃገራችን የፎክሎር ጥናት አልባሳትን እና ጌጣጌጦችን የተመለከቱ ጥናቶች የተወሰኑ ቢሆንም በቂ ናቸው ለማለት አያስደፍርም፤ በተለይ የአልባሳትን ፋይዳ ከማህበረሰቡ ባህል ጋር አቆራኝቶ ማጥናት በበቂ ሁኔታ አይገኝም:: ይህም በዚህ የጥናት መስክ ላይ ክፍተት መኖሩን አመላካች በመሆኑ ለዚህ ጥናት ዋነኛው አነሳሽ ምክንያት ሆኗል::

የኮንሶ ብሄረሰብ በተለይ በእርከን ስራ አለም አቀፍ እውቅናን ያገኘ ነው:: በዚህ ሃገረሰባዊ እውቀት እውቅናን ያገኘው ይህ ብሄረሰብ በሃገረሰባዊ አልባሳቱ አማካይነት

የሚገልፃቸው አስተሳሰቦች፣ ፍልስፍናዎች፣ እምነቶች እና ጥበባትስ ምንድን ናቸው? የሚለው ጥያቄ ሌላው የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ነው:: በኮንሶ ብሄረሰብ ቁሳዊ ባህል ላይ የተሰሩ ጥናቶች በተለይ በሃገረሰባዊ አልባሳት ላይ ተመርኩዞ የተሰራ አንድም ጥናት አለመኖርም ሌላው አነሳሽ ምክንያት ነው::

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የኮንሶን ሃገረሰባዊ አልባሳት እና ጌጣጌጦች ዐበይት ቁሳዊ ገፅታዎችን ማህበራዊና ጥበባዊ ፋይዳዎችን መመርመር ነው::

የጥናቱ ንዑሳን ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፦

1. የኮንሶን አልባሳት፣ ጌጣጌጦችና የፀጉር አልባሳት ዐበይት ቁሳዊ ገፅታዎች ማሳየት
2. የአልባሳቱን አጠቃቀም ስርዓትና ማህበረ- ባህላዊ ዳራዎቹን ማሳየት
3. የአልባሳቱን፣ ጌጣጌጦቹንና የፀጉር አሰራሩን ማህበራዊ እና ጥበባዊ ፋይዳ መመርመር
4. በአልባሳቱ አጠቃቀም ላይ በመታየት ላይ ያሉ ለውጦችን እና ምክንያቶችን ማሳየት

## 1.4 የምርምር ጥያቄዎች

ከላይ የተጠቀሱትን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ ይቻል ዘንድ ጥናቱ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጥናቱ ይመልሳል::

1. ዋና ዋናዎቹ የኮንሶ ሃገረሰባዊ አልባሳት፣ ጌጣጌጦች እና የፀጉር አሰራር ምን ምን ናቸው?
2. የእነዚህ ቁሶች ቁሳዊ ገፅታስ ምን ይመስላል?
3. የአልባሳቱ፣ ጌጣጌጦቹና የፀጉር አሰራሩ ማህበረ-ጥበባዊ ፋይዳዎች ምንድን ናቸው?
4. እነዚህ ቁሳዊ ጥበባት በማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸው ፍቺና እሴት ምንድን ነው?

## 1.5 የመረጃ ምንጭና መሰብሰቢያ ዘዴ

ይህ ጥናት በዋነኛነት ከመስክ በተሰበሰቡ ቀዳማይ መረጃዎች ላይ የተመሰረተ ሲሆን መረጃዎችን ለመሰብሰብም የቃለመጠይቅ እና የምልከታ ዘዴ ተተግብረዋል::

### 1.5.1. ቃለ መጠይቅ

ይህንን ጥናት ለማካሄድ ይረዳ ዘንድ በዋናነት የቃለ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ተግባር ላይ ውሏል:: ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ባህላዊ አልባሳቱና ጌጣጌጦቹ በማህበረሰቡ የሚሰጣቸውን ቦታ፤ ማህበራዊ ፋይዳቸውን፤ በማህበረሰቡ ውስጥ የቁሶቹን ውክልና ወይም ተምሳሌትነት እና የመሳሰሉትን ለመገንዘብ ተተግብሯል:: ለቃለ መጠይቅ የሚረዱ ሶስት አይነት የመረጃ አቀባዮች ሲኖሩ እነዚህም በማህበረሰቡ ዘንድ ባህሉን በተለይ ስለ ሃገረሰባዊ አልባሳትና ጌጣጌጦች ጠንቅቀው ያውቃሉ የሚባሉ ግለሰቦች፤ ሃገረሰባዊ አልባሳትንና ጌጣጌጦችን የሚሰሩ ግለሰቦች እና የባህል ቢሮ ባለሞያዎች ናቸው::

እነዚህን የመረጃ አቀባዮች ታላሚ የናሙና አወሳሰድ ዘዴን በመጠቀም የተወሰዱ ናቸው:: እነዚህ ቁልፍ የመረጃ አቀባዮች መደበኛ ቃለመጠይቅ የተደረገላቸው ሲሆን አልፎ አልፎ የተለያዩ ተያያዥ ጉዳዮችን ለማጣራት ኢ-መደበኛ ቃለመጠይቅ ተደርጎላቸዋል:: ከእነዚህ ቁልፍ የመረጃ አቀባዮች ጋር የተደረገው ቃለመጠይቅ በመኖሪያ ቤቶች እና በስራ ቦታዎች የተካሄደ ሲሆን ከእነዚህ መረጃ አቀባዮች በተጨማሪ በተለያየ ወቅትና በተለያየ አጋጣሚ መንገድ ላይ እና ገበያዎች አካባቢ የተገኙ ግለሰቦችን በአጠቃላይ ስለ አካባቢው እና በተለይ ደግሞ ስለሃገረሰባዊ አልባሳት ኢ-መደበኛ ቃለመጠይቅ በማድረግ መረጃዎች ተሰብስበዋል::

### 1.5.2. ምልከታ

ከቃለ መጠይቅ ዘዴ በተጨማሪ በተወሰነ መንገድ የምልከታ ዘዴ ተግባር ላይ ውሏል:: በዚህ ዘዴ የማህበረሰቡን የአልባሳት አይነት እና ስርዓት፤ ጌጣጌጦችን እና የመሳሰሉትን ጉዳዮች አካላዊ ገፅታ ለማየትና ለመገንዘብ ተችሏል:: ይህን እና የማህበረሰቡን የእርስ በእርስ መስተጋብር ለመመልከትም በተለይ በገበያ ቦታዎችና በመኖሪያ መንደሮች ተገኝቼ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ሞክሬያለሁ:: በእነዚህ ዘዴዎች የሚገኘው መረጃ በፎቶ ካሜራ እንዲሁም በድምፅ መቅረጫ ተሰብስቧል::

በባህላዊ ቁሶች ላይ ትኩረቱን የሚያደርገውን ይህን ጥናት በተለያዩ ንድፈሃሳቦች እና መረጃዎች ለማጠናከር ይረዳ ዘንድ ካዕላይ የመረጃ ምንጮች ተጠቅሜያለሁ:: ከተለያዩ ቤተመፃህፍት እንዲሁም ድረ ገፆች የተገኙ የንድፈሃሳብ መፃህፍት፣ ጥናታዊ ፅሁፎች፣ መፅሄቶች እና መሰል መረጃዎች ተሰብስበዋል:: በመሆኑም ይህ

ጥናት ከርእሰ ጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ባላቸው ንድፈ ሃሳቦች የሚቃኝ ሲሆን በገላጭና ትንታናዊ የምርምር ስልቶች ቀርቧል::

## 1.6 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት በቁሳዊ ባህል በተለይም በሃገረሰባዊ አልባሳትና ጌጣጌጦች ላይ ትኩረት አድርገው ለሚንቀሳቀሱ አጥኝዎችም ሆነ ድርጅቶች እንደ መነሻ መረጃ አቀባይ ሆኖ ያገለግላል:: በተለይ በኮንሶ ብሄረሰብ ባህል ላይ ትኩረታቸውን ለሚያደርጉ አካላት በቁሳዊ ባህል ዙሪያ መረጃ በመስጠት ያገለግላል ተብሎ ይታመናል::

## 1.7 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በኮንሶ ሃገረሰባዊ አልባሳትና ጌጣጌጦች አካላዊ ገፅታ እና ማህበረ_ጥበባዊ ፋይዳዎችን በመግለፅ ላይ የተወሰነ ነው:: ከዚህ ውጭ የአሰራር ሂደታቸውን አይመለከትም:: Wilson የተባሉ ምሁር እንደሚያስረዱት ሃገረሰባዊ አልባሳት(Folk Costume) ከልብሶች(Clothing) በተጨማሪ ጌጣጌጦችን(Jewelry)፣ የፀጉር አሰራርን(Hair styles)፣ ንቅሳትን(tattoos)፣ የገላ ላይ ጌጦችን(Body decorations)፣ ማስኮችን(masks) እና የመሳሰሉትን ሁሉ ያጠቃልላሉ::( Wilson; 147) ነገር ግን ይህ ጥናት ከላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ ልብሶችን፣ ጌጣጌጦችንና የፀጉር አሰራርን ብቻ ይዳስሳል::

የኮንሶ ብሄረሰብ ከኮንሶ ልዩ ወረዳ ውጭ በኦሮምያ ክልል በተልተሌ እና በያቤሎ ወረዳዎች፣ በደቡብ ክልል በባስኬቶ ልዩ ወረዳ፣ በደቡብ ኦሞ ዞን በሰላማጎ ወረዳ፣ በአርባምንጭና በጅንካ ከተሞች ይገኛሉ::(የደ/ብ/ብ/ህ/ ፕሮፋይል፣150) በመሆኑም የዚህ ጥናት ትኩረት የሚሆነው በኮንሶ ልዩ ወረዳ የሚገኘው ብቻ ነው:: ከዚህ በተጨማሪም ይህ ጥናት የልጆችን አልባሳት አያጠቃልልም:: ምክንያቱም በመስክ ቆይታየ ወቅት ባገኘሁት መረጃ መሰረት ህፃናት እስከ 10 ወይም 14 ዓመታቸው ድረስ ልብስ ማድረግና አለማድረጋቸው አከራካሪ ነው::

## 1.8 ያጋጠሙ ችግሮች

በነበረው የጊዜ እጥረት ምክንያት በመስክ ቆይታዬ ወቅት ማግኘት የነበሩብኝን ቁልፍ የመረጃ አቀባይ ግለሰቦች በወቅቱ በአካባቢው ባለመኖራቸው ስለጉዳዩ እውቀት ያላቸውን ግለሰቦች ማግኘት አልተቻለም:: ይህን ክፍተት ለመሙላትም ሌሎች የአካባቢው ነዋሪዎችን ለመጠቀም ተችሏል:: ሌላው በመስክ ላይ ያጋጠመው ችግር አንዳንድ ሃገረሰባዊ አልባሳትን የመመልከት እድል አለማጋጠም ነው:: ለዚህም እንደምክንያት የሆነው አንዳንድ ሃገረሰባዊ አልባሳት በጣም በተወሰኑ ግለሰቦች እጅ ብቻ መገኘታቸው ነው:: ለምሳሌ ያክል "ቱማ" የሚባለው የእጅ ጌጥ የሚገኘው በጎሳ መሪው እጅ ብቻ ነው:: ከዚህ በተጨማሪም አሁን ላለው የሴቶች ቀሚስ መሰረት የነበረውና ከቆዳ ይሰራ የነበረውን "ኡዋ" ለማየት አልተቻለም:: ይህም አንድም በአሁኑ ወቅት የሚጠቀምበት ባለመኖሩ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ሲወርድ ሲዋረድ የመምጣት እድሉ አነስተኛ መሆኑ ነው ምክንያቱም በኮንሶ ባህል መሰረት አንድ ሰው ሲሞት ልብሶች አብረው ስለሚቀበሩ ነው[1]::

በሶስተኛነት እንደ ችግር ያጋጠመው የተተኳሪ ቡድን ውይይት ለማካሄድ የመረጃ አቀባዮች ጊዜ አለማመቻቸት ነው:: በዚህ መረጃ የመሰብሰቢያ ዘዴ የሚገኘውን መረጃ ለማሟላት ተደጋጋሚ ቃለመጠይቅ ተደርጓል:: ሌላው ያጋጠመው ችግር በመስክ ወቅት በተለያዩ ቦታዎች የተገኙ የሃገረሰባዊ አልባሳት ተጠቃሚዎች ፎቶ ለመነሳት ፈቃደኛ አለመሆን ነው:: ይህም በፎቶ ተደግፈው የሚቀርቡ መረጃዎችን ሃይል በተወሰነ መልኩ የቀነሰው ሲሆን ይህን ችግር ለመቅረፍ በአጋጣሚ ያነሳኋቸውን እና ከአንድአንድ ፈቃደኛ ሰዎች ያገኘኋቸውን ፎቶዎች ለመጠቀም ችያለሁ::

## 1.9 የመስክ ቆይታ

የኮንሶ ሃገረሰባዊ አልባሳት ላይ ትኩረቱን ላደረገው ለዚህ ጥናት የሚጥቅም መረጃ የመሰብሰቡ ሂደት የተጀመረው ወደ መስክ ጉዞ ከመደረጉ ቀደም ብሎ ነው:: በዚህ የቅድመ መስክ ዝግጅት ወቅት ስለአካባቢው በደንብ የሚያውቁና የአካባቢው ተወላጆች የሆኑ ግለሰቦችን በማነጋገር ስለአንድአንድ ሁኔታዎች ግንዛቤ ለመያዝ ተሞክሯል::

---

[1] በቃለመጠይቅ ወቅት መረጃ አቀባዮቹ እንዳሉት ይህ የሚሆንበት ምክንያት ከሞት በኂላ ህይወት እና ማህበራዊ ህይወት እንዳለ በመታመኑ ነው:: በመሆኑም የሞተው ሰው ቀድመውት ከሞቱት ጋር ሲቀላቀል እርቃኑን እንዳይሆንና እንዳያገለት ለማድረግ መሆኑን ሲጠቁሙ የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ፕሮፋይል ላይ የሚገኘው ፅሁፍ የሚያመለክተው ደግሞ አልባሳቱ አብረው የሚቀበሩት የሟች የሙት መንፈስ ወደ ቤተሰቦቹ ቤት እየመጣ እንዳይረብሽ በማሰብ ነው በማለት ያትታል::

በቤተመፃህፍት ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ መፃህፍትና የምርምር ስራዎች ሌሎች ስለአካባቢው የተለያዩ ሃሳቦችን ያስጨበጡኝ ናቸው:: ከነዚህ ባለፈ በአሁኑ ሰዓት በአካባቢው የሚኖሩ ሁለት ግለሰቦች ጋር በስልክ በመገናኘት ለመስክ ቆይታየ የተመቻቸ እንዲሆን ለማድረግ ጥረት አድርጊያለሁ::

በዚህ መሰረት ሁኔታዎች ከተስተካከሉ በኋላ ሚያዚያ 21 ከአዲስ አበባ ወደ ኮንሶ ጉዞ ተጀመረ:: ኮንሶ ከአዲስ አበባ በ595 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ ትገኛለች:: ከአዲስ አበባ ወደ ኮንሶ የቀጥታ የመጓጓዣ አገልግሎት ባለመኖሩ እና ወደ ቦታውም በአንድ ቀን መግባት ስለማይቻል በመጀመሪያ ወደ አርባምንጭ መሄድና ማረፍ ግድ ይላል:: አርባምንጭ ካረፍኩ በኋላ በሁለተኛው ቀን ወደ ኮንሶ ካራት በመሄድ በፊት በስልክ አገኛቸው ከነበሩት ግለሰቦች ጋር ተገናኘሁ ስላለው ሁኔታም አጫወቱኝ:: ሰኞ ረፋዱ ላይ የትምህርት ክፍሉ የፃፈልኝን የትብብር ደብዳቤ በመያዝ ወደ ልዩ ወረዳው ባህልና ቱሪዝም ቢሮ አመራሁ:: ደብዳቤየንም ለቢሮው ሃላፊ ሰጠሁ:: የቢሮው ሃላፊ ደብዳቤውን ካነበቡት በኋላ በሃሳቡ መደሰታቸውን በመግለፅ የሚያስፈልገኝን ሁሉ ለማቅረብ እንደሚችሉ ገለፁልኝ:: ሃላፊው ስለቆይታየ ትንሽ ካነጋገሩኝ በኋላ በባህልና ቱሪዝም ቢሮው ውስጥ ባልደረባ የሆነና ስለባህሉ ጠንቅቆ የሚያውቅ የአካባቢው ተወላጅ የሆነ ረዳት መደቡልኝ::

ረዳት ከተመደበልኝ በኋላ የጥናቴን ሃሳብ በማስረዳት መቼ፣ምን ከማን መረጃ ማግኘት እንደምንችል እቅድ ነደፍን:: በዚህ መሰረትም በቀጣይ መጀመር ያለብን በኮንሶ የሚገኙ ሃገረሰባዊ አልባሳትን አካላዊ ገለፃ ለማድረግ ተብሎ የተሞከረ ጥናት በባህል ቢሮው ባልደረቦች ተጀምሮ ስለነበረ ይህን ካካሄዱት ጋር የተወሰነ ውይይት ማድረግ እንዳለብን ረዳቴ በጠቆመኝ መሰረት ውይይቱን ይህን ሃላፊነት ከወሰዱት ጋር በቃለ መጠይቅ መልክ አደረግን:: ይህን ካደረግን በኋላ ባሉት ቀናት ባህሉን ጠንቅቀው ያውቃሉ የተባሉ ግለሰቦችን እንዲሁም የእጅ ባለሞያዎችን እቤታቸውና የስራ ቦታቸው ድረስ በመሄድ ቃለ መጠይቅ ለማድረግ ተችሏል:: ቃለመጠይቁን ለማድረግ በተዘዋወርንባቸው ቦታዎችና ምልከታ ለማካሄድ በተገኘሁባቸው የገበያ ቦታዎች ውስጥ የተለያዩ ሁኔታዎችን ለመገንዘብና ለመታዘብ ችያለሁ::

የኮንሶ ማህበረሰብ ያላቸው የሰው አቀባበል የሚገርም ነበር:: ወደ መስክ ከመውጣቴ በፊት በስልክ አገኛቸው ከነበሩ ግለሰቦች እስከ መረጃ አቀባዮቼ ድረስ ያስተናገዱኝ በጥሩ ሁኔታ ነበር:: ቃለመጠይቅ ለማድረግ በሄድኩባቸው ቤቶች ቤት ያፈራውን

በማቅረብ ነበር ያስተናገዱኝ:: በመረጃ በምሰበስብበት ወቅት ወደ መኖሪያ መንደሮች የመግባት እድሉ የገጠመኝ ሲሆን በእነዚህ መንደሮች ውስጥ የተለያዩ ባህላዊ ጉዳዮችን ለመመልከት ችያለሁ:: ለምሳሌ ያክል የተለያዩ ሃይማኖታዊ እና ማህበራዊ ጉዳዮች የሚስተናገዱበት "ሞራ" በመባል የሚታወቀውን ቦታ እንዲሁም የመቃብር ቦታዎችና በዚህም የሚቆሙ የሚቹን ጀግንነት የሚመሰክሩ ምስሎች ተጠቃሾች ናቸው::

በመስክ ቆይታዬ ሌላው የተገነዘብኩት ነገር በገበያ ቦታዎች ያየሁት የገበያ ሁኔታ ነው::ከአርባ አመታት በፊት በቦታው የነበሩትና ስለ ኮንሶ ባህል በጥልቀት ያጠኑት በዚህ ዙሪያም መፅሃፍ ያሳተሙት Hallpike በወቅቱ ስለነበረው የገበያ ሁኔታ እንደገለፁት በገበያ ቦታዎች ከምግብና ምግብ ነክ ሸቀጦች ይልቅ አልባሳት የሚበዙ መሆኑን ካስረዱ በኋላ ከእነዚህ ውስጥም ብዙዎቹ ከሌላ ቦታዎች የመጡ ልባሽ(ሰልባጅ) ጨርቆች መሆናቸውን ይናገራሉ:: ይህ የምሁሩ ትዝብት አሁንም ድረስ ያለ መሆኑ ካስገረሙኝ ጉዳዮች አንዱ ነው:: በተለይ ሎኮቱ በሚባለው አካባቢ ባለው የገበያ ቦታ በጣም ብዙ ሰልባጅ ልብሶች የሚሸጡ ሲሆን በተቃራኒው ባህላዊ አልባሳት በጣም በጥቂቱ ብቻ ይገኛሉ::

## 1.10 የጥናቱ አደረጃጀት

ይህ የጥናት ፅሁፍ በስድስት ምዕራፎች የተከፋፈለ ነው:: ምዕራፍ አንድ የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ ምን እንደሚመስል የሚያሳይ ሲሆን የጥናቱን ዳራ አነሳሽ ምክንያት ዓላማ የጥናት ዘዴና የመሳሰሉትን የሚያጠቃልል ነው:: ይህም ጥናቱ ምን እንደሚመስል የሚጠቁም ነው:: ከጥናቱ ጋር ዝምድና ያላቸው ጥናቶችና ንድፈ ሃሳቦች በምዕራፍ ሁለት ይዳሰሳሉ:: ይህ ምዕራፍ በዋናነት ሁለት ክፍሎች ያሉት ሲሆን በመጀመሪያው ክፍል ከዚህ በፊት በአልባሳት ዙሪያ የተሰሩ ጥናቶች ምን እንደሚመስሉ በአጭሩ የሚያስቃኝ ነው:: ሁለተኛው ክፍል በጥናቱ የሚነሱት ሃሳቦችን በተመለከት የዘርፉ ምሁራን ያነሷቸው ንድፈ ሃሳቦች ይይዛል:: የጥናቱ ትኩረት የሆነው የኮንሶ ብሄረሰብ ማህበረ-ባህላዊ ዳራ ምን እንደሚመስል በምዕራፍ ሶስት የሚዳሰስ ሲሆን በዚህም የአካባቢው አጠቃላይ ባህላዊና አካላዊ ገፅታ (በተለይ ከአልባሳት ጋር ቀጥተኛም ሆነ ተዘዋዋሪ ዝምድና ያላቸው) በአጭሩ ይቀርባሉ::

የጥናቱ ዋና ክፍል የሚይዘውና በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተገኙ መረጃዎች የሚተነተኑበት ምዕራፍ አራት እንደማሳያነት የተወሰዱ የኮንሶ ሃገረሰባዊ

አልባሳትን ትንታኔ ይይዛል:: በዚህም የአልባሳቱ አካላዊ ገፅታ ከባህሉ አንፃር ትንታኔ ይሠጥባቸዋል:: ምዕራፍ አምስት በምዕራፍ አራት ትንታኔ የተሰጠባቸው አልባሳትን ማህበረ-ጥበባዊ ፋይዳ የሚያሳይ ሲሆን አልባሳቱ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚያስተላልፉትን መልዕክት ይዳስሳል:: የመጨረሻው ምዕራፍ ማጠቃለያ ሲሆን በጥናቱ የተነሱ ሃሳቦችን ያጠቃልላል::

## 2. ክለሳ ድርሳናት

ይህ ምዕራፍ ለጥናቱ እንደ የጀርባ አጥንት የሚያገለግሉ ስለ ቁሳዊ ባህል እና ሃገረሰባዊ አልባሳት በተለያዩ ምሁራን የተነሱ ንድፈ ሃሳቦች እና በዚህ ላይ ትኩረታቸውን ያደረጉ ጥናቶች የሚቃኙበት ነው:: እነዚህ ሃሳቦች በሁለት ክፍሎች ተከፍለው የሚቀርቡ ሲሆን በመጀመሪያው አልባሳትን የሚመለከቱ ንድፈሃሳቦች ይቀርባሉ:: በዚህ ክፍልም የቁሳዊ ባህል ምንነት፣ የአልባሳት ምንነት፣ የአልባሳትና ማንነት ቁርኝት፣ተግባር እንዲሁም የቁሳዊ ባህል ጥናት አስፈላጊነትና የትኩረት አቅጣጫዎች ከትንተና ሂደቶች ጋር ይዳሰሳሉ:: ሁለተኛው ክፍል ቀደም ባሉት ጊዜያት አልባሳትን ዋና ትኩረታቸው አድርገው የተሰሩ የጥናት ስራዎች ይቃኛሉ::

### 2.1 ቁሳዊ ባህል፦ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት

ቁሳዊ ባህል(Material Culture) በሰው እጅ የተሰሩ እና በአይን የሚታዩ እንዲሁም በእጅ የሚዳሰሱ ቁሶች መሆናቸውን ብዙ ምሁራን ይስማሙበታል::(Prown; 1, Glassie; 41, Woodward; 3, Sims & Stephens; 13, ፊቃደ; 15, Michael; 540) Ian Woodward ቁሳዊ ባህልን ሲተነትኑ በእጅ የሚዳሰሱና ግዘፍ ነስተው የሚገኙ ህያው የሰው ልጅ ማህበራዊና ባህላዊ እንቅስቃሴዎች ምስክሮች ናቸው በማለት ነው:: ቁሳዊ ባህል ሁለት የማይገናኙ ጉዳዮች ተቆራኝተው የምናገኝበት ነው፦ አካላዊ ከመንፈሳዊ ጋር:: ቁስ በአይን የምናየው እና በተጨባጭ የምናገኘው አካላዊ ገፅታው የጎላ ነው:: ባህል ረቂቅ የሆነ እና በሃሳብ ደረጃ የሚገኝ ነው:: እነዚህን ሁለት የማይገናኙ ነገሮች በቁሳዊ ባህል ውስጥ እናገኛቸዋለን:: ረቂቅ የሆነው የሰው ልጅ አስተሳሰብ፣ አመለካከት፣ እምነትና መሰል ጉዳዮች ተጨባጭ በሆኑት ቁሶች ይገለፃል::

Sims እና Stephens የተባሉ ምሁራን ቁሳዊ ባህልን በተመለከተ በሰጡት ብያኔ እንደሌሎቹ ሁሉ ተጨባጭነቱ በመግለፅ ቋሚ ወይም ጊዜያዊ ሊሆኑ እንደሚችሉ ጠቁመዋል:: ቋሚ ቁሳዊ ባህል ሲባል ለብዙ ጊዜያት አንዴ እንደተሰሩ ሊቆዩ የሚችሉትን እንደ ሃገረሰባዊ ቤቶች የሆኑት የሚያሳይ ነው:: ከእነዚህ በተጨማሪም በየጊዜው የሚሰሩ እና የሚታደሱ እንደ የፀጉር አሰራር፣ ባህላዊ ምግቦች እና የገላ ላይ ጌጦች ያሉ የቁሳዊ ባህል ቅርፆች አሉ:: በመሆኑም ቁሳዊ ባህል በቋሚነት ከሚገኙት በተጨማሪም ጊዜያዊ የሆኑትንም ያጠቃልላል::

ቁሳዊ ባህል የሰውን ልጅ የዕለት ተዕለት የህይወት መልኮች ለማቆየት የሚረዳ አይነተኛ መንገድ ነው:: ይህም ቁሶች ልክ እንደ ስነቃል ዘርፎች ቀጣይነት ይኖራቸው ዘንድ ከዋኝ አለመፈለጋቸው ነው:: የቁሶች በአንድ ቦታ መገኘት በራሱ ስለ ምንነታቸው ለመመስከር በቂ ነው:: ይህ ባህሪያቸውም የታሪክ ነጋሪነት ሚናቸውን የሚያሳይ ነው:: Glassie እንደሚገልፁት በአለም የሚገኙ ማህበረሰቦች በአብዛኛው ታሪካቸው ለብዙ ዘመናት ተጠብቆ የቆየው በፅሁፍ በሚገኙ መረጃዎች ሳይሆን ማህበረሰቡ በሰራቸው ቁሶች ነው:: በዚህ ምክንያትም ቁሳዊ ባህል ለታሪክ አጥኚዎች ዋና የመረጃ ምንጮች በመሆንም ያገለግላሉ::

ቁሳዊ ባህል የተለያዩ ክፍሎች አሉት:: እነዚህም

1. ሃገረሰባዊ እጅስራ(Folk Craft)
2. ሃገረሰባዊ ምህንድስና(Folk Architecture)
3. ሃገረሰባዊ አልባሳት(Folk Costume)
4. ሃገረሰባዊ ስእል(Folk Art) እና
5. ሃገረሰባዊ የምግብ አሰራር(Folk Cookery)

ናቸው::(ፈቃደ፣ 15)የዚህ ጥናት ትኩረት ሃገረሰባዊ አልባሳት ላይ በመሆኑ ስለ ምንነታቸው፣ ተግባራቸው እና ከማንነት ጋር ያላቸውን ቁርኝት በመቀጠል እንመልከታለን::

### 2.1.1 ሃገረሰባዊ አልባሳት

የሰው ልጅ አልባሳትን መቼና ለምን ተግባር መጠቀም እንደጀመረ በትክክል መናገር አይቻልም:: ሆኖም ከ100,000 ዓመታት በፊት መሆኑን መገመት እንደሚቻል Daneis ያስረዳሉ:: የሃገረሰባዊ አልባሳትን(Folk Costume) ምንነት በተመለከተ ትንተና የሰጡ ምሁራን በርካታ ናቸው:: ከእነዚህ መካከል Yoder እና Wilson ይጠቀሳሉ:: እነዚህ ምሁራን ስለሃገረሰባዊ አልባሳት ምንነት የሰጡት ገለፃ ተቀራራቢ ነው:: Yoder እንደገለፁት ሃገረሰባዊ አልባሳት አንድም የማህበረሰቡን ማንነት የሚያሳዩ ትእምርቶችን የያዙ እንዲሁም በዚያ ማህበረሰብ ውስጥ በሚገኙ ግለሰቦችና በማህበረሰቡ መካከል ተግባቦትን መፍጠር የሚችሉ መሆናቸውን ያስረዳል::

Wilson ሃገረሰባዊ አልባሳትን በተመለከተ የሰጡት ገለፃ ከዚህ ብዙ የተለየ አይደለም:: እንደእሳቸው አባባል ሃገረሰባዊ አልባሳት በማህበረሰቡ ውስጥ ተግባቦትን መፍጠር



ILS LIBRARY

የሚችሉ ትእምርቶችንና ቅርፆችን በመያዝ የማህበረሰቡን አባላት ማንነት መግለፅ የሚችሉ አልባሣት እንደሆኑ ያስቀምጣሉ:: በመሆኑም ሃገረሰባዊ አልባሳት ስንል አንድ ማህበረሰብ የኔ ብሎ በሚመራበት ባህል ውስጥ በሚታወቁ ትእምርቶች የበለፀጉና በማህበረሰቡ ዘንድ ተግባቦትን መፍጠር የሚችሉና በሚያስተላልፉት መልእክትም የተለያዩ ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊ እና የመሳሰሉ ጉዳዮችን ማሳወቅና መግለፅ የሚችሉ ቁሶች ናቸው::(148)

አልባሳት ልዩ ልዩ መልእክቶችን የማስተላለፍ ከፍተኛ የሆነ ብቃት አላቸው:: ይህንንም የሚያደርጉት በተለይ ኢ ቃላዊ በሆነ መንገድ ተግባቦትን በመፍጠር ነው:: በአልባሳት የሚተላለፈው መልእክት በመጀመሪያ ደረጀ የሚያሳዩት የማህበረሰቡ ማንነት ሲሆን ይህም ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ አካባቢያዊና የመሳሰሉ ጉዳዮችን እንደሚያጠቃልል Svensson ያስረዳሉ:: በትእምርቶች አማካኝነት የሚተላለፈው መልእክት ትርጓሜ የሚወሰነው አንድም በለባሹ ማንነት ወይም በመለበሻ አጋጣሚው እንዲሁም በመለበሻ ቦታው ሲሆን ይህም የአልባሳት ትእምርታዊ ፋይዳ አውድ ላይ መሰረት ያደረገና አውዳዊው ተፅዕኖው የጎላ መሆኑን ያሳያል::

## 2.1.2 አልባሳትና ማንነት

የሰው ልጅ በሚሰራቸው፣ በሚጠቀምባቸው እና በአካባቢው በሚገኙ ቁሶች ማንነቱን ይገልፃል:: እነዚህ ቁሶች ማህበራዊ ትርጓሜን የመፍጠር አቅም አላቸው:: በመሆኑም ባህላዊ ቁሶች በአንድ ባህል ውስጥ የማህበረሰቡንም ሆነ የግለሰብን ማንነት በማሳየት እንዲሁም በመቅረፅ ረገድ ከፍተኛ ድርሻ አላቸው:: ማንነት(Identity) ማለት አንድ ማህበረሰብ ወይም ግለሰብ "ማን ነኝ?" ለሚለው ጥያቄ የሚያስቀምጠውና የሚፈጥረው በማህበራዊ መንገድ የተወሰነና የተገደበ መልስ መሆኑን Woodward ያስረዳሉ::(134) ከእንደነዚህ አይነት ቁሶች ውስጥ ደግሞ አልባሳት ዋነኞቹ ናቸው:: አልባሳት ማንነትን በማሳየትም ሆነ በመቀየር ወይም በማጥፋት ረገድ የራሳቸው ድርሻ እንዳላቸው Twigg " Clothing can play an important part in signaling or erasing aspects of identity" በማለት ያስረዳሉ::

አልባሳት ማህበረሰባዊ ማንነትን በመቅረፅ ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ሲኖራቸው በአልባሳት ውስጥ የሚገኙ ትእምርቶች የግለሰብንም ሆነ የማህበረሰቡን ማን መሆን በደንብ የመግለፅ ብቃት እንዳላቸው Baatshwana የተባሉ ምሁር ይገልፃሉ:: ይህም አልባሳት ከአካላዊ ገፅታቸው በተጨማሪ በሚይዟቸው ትእምርቶች አማካኝነት

ከሚያስተላልፏቸው ጉልህ መልእክቶች የመነጨ መሆኑ የሚያሳይ ነው:: Twigg የተባሉት ምሁር Tseelonን በመጥቀስ የአልባሳትና የማንነትን ጉዳይ ሲገልፁ *"Clothes are expressions of identity, one of the perennial means whereby we signal to the social world who and what we are; they are part of our repertoire of social technology, a means whereby ideas of identity are grounded in the visual."(Twigg; 5)*

ብለዋል:: አልባሳት ማን እና ምን መሆናችንን በግልፅ የምናሳይባቸው እና የምንገልፅባቸው መንገዶች ናቸው:: በመሆኑም በአልባሳት እና በማንነት መካከል ቁርኝት መኖሩን መረዳት ይቻላል::

### 2.1.3 የአልባሳት ተግባር

አልባሳት አራት መሰረታዊ ሊባሉ የሚችሉ ተግባራት እንዳሏቸው የዘርፉ ምሁራን ይጠቅሳሉ:: Kaiser እነዚህን አራት ተግባራት የሰው ልጅ በመጀመሪያ ለምን አላማ አልባሳትን ተጠቀመ ለሚለው ጥያቄ የሚሰጡ የቲወሪ አቅጣጫዎች እንደሆኑ ያስረዳሉ::

#### የመከላከል ተግባር

ይህ የአልባሳት የመጀመሪያውና ዋነኛው ተግባር ሲሆን አልባሳት የሰውን ልጅ ውጫዊ አካል ከተለያዩ ተፈጥሯዊ ችግሮች ማለትም ከሙቀት ከቅዝቃዜ ከተለያዩ ነፍሳት እንዲሁም እንስሳት የመጠበቅ ተግባር እንዳላቸው የሚያሳይ ነው:: ይህ ተግባር በአብዛኛው የሰው ልጅ በሚኖርበት አካባቢ በሚከሰቱ የአየርንብረት ልዩነቶችና ሌሎች ተፈጥሯዊ ጉዳዮች ጋር የተቆራኘ ነው:: አልባሳት የሰውን ልጅ ውጫዊ አካል ከተለያዩ ክስተቶች ከመጠበቅ ባለፈ የሰውን ልጅ ከተለያዩ ክፉ መናፍስት የመከላከል ተግባርም እንዳላቸው Gracia ይገልፃሉ:: በመሆኑም የአልባሳት የመከላከል ተግባር ከአካላዊ በተጨማሪ መንፈሳዊውንም የሚያጠቃልል መሆኑን መገንዘብ ይቻላል::

#### ሃፍረትን የመሸፈን ተግባር

ይህ ተግባር የሰው ልጅ እንዳይታይበት የሚፈልገውን የሰውነት ክፍል ከእይታ ለመሸፈን ሲባል አልባሳትን በሚጠቀምበት ጊዜ የሚመጣ ነው:: እንደ Kaiser(15) አባባል ይህ የአልባሳት ተግባር መፀሃፍ ቅዱሳዊ መነሻ ያለው ነው ባይ ናቸው::

ይህም በመፀሃፍ ቅዱስ ታሪክ መሰረት የሰውልጅ መጀመሪያ የሚባሉት አዳምና ሄዋን አትብሉ የተባሉትን በመብላታቸው ፀጋቸው ሲገፈፍ ሃፍረታቸውን ለመሸፈን የተጠቀሙበትን የሚያስታውስ መሆኑን ነው:: በመሆኑም የሰውልጅ እንደ ባህሉ መታየት የሌለባቸውንና ነውር የሚባሉትን የሰውነት ክፍሎች ለመሸፈን የሚገለገልበት ሲሆን የአልባሳት ተግባር ሃፍረትን የመሸፈን ይሆናል:: ከዚህ በተቃራኒ አልባሳት ሰውነትን የማጋለጥ ተግባር አላቸው:: ይህ አይነቱ የአልባሳት ተግባር አንድ ለባሽ የሰውን አትኩሮት ለመሳብ ሲባል የሚከሰት ነው:: ይህም በተለይ ወሲብ ቀስቃሽ የሆኑና ሰውነትን የሚያጋልጡ ልብሶችን በሚደረጉበት ጊዜ የሚፈጠር እንደሚፈጠር Kaiser ያስረዳሉ::(15) አልባሳት ሰውነትን ለመሸፈን እንደሚያገለግለው ሁሉ ሰውነትንም ለማጋለጥ ይረዳል:: ለዚህም በጣም ስስ ልብሶች ተጠቃሾች ናቸው::

የማስዋብ ተግባር

አልባሳት ከሌሎች ተግባራቸው በተጨማሪ ለማጌጫነት ያገለግላሉ:: ይህም ተግባር ሰዎች ራሳቸውን በጠበቀ መልኩ ውበታቸውን ለማጉላት ሲሉ በሚጠቀሙበት ጊዜ የሚከሰት ነው:: ራስን ማስዋብ የተመልካቹን አትኩሮት ከመሳቡም በተጨማሪ የለባሹን ማህበራዊ ደረጃ እና ማንነት በማሳየት ያገለግላል::

### 2.1.4 የቁሳዊ ባህል ጥናት

የቁሳዊ ባህል ጥናት እንደሌሎች የፎክሎር ዘርፎች ጥናት ቀደምት ሳይሆን የቅርብ ጊዜ የጥናት ትኩረት መሆኑን የዘርፉ ምሁራን ያስገነዝባሉ:: ይህ የጥናት ዘርፍ የአንድ የትምህርት መስክ ብቻ ጉዳይ ሳይሆን የበርካታ የትምህርት ዘርፎች የጋራ የጥናት ሃብት ሲሆን ይህም በተለይ የፎክሎርን፣ የአርኪኦሎጂን፣ የአንትሮፖሎጂን፣ የታሪክንና መሰል ዘርፎችን የሚያካትት ነው::(Woodward; 3 & 4) የቁሳዊ ባህል ጥናት ዋና ትኩረት በቁሶቹና በማህበረሰቡ መካከል ያለውን ግንኙነት ላይ ሲሆን በዚህም በቁሶቹና በማህበረሰቡ መካከል ያለውን ተራክቦ ወይም መስተጋብር መመርመር መሆኑን Millerንና Tilleyን በመጥቀስ Oestigaard(28) ያስረዳሉ::

#### 2.1.4.1 አስፈላጊነት

ሰዎች አመለካከታቸውን እና እምነታቸውን የሚገልፁትም ሆነ እራሳቸው የሚገለፁበት በሚሰሯቸው ቁሶች እንደሆነ Prown በአፅንኦት ይገልፃሉ:: በዚህ ምክንያትም ቁሳዊ ባህልን የማጥናት አስፈላጊነትን በተመለከተ በርካታ ምክንያቶችን

ያስቀምጣሉ:: ቁሶች የሚገለገልባቸውን ማህበረሰብ እሴት ከነሙሉ ለዛቸው ይዘው በማቆየት ተወዳዳሪ የማይገኝላቸው ናቸው:: ይህም የማህበረሰቡን ባህላዊ ገፅታ በቁሶቹ አማካኝነት እንድናውቅ የሚያደርግ በመሆኑ ቁሳዊ ባህልን ማጥናት ተገቢ እንደሆነ ያመለክታል::(Prown; 2) Fleming ይህን የቁሶችን መጠናት አስፈላጊነት እንዲህ በማለት ይገልፁታል:: *"Along with the man's physical constitution, his ideas, and institutions, the physical settings in which he has lived, and the records of his actions in time, there is an obvious, natural, universal fascination with the things man has made."(Fleming; 153)*

ቁሶች የቀደምት አመታት ውጤቶች በመሆናቸው የድሮውን ለመናገር የሚያስችሉ ብቸኛ የታሪክ ምስክሮች ናቸው:: በመሆኑም የአንድን ማህበረሰብ ታሪክ ለማወቅ ቁሶቹ እንደ ትልቅ መረጃ የሚያገለግሉ በመሆናቸው የመጠናታቸው አስፈላጊነት አያጠራጥርም::(Prown, 3) ከዚህ በተጨማሪ ቁሶች ከቃላት ይልቅ ውክልናቸው በብዙሃን ዘንድ ተቀባይነት ያለው በመሆኑ የተሻለ ተቀባይነት ሲኖራቸው በተለይም ቀደም ባሉት ጊዜያትም ሆነ በአሁኑ ወቅት ባልተማረው የህብረተሰብ ክፍል ዘንድ ተግባቦትን በቀላሉ መፍጠር የሚችሉ በመሆናቸ የመጠናታቸውን አስፈላጊነት ሁሉንአቀፍ ያደርገዋል:: በእነዚህና መሰል ምክንያቶች የተነሳ ቁሳዊ ባህልን ማጥናት እጅግ አስፈላጊ ሲሆን እንደ Prown አገላለፅ ይህን ዘርፍ የዘነጋ ጥናት ጎደሎነቱ የማያጠያይቅ መሆኑን በማንሳት ነው::(Prown; 5) ከዚህ በተጨማሪም Fleming የሰው ልጅን ለማጥናት መዘንጋት የሌለበት መስክ መሆኑን ለማስረዳት "To know man, we must study the things he has made" በማለት ገልፀዋል::(Fleming, 153)

### 2.1.4.2 የቁሳዊ ባህል ጥናት የትኩረት አቅጣጫዎችና ሂደቶች

#### የትኩረት አቅጣጫዎች

ቁሳዊ ባህል ሲጠኑ ትኩረት ሊደረግባቸው ነጥቦችን በተመለከተ ሃሳብ ከሰነዘሩ ምሁራን መካከል Schelereth እና Fleming ይጠቀሳሉ:: Schelereth ባህላዊ ቁሶች ስናጠና ዘጠኝ ጉዳዮች ላይ ማተኮር እንዳለብን የሚገልፅ ሲሆን እነዚህም የጥበቡን ታሪካዊነት (Art Historical)፣ ትዕምርታዊነት (Symbolic)፣ ባህላዊነት(Cultural) ፣ አካባቢያዊነት (Enviromental)፣ አገልግሎት (Functionalist) ፣ መዋቅራዊነት (structuralist)፣ ባህሪ አመላካችነት (Behaviorist) ፣ ማህበረሰብ (Community) እና ማህበራዊ ታሪካዊነት (Social Historical) ናቸው:: Fleming የSchelerethን ዘጠኝ

ወደ አምስት በማውረድ የትኩረት ነጥቦች መሆን ያለባቸው የቁሱ ታሪክ (Its' history)፣ የተሰራበት ንጥረነገር (Material)፣ አወቃቀር (Construction)፣ አሰራር (Design) እና አገልግሎት (Function) መሆናቸውን ይጠቁማሉ::

**ሂደቶች**

የቁሳዊ ባህል ትንተና በምን አይነት ሂደት ማለፍ አለበት ለሚለው ጥያቄ Prown እና Fleming በተቀራራቢ ግን በተለያይ መልክ መልስ ሰጥተዋል:: Prown ቁሶችን ስንተነትን ሶስት ደረጃዎችን ማለፍ እንዳለባቸው ይገልፃሉ:: እነዚህ ደረጃዎችም ገለፃ፣ ምርመራና መላምት ናቸው:: በእነዚህ ደረጃዎች ውስጥም የቁሱ ምንነት፣ በቁሱና በተመልካቹ መካከል ያለው መስተጋብር እና ወደ ድምዳሜ የሚያደርስ መላምት መቅረፅን ይካተታሉ::(Prown, 7) Fleming የተወሰኑ ለውጦችን በማከል ወደ አራት ከፍ ያደርጓቸዋል:: የመጀመሪያው ደረጃ መለየት(Identification) ሲሆን ይህም በውስጡ ምደባን፣ ማፅደቅንና ገለፃን የሚያካትት ነው:: ምደባ የሚደረገው እንደ ጥናቱ ቢሆንም በተግባሩ ወይም በተሰራበት ቁስ አልያም በአሰራሩ እንዲሁም በአወቃቀሩ ሊሆን ይችላል:: የዚህ ደረጃ ዋና ዓላማ ስለሚጠናው ቁስ ትክክለኛ መረጃ ማቅረብ ነው:: ግምገማ(Evaluation) ሁለተኛው የሂደት ደረጃ ነው:: ይህም የሚጠናው ቁስ ከሌሎች ተመሳሳይ ቁሶች ጋር ማነፃፀርን የሚያካትት ነው::(Fleming, 156)

ባህላዊ ትንተና(Cultural Analysis) ሶስተኛው ደረጃ ሲሆን በሚጠናው ቁስና በባህሉ መካከል ያለውን የተለያዩ የግንኙነት መስመሮች የሚመረመርበት ነው:: ይህ ደረጃ በተለይ ቁሱ በባህሉ ውስጥ ያለውን ተግባር የሚመለከትና ይህም ተግባር በግልፅ የሚታየውን(ተጨባጭ የሆኑትን ተግባራት) እንዲሁም በተጨባጭ የማይታየውንና በትእምርቶች የሚተላለፈውን ተግባርንም የሚያካትት ነው:: የመጨረሻው ደረጃ ፍከራ(Interpretation) በሌሎች ደረጃዎች የተተነተኑትን ቁሶች ትርጓሜ ካለው ባህል ጋር ማየትን የሚጠይቅ ነው:: የFleming የሂደት ደረጃዎች ከPrown ይልቅ ቁሱን ከሚገኝበት ባህል አንፃር ከማየት አንፃር የተሻለ ሆኖ ይገኛል:: በመሆኑም ይህ የFleming የሂደት ደረጃዎች ተመራጮች ሆነዋል::

## 2.2 የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት

በሃገራችን ኢትዮጵያ ባህላዊ አልባሳትን የተመለከቱ ጥናቶችና ፅሁፎች መውጣት የጀመሩ ከአራት አስርት ዓመታት በፊት ነበር:: የእነዚህ ቀደምት ጥናቶች ትኩረት በአብዛኛው በእጅ ባላሙያዎች ህይወትና በሙያው ላይ የነበረ ሲሆን ከሃገረሰባዊ የእጅ ስራ ጋር የተያያዙ ጥናቶች ናቸው:: እነዚህ ጥናቶች ከማህበረሰብ ጥናት የተሰሩ ናቸው:: ይህን ካጠኑ አጥኝዎች በተለይ Richard Pankhurst እና Silverman ተጠቃሽ ናቸው:: ሃገረሰባዊ አልባሣትን ከባህሉ እና ከማህበረሰቡ አንፃር በማየት ትንተና የሚሰጡ ጥናቶች ግን የቅርብ ጊዜ ክስተቶች ናቸው ማለት ይቻላል በተለይ ከ1990ዎቹ ጀምሮ ::

እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ2002 የተሰራው የPeri Klem ጥናት በሃገረሰባዊ አልባሳት ጥናት ቁሶቹን ከማህበረሰቡ ማህበረሰባዊ ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊ ና ባህላዊ ጉዳዮችን ጋር በማስተሳሰር እና ይህንንም አውዳዊ በሆነ መንገድ ከተሰሩ ስራዎች ፊርቀዳጅና ጥልቅ ምርምር የተካሄደበት የፒኤችዲ ጥናት ነው:: ይህ *Shaping the future, Wearing the Past: Dress and the Decorated Body among the Afan Qallo Oromo in East Hararghe, Ethiopia* በሚል ርዕስ የተሰራው ይህ ስራ ትኩረት የቃሉ ኦሮሞ ሴቶች ባህላዊ አልባሳትና ሌሎች መዋቢያዎችን ታሪካዊ ዳራውን መተንተንና በዚህም ባህላዊ አልባሳቱን ከነበረው የንግድ እንቅስቃሴ፣ ከእስልምና እምነት መጀመር ጋር እና ከተለያዩ ክስተቶች አንፃር ማየት ሲሆን ከዚህ ጋርም አልባሳቱን ከማህበረሰቡ ታሪክ፣ ማንነትና ውበት ጋር በማያያዝ የሚመረምር ነው:: ይህ ጥናት በተለይ ባህላዊ አልባሳትንና መዋቢያዎችን ከተጠኚው ማህበረሰብ ታሪክ ላይ በመመስረት የተሰራ ነው::

ከPeri ጥናት በኂላ የመጡና ትኩረታቸውን በባህላዊ አልባሳትና ጌጣጌጦች ላይ ያደረጉ ሰባት የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች ያሉ ሲሆን እነዚህም የኤአለም አረዶ(2000) "የአርሲ ሴቶች ጌጣጌጥ ጥናት በኮኮሳና ገደብ ሀሰሳ ወረዳዎች"፤ ያሬድ ተፈራ(2002) "በሰቆጣና በአርገሌ ገጠራማ ወረዳዎች የሴቶችና የወንዶች የአለባበስና የአጊያጊያጥ ማህበራዊ እሴቶች"፤ ሰይድ ይማም(2002) "በከሚሴ ከተማ ዙሪያ በሚገኙ ገጠር አካባቢዎች የወጣት ወንዶችና ሴቶች አለባበስና አጊያጊያጥ"፤ ዋልተንጉስ መኮንን(2000) "የሽመናና የጥልፍ ትውፊት በአክሱም"፤ Sintayahu

Kidanie(2010) "Traditional Cloth- Making and its Dynamics in post Libration Addis Ababa: Weaving among the Dorze of Siromeda"፣ Zufan Fikre(2010) "Traditional Cloth- Making in Kutaber of south Wollo" እና ዐብዬ አስማማው(2000) "የአርጎባ ብሄረሰብ የቤት ውስጥ መገልገያና የማጌጫ ቁሶች በአማራ ክልል ደቡብ ወሎ ዞን አርጎባ ልዩ ወረዳ" የሚሉ ሲሆኑ በአልባሳት ስያሜ ላይ የተሰሩ ሁለት የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች አሉ እነዚህም አያል አድማሱ(1992) የጎጃም አካባቢ የአልባሳት ስያሜ እና የውብሸት አስፋው(1972) የወይዛዝርት አልባሳትና ጌጣጌጥ ስሞች በአማራው ክልል የሚሉ ናቸው::

ሰባቱን የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች እንደተነሱበት ጉዳይ ለሶስት መድቦ ማየት ይቻላል:: የመጀመሪያው ምድብ ጉዳያቸውን ከሃገረሰባዊ አልባሳት ውስጥ አልባሳትም ጌጣጌጦችም ላይ ያደረጉ ሶስት ጥናቶችን ሲይዝ ሁለተኛው ምድብ ደግሞ ትኩረታቸውን በአልባሳት ላይ ብቻ ያደረጉ ሶስት ጥናቶች ይገኛሉ:: ጌጣጌጦች ላይ ትኩረት በማድረግ የተጠናውን አንድ ጥናት በሶስተኛው ምድብ እናገኛለን:: እነዚህ ጥናቶች ምንም እንኳን እንደየምድባቸው የተነሱበት የጥናት ትኩረት ቢመሳሰሉም እንደ ተነሱበት የትኩረት አቅጣጫ፣ አተያይና የጥናት ዓላማ ይለያያሉ:: ይህን እና የጥናቶቹን ቅኝት ቀጥለን እንመለከታለን::

በመጀመሪያው ምድብ የሚመጡ ሶስት ጥናቶች ትኩረታቸውን በባህላዊ አልባሳቱና ጌጣጌጦቹ ላይ ሲሆን ጉዳያቸውም የእነዚህን ቁሶች ምንነት የአለባበስ ስርዓትና ፋይዳ እንዲሁም ተያያዥ ጉዳዮችን የሚተነትኑ ናቸው:: በዚህ ምድብ የሚመጡት ጥናቶች የየኔአለም አረዶ "የአርሲ ሴቶች ጌጣጌጥ ጥናት በኮኮሳና ገደብ ሀሰሳ ወረዳዎች"፣ የያሬድ ተፈራ "በሰቆጣና በአርገሌ ገጠራማ ወረዳዎች የሴቶችና የወንዶች የአለባበስና የአጊያጊያጥ ማህበራዊ እሴቶች" እና የሰይድ ይማም "በከሚሴ ከተማ ዙሪያ በሚገኙ ገጠር አካባቢዎች የወጣት ወንዶችና ሴቶች አለባበስና አጊያጊያጥ" የሚሉት ናቸው::

እነዚህ ጥናቶች ምንም እንኳን የተለያዩ ቢሆኑም ተመሳሳይ ጉዳዮችንም ሲያነሱ ይታያሉ:: ለምሳሌ ሶስቱም ጥናቶች የአልባሳቱንና የጌጣጌጦቹን አካላዊ ገለፃ ከማቅረብ በተጨማሪ ተግባራቸውንና የእጅ ባለሞያዎችን ህይወት በስፋት ይገልፃሉ:: የየኔአለምና የያሬድ ጥናቶች ከዚህ በተጨማሪም ሌሎች ጉዳዮችንም በማንሳት ይመሳሰላሉ:: ሁለቱም ጥናቶች በቁሶቹ ላይ የታየውን ለውጥ የሚመረምሩ ሲሆን የሰይድ ጥናት ደግሞ ከዚህ ጋር በተያያዘ በሃገረሰባዊው አልባሳት ላይ ተፅእኖ

የሚፈጥሩ ጉዳዮችን በማወቅ ቁሶችን ጠብቆ ለማቆየት የሚደረገውን ጥረት ያያል:: በሌላ በኩል የየኔአለምና የሰይድ ጥናቶች የአልባሣቱንና የጌጣጌጦችን የመለበሻ አጋጣሚዎች በስፋት በማየታቸው ይመሳሰላሉ:: ከዚህ ውጭ ግን ሁሉም ጥናቶች የሚያነሷቸው ሌሎች ጉዳዮችን የያዙ በመሆናቸው እያንዳንዳቸውን እንደሚከተለው ይታያሉ::

የኔአለም አረዶ በ2000 ዓ ም ባቀረበችው ጥናት የአርሲ ማህበረሰብ ሴቶች በተለያዩ የእድሜና ማህበራዊ ደረጃዎች የሚለበሱ ባህላዊ አልባሳትንና ጌጣጌጦች የቀድሞና የአሁን ይዞታንና አሁን ያለበትን ደረጃ የሚመረምር ሲሆን የአልባሳቱን ጠቀሜታ በሃይማኖት ምክንያት የሚከሰት የአጠቃቀም ልዩነት መኖሩንም ይገልፃል:: የየኔአለም ጥናት ተተኳሪ ቡድኑ ሴቶች ብቻ ከመሆኑ አንፃር ፆታ ተኮር የሆኑ የተለያዩ የቲዎሪ አቅጣጫዎችን ቢተገብር የተሻለ ሊያደርገው ይችል እንደነበር መገመት ይቻላል:: እንደ Kaiser ገለፃ ባህላዊ አልባሳት በፆታ ከፋፍለን ስናያቸው ልንጠቀምባቸው የምንችላቸው የተለያዩ አይነት የቲዎሪ አቅጣጫዎች እንዳሉ የጠቀሱ ሲሆን ከነዚህም የSemiotics እና Feminist Theory ተጠቃሾች ናቸው:: በነዚህም ማህበረሰቡ አልባሳቱን ከፆታ ልዩነት ጋር አያይዞ የሚኖረውን አመለካከት አስተሳሰብና መሰል ጉዳዮችን ማየት ይቻላል::ከዚህ በተጨማሪም ፆታን መሰረት ባደረጉ ጥናቶች ሊታይ የሚችለው Symbolic-Interactionist አንፃር ሲሆን ይህም በአልባሳቱ ውስጥ ፆታ ተኮር የሆኑ ኮዶችን ትርጓሜ እንድንረዳ የሚያደርግ መሆኑን Kaiser ያስረዳሉ::

የያሬድ ተረፈ 'በሰቆጣ እና በአርጎቤ ገጠርማ ወረዳዎች የሴቶችና የወንዶች የአለባበስና የአጊያጊያጥ ማህበራዊ እሴቶች' ጥናት በሁለቱ ወረዳዎች ያለውን የአለባበስና የአጊያጊያጥ ልማዶችን የሚመረምር ሲሆን ቁሶቹን፣ የቁሶቹን አሰራር፣ ተግባር፣ ባለሞያዎቹን እንዲሁም የተደረገባቸውን ለውጥና ከቁሶቹ ጋር ተያይዘው የሚባሉ ስነቃሎችን የሚያሳይ ነው:: የFleming 5 የትኩረት አቅጣጫዎችን መሰረት በማድረግ ትንተናውን ያደረገ ሲሆን ለማሳያነት የተመረጡ አራት አልባሳትና ሰባት ማጌጫዎች ያካትታል:: ያሬድ ከዚህ በተጨማሪ በአልባሳቱና ጌጣጌጦቹ ላይ ያለውን ለውጥ ምንነት የለውጡን ምክንያት እና ማህበረሰቡ ለለውጡ ያለውን አመለካከት አይቷል:: ከሌሎች ጥናቶች የያሬድ ጥናት ቁሶቹን ከማህበረ-ባህላዊ አውድ በመግለፅ የተሻለ ሆኖ ይገኛል::

በከሚሴ ዙሪያ በሚገኙ አምስት የገጠር አካባቢዎች የሚገኙ ወጣት ወንዶችና ሴቶች የሚለብሱትን ባህላዊ አልባሳትና ጌጣጌጦችን ምንነት አገልግሎትና ማህበረ_ባህላዊ ፋይዳዎችን የሚመረምረው የሰይድ ይማም ጥናት ተጠኝ ቡድኑ አልባሳቱንና ጌጣጌጦቹን መቼና ለምን አላማ እንደሚጠቀምባቸው ይዳስሳል:: የዚህ ጥናት ተጠኝ ቡድን ወጣት ወንዶችና ሴቶች ሲሆኑ በተለይ ሴቶች ከመታጨታቸው በፊት በታጨበት ወቅትና ካገቡ በኋላ የሚጠቀሟቸውን አልባሳትና ጌጣጌጦች ላይ ትንተና ተሰጥቷል:: ከዚህ በተጨማሪም ጥናቱ የአልባሳቱ ቀለሞች ትእምርታዊ ትርጓሜ የሰጠ መሆኑ አስፈላጊ መሆኑ የማያጠራጥር ቢሆንም የተጠኘው ቡድን ወጣቶች እንደመሆናቸው መጠን ከወጣትነት የእድሜ ደረጃ ጋር ተያይዞው በማህበረሰቡ የሚነሱ ጉዳዮችን መተንተንም እጅግ አስፈላጊ ነው ማለት ይቻላል:: ከዚህ አንፃር መታየቱ አንድም ማህበረሰቡ ለዚህ የእድሜ ደረጃ ያለውን አመለካከትና አስተሳሰብ ማወቅ የሚያስችል ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የለባሾቹን ማህበራዊ ደረጃ ለማወቅ ያስችለናል::

በሁለተኛው ምድብ የሚመጡት ሶስት ጥናቶች ትኩረታቸው በአልባሳት አሰራርና ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮችን የሚዳስሱ ሲሆኑ እነዚህ ጥናቶችም የዋልተንጉስ መኮንን ፤ የስንታየሁ ኪዳኔ እና የዙፋን ፍቅሬ ናቸው:: እነዚህ ሶስት ጥናቶች በአልባሳት የአሰራር ሂደት ላይ ያነጣጠሩ ጉዳዮችን የሚተነትኑ ቢሆኑም እንደተነሱበት የትኩረት አቅጣጫ ግን ይለያያሉ:: ሶስቱም ጥናቶች በሃገረሰባዊው የአልባሳት አሰራር ሂደት ላይ ለውጥ መኖሩን የሚያሳዩ መሆናቸውን የሚያሳዩ ቢሆኑም ለዚህ ጉዳይ እንደሰጡት ትኩረት ግን ይለያያሉ:: ለምሳሌ የስንታየሁ ጥናት ሙሉ በሙሉ በለውጡ ላይ የተሰራ ሲሆን የዋልተንጉስ ና የዙፋን ስራዎች ግን በተወሰነ መልኩ ይዳስሱታል:: የዋልተንጉስና የዙፋን ጥናቶች በአብዛኛው ያተኮሩት ቁሶቹ እንዴትና በምን ይሰራሉ በሚሉት ጉዳዮች ላይ ሲሆን የስንታየሁ ጥናት ደግሞ የአልባሳት የአሰራር ሂደት ለውጥ ላይ ያነጣጠረ ስራ ነው::

በ2000 ዓ. ም የተሰራው የዋልተንጉስ መኮንን "የሸመናና የጥልፍ ትውፊት በአክሱም" ጥናት በአልባሳት ላይ ትኩረት ካደረጉ ስራዎች አንዱ ሲሆን ይህ ስራም የሸመናና የጥልፍ ትውፊት በአክሱም እንዲከሰቱ ያደረጉና እነሱንም ከሌሎች የአኗኗር ዘይቤዎች ጋር ያስተሳሰራቸውን የእምነት የአምልኮና የእሴት ገፅታዎችን ለማሳየት የተጠና ነው:: አጥኚው የሸማ እቃዎችን ትእምርታዊ ፋይዳ በሰፊው የተነተነ ሲሆን በዚህም ሁሉም ቁሶች ሃይማኖታዊ ትርጓሜ ያላቸው መሆናቸውንና

ይህም የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ስርዓትና አስተምህሮ ጋር በእጅጉ የተቆራኘ መሆኑና ለዚህ ጉዳይም ቃለመጠይቅ የተደረገላቸው ግለሰቦች የቤተ ክርስቲያኗ የሃይማኖት አባቶች መሆናቸው ተጠቅሷል:: እንደጥናቱ ገለፃ ሁሉም የሸማ ሰሪዎች የእስልምና እምነት ተከታይ ናቸው:: ከዚህ አንፃር ለቁሶቹ የተሰጠው ሃይማኖታዊ ትርጓሜ የሸማ ሰሪዎቹንም አስተሳሰብና አመለካከት ያካተተ ሊሆን የሚገባው ነው ይቻላል:: ምክንያቱም ቁሶቹ ለባለሞያዎቹ ከቁስነታቸው ባለፈ ምን እንደሆኑም ማየት ስራውን የተሟላ ሊያደርገው ይችል ነበር::

የስንታየሁ ኪዳኔ ጥናት በተለይ ከባህል ለውጥ ጋር በተያያዘ በጥናቱ ቦታ ማለትም በሽሮሜዳ በሚገኙ የዶርዜ ሸማ ሰሪዎችና ስራዎቻቸው ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ሁኔታዎችን ታሪካዊ ዳራቸውን የሚተነትን ሲሆን በሸማ ስራ በተክኖሎጂው በአቅርቦት በልውውጡና በመሳሰሉት ጉዳዮች ያለውን ባህላዊና ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች በየጊዜው ላለው ለውጥ ያበረከቱትን አስተዋፅኦ በጥልቀት ያስረዳል::በጥናቱም ለውጥ ያለባቸው የተባሉ ጉዳዮች በሰፊው ተዳሰዋል:: ይህ ጥናት በባህላዊ አልባሳት ላይ ትኩረት ማድረጉ እና በተለይ ለውጡን ማየቱ ከሌሎች ጥናቶች ጋር ሊያመሳስለው ቢችልም ጥናቱ ሙሉ በሙሉ ከአልባሳቱ የአሰራር ሂደት ጋር ዝምድና ያለውና በተለይ በሸማ ስራና ሰሪዎች ላይ ባለው ለውጥ ላይ በማነጣጠር ታሪካዊ ይዘት ያለውና በዚህም ጥልቅ ምርምርን ያደረገ በመሆኑ የተለየ ያደርገዋል::

በሃገረሰባዊ አልባሳት ላይ ትኩረት በማድረግ ከተሰሩት ጥናቶች ውስጥ የዙፋን ፍቅሬ ጥናት አንዱ ሲሆን ጥናቱ ባህላዊ አልባሳቱ የሚሰራባቸውን ቁሶች ምንነት፣ አገልግሎት፣ መሳሪያዎች በአጠቃላይ አሰራሩን እንዲሁም ከስራውና ቁሶቹ ጋር ተያይዘው የሚባሉ ስነቃሎችን የሚዳስስ ነው:: ጥናቱ ከSchlereth ዘጠኝ የመተንተኛ ሞዴሎች ተግባራዊ የሆኑት የመዋቅራዊነት እና የአገልግሎት ሰጪነት ሞዴሎች ናቸው::

በሶስተኛ ምድብ የሚገኘው ጌጣጌጦችን ከሌሎች ቁሳዊ ባህል ክፍሎች ጋር በአንድ ላይ በማድረግ ያጠናው የዐቢዩ አስማማው "የአርጎባ ብሄረሰብ የቤት ውስጥ መገልገያና የማጌጫ ቁሶች በአማራ ክልል ደቡብ ወሎ ዞን አርጎባ ልዩ ወረዳ" ጥናት ነው:: ይህ ጥናት ሁለት ጉዳዮችን የያዘ ቢሆንም ለዚህ ፅሁፍ የሚያገለግለው ስለጌጣጌጦች የተነሳበት ክፍል በመሆኑ ይህ ብቻ ይቃኛል:: ይህ ጥናት እነዚህ ባህላዊ ቁሶችን

ከባህላዊ ገፅታቸው አንፃር የሚመረምር ሲሆን ቁሶቹ በማን ከምንና እንዴት እንደሚሰሩ መቼ ለምንና እንዴት አገልግሎት ላይ እንደሚውሉ በተጨማሪም ምን አይነት ቅርፅ ለምን ምክንያት እንደተንሀባረቀባቸው የሚያሳይ ነው::

አጥኚው ቁሶችን ለመተንተን በAmes የመመደቢያ መስፈርት የተጠቀመ ሲሆን ጌጦቹ እንደሚያርፉበት የሰውነት ክፍል(ቦታ) የአንገት የእጅ የወገብና የእግር በማለት ተመድበው በSchlereth የመተንተኛ ሞዴሎች ተንትነዋል:: ከነዚህ ሞዴሎች ውስጥም በተለይ ከአገልግሎት ሰጪነትና ከመዋቅራዊነት አንፃር ሁሉም ቁሶች የተተነተኑ ሲሆን ሌሎቹን ሞዴሎችም እንደ ቁሶቹ አይነት በተለያዩ ቦታዎች ተተግብረዋል::

በአጠቃላይ በእነዚህ ጥናቶች በተለያዩ ማህበረሰቦች የሚለበሱ ሃገረሰባዊ አልባሳት ከተለያዩ አቅጣጫዎች አንፃር የታዩ ሲሆን ሁሉም ጥናቶች የእጅ ባለሞያዎችን ህይወት የዳሰሱ እና አብዛኞቹ ደግሞ የአልባሳትን አገልግሎትና መዋቅር በስፋት የተተተነተኑ ናቸው:: ይህም በሃገራችን የሃገረሰባዊ አልባሳት ጥናት በተለይ ማህበረ ባህላዊውን ጉዳይ በማንሳት ረገድ ጥሩ ጅምር እንዳለ የሚያመለክት ነው:: እነዚህ ጥናቶች የPeriን ሳይጨምር በአብዛኛው ለአካላዊ ገለፃው ትኩረት የሰጡ ሲሆን ማህበረሰቡ በቁሶቹ አማካኝነት ቀርፆ ሊያስተላልፍ የፈለገውን መ ልእክት ለመተንተን የተወሰነ ሙከራ የተደረገ ቢሆንም በቂ ነው ለማለት ግን አያስደፍርም::

በተለይ በአሁኑ ወቅት አልባሳትን የተመለከቱ ቲወሪዎች ማህበረሰቡ በአልባሳቱ የሚያስተላልፈውን መልእክት የሚመረምሩ ናቸው:: ከነዚህ ውስጥም ትእምርታዊነት (Symbolism) ይጠቀሳል:: እንደ Bronner ገለፃ ማንኛውም ባህላዊ ቁስ አካላዊ ከሆነው ተግባሩ በተጨማሪ መንፈሳዊ በሆነ መንገድ የሚያስተላልፈው መልእክት ይኖረዋል:: በዚህም የማህበረሰቡን እምነት አመለካከት ብልሃት እውቀትና የመሳሰሉ ሃብቶቹን የሚይዙ ሲሆን ማህበረሰቡ እነዚህን እውነቶች የሚቀርፅባቸውና የሚያስተላልፍባቸው መንገዶች ናቸው:: በመሆኑም እነዚህን ሃብቶች የያዙትን ባህላዊ ቁሶች መተንተን ማህበረሰቡን ለማወቅ ተመራጭ ናቸው:: የትእምርታዊ አንፃር ግብም ይህን በአልባሳቱ ወይም በቁሶቹ የሚተላለፈውን ጥልቅ መልእክት መመርመርና መተንተን ነው:: በመሆኑም ሃገረሰባዊ አልባሳቱን ከሚደረጉበት ማህበረሰብ ባህል አንፃር ማየት ተገቢ ነው::

በአጠቃላይ ይህ ጥናት የሃገረሰባዊ አልባሳቱ ማህበራዊ ፋይዳ ከባህሉ አንፃር የሚተነትን በመሆኑ ከሌሎች በተወሰነ መልኩ ይለያል:: ይህን ለማድረግ ይረዳ ዘንድ የኮንሶን ማህበረ-ባህላዊ ገፅታን መመልከት አስፈላጊ ነው:: በመሆኑም በቀጣይነት ይዳሰሳል::

## 3. ኮንሶ፦ማህበረ_ባህላዊ ዳራ

ይህ ምዕራፍ የኮንሶ ብሄረሰብ አካባቢያዊ፣ ባህላዊና ማህበራዊ ገፅታዎችን ይገልፃል:: በዚህም መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ፣ የብሄረሰቡ አመጣጥ፣ ቋንቋ፣ ኢኮኖሚ፣ ባህላዊ አስተዳደርና የተለያዩ ባህላዊ እሴቶች ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ይዳሰሳሉ::

### 3.1 መልክዓ_ምድራዊ አቀማመጥ

ኮንሶ የሚለው ቃል የተወሰደው "ኮንሲታ" ከሚለው የኮንስኛ ቃል ሲሆን፣ ፍቺውም "ለም፣ ለምርት ተስማሚ መሬት" ማለት ነው::የኮንሶ ብሄረሰብ በዋናነት በደቡብ ክልል ከሚገኙና በዋና ወረዳነት ከተዋቀሩ ስምንት ልዩ ወረዳዎች አንዱ በሆነው የኮንሶ ልዩ ወረዳ የሚገኝ ሲሆን ከሌሎች ህዝቦች ጋርበመቀላቀል ደግሞ በኦሮምያ ክልል በተልተሌና በያቤሎ ወረዳዎች በደቡብ ክልል በባስኬቶ ልዩ ወረዳ በደቡብ ኦሞ ዞን በሰላማጎ ወረዳ በአርባምንጭ እና በጂንካ ከተሞች ይገኛል:: የኮንሶ ልዩ ወረዳ በሰሜን የደራሼ ልዩ ወረዳ በደቡብ የኦሮሚያ ክልል በምእራብ የቡርጂ እና የአማሮ ልዩ ወረዳዎች እንዲሁም በምስራቅ የደቡብ ኦሞ ዞን ያዋስኗታል::(የደ/ብ/ብ/ህዝቦች ፕሮፋይል፣ 151)

የኮንሶ ልዩ ወረዳ ዋና ከተማዋ ካራት ስትሆን ከአዲስ አበባ በ595 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች:: የልዩ ወረዳዋ የቆዳ ስፋት 2500 ካሬ ሜትር ሲሆን ከባህር ጠለል በላይ ከ1400-2000 ሜትር ከፍታ ላይ ትገኛለች:: አካባቢው በአብዛኛው ተራራማ ድንጋያማ ገደላማና ወጣገባ የበዛበት ነው ማለት ይቻላል::

ለኮንሶ ብሄረሰብ ዝናብ ከአለታዊ ጥቅሙ ባሻገር ከእምነታዊ ገፅታው ጋር የተሳሰረ ነው:: በባህላዊ እምነቱ መሰረት ዝናብ ማህበረሰቡ ከአምላኩ ወይም "ዋቃ" ጋር ያለውን ግንኙነት የሚገነዘብበት ሲሆን ይህም ማለት "ዋቃ" በማህበረሰቡ ውስጥ የዕርስ በእርስ ግጭትና አለመረዳዳት ካለ የሚቀጣበት አንደኛው መንገድ ዝናብ ማሳጣት ነው የሚል ነው::(Hallpike; 23) በመሆኑም የዝናብ መምጣትና አለመምጣት ከወቅታዊው ሁኔታ ባሻገር እምነታዊ ትርጓሜንም የሚይዝ ነው::

በኮንሶ አካባቢ ሁለት የተለመዱ የዝናብ ወቅቶች ያሉ ሲሆን እነዚህም ከየካቲት ግማሽ እስከ ሚያዚያ ያለው በኮንስኛ "ሮባሃጋያ" ተብሎ የሚጠራውና ሁለተኛው ወቅት ደግሞ ከነሃሴ እስከ ጥቅምት አጋማሽ ያለውን ይሸፍናል:: ይህ ወቅትም "ሮባ ካዳና" ተብሎ በአካባቢው ይታወቃል:: ከእነዚህ ሁለት ወቅቶች ውጪ ያሉት ወራት

ደረቅሆነው ያሳልፋሉ:: አካባቢው በአብዛኛው ሙቀታማና የዝናብ እጥረት የሚያጋጥመው ሲሆን አመታዊ የዝናብ መጠኑምከ650 ሚሊ ሊትር በታች መሆኑም መረጃዎች ይጠቁማሉ::

የኮንሶ ብሄረሰብ የራሱ የሆነ የቀን አቆጣጠር ያለው ሲሆን በሰላሳ ቀናት የተከፋፈሉ አስራ ሁለት ወራትን የያዘ ነው:: በዚህ የቀን አቆጣጠር መሰረት የመጀመሪያው ወር ጥር ሲሆን ታህሳስ ላይ ያልቃል::

ሠንጠረዥ 1: የኮንሶ ብሄረሰብ ወራት

| ተ.ቁ | ወራት በመገኛ ቋንቋ | ወራት በአማረኛ |
|---|---|---|
| 1 | ኦይባ | ጥር |
| 2 | ሳጋኖጋማ | የካቲት |
| 3 | ሙሬኖ | መጋቢት |
| 4 | ፓላሎ | ሚያዚያ |
| 5 | ሃሪ | ግንቦት |
| 6 | ቶላ | ሰኔ |
| 7 | ኦርሃልሳ | ሐምሌ |
| 8 | ሴሳይሳ | ነሃሴ |
| 9 | ፓርቱካታ | መስከረም |
| 10 | ኪሳ | ጥቅምት |
| 11 | ሁሊንዳላ | ህዳር |
| 12 | ፖሪንጋ | ታህሳስ |

ምንጭ: (Mamitu; 40)

የኮንሶ ብሄረሰብን አመጣጥ የተመለከቱ የተለያዩ መረጃዎች እንደሚያሳዩት የኮንሶ ህዝብ ቀደምት አባቶች ከተለያዩ ቦታዎች የመጡ ናቸው:: እነዚህ መረጃዎችም በአብዛኛው የሚስማሙበት ከምዕራብ እና ምስራቅ ኦሮምያ አካባቢ በተለይ ከሊበን ቦረና እና ገወዳ አካባቢዎች ተነስተው ለብዙ አመታት ያህል በኮንሶ ተራራማ አካባቢዎች ከሰፈሩ በኋላ ቀስበቀስ አሁን ወዳሉበት ቦታ መስፈራቸውን ይተነትናሉ::

የኮንሶ ብሄረሰብ የራሱ የሆነ የመግባቢያ ቋንቋ ሲኖረው "አፋን ኮንሶ" በመባል ይታወቃል:: ይህ ቋንቋ በኩሻዊ የቋንቋ ቤተሰብ ውስጥ የሚመደብ ነው:: የ"አፋን ኮንሶ" ቋንቋ በተለይ ከ ኦሮምኛ ቋንቋ ጋር የሚያመሳስለው ብዙ ነገሮች መኖሩን የሚጠቁሙት Hallpike እንደሚያስረዱት ይህ የሁለቱ ቋንቋዎች መመሳሰል የኮንሶ ብሄረሰብ ጥንተ አመጣጥ ከኦሮምያ አካባቢ ነው የሚለውን አባባል የሚያጠናክር ነው ይላሉ::

የኮንሶ ማህበረሰብ የገቢ ምንጩ በአብዛኛው በእርሻ ላይ የተመሰረተ ሲሆን የተለያዩ አይነት የእህል አይነቶችን በማምረት የሚታወቁ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም ጥጥ ጫት ቡናና መሰል ምርቶችንም ያለማሉ:: ከእርሻ በተጨማሪ የእጅ ባለሞያ ውጤቶችም ሌላው የማህበረሰቡ የገቢ ምንጭ ነው:: ከእነዚህ የእጅ ስራዎችም የተለያዩ የሽመና ውጤቶች የብረታ ብረት የሸክላ እንዲሁም የቆዳ ውጤቶች ተጠቃሽ ናቸው:: በአካባቢው የንግድ ስራም ሌላው የገቢ ምንጭ የሆነ የስራ አይነት ነው::

## 3.2 ባህላዊ አስተዳደር

የኮንሶ ብሄረሰብ ዘጠኝ ጎሳዎች ሲኖሩት እነዚህም ኢሻ፣ ኬርታ፣ ፓሳንታ፣ ሳውዳታ፣ መሃሌታ፣ ኤሌይታ፣ አርካማይታ፣ ቶክመሊታ እና ቲኬስየታ በመባል ይታወቃሉ:: እነዚህ ጎሳዎች እያንዳንዳቸው "ፓቆላ ቱማ" የሚል የማዕረግ መጠሪያ ያላቸው የጎሳ መሪዎች አሏቸው:: እነዚህ የጎሳ መሪዎች በማህበረሰቡ ዘንድ የአመራር እና የዳኝነት ስልጣን ያላቸው ሲሆን ወደ ስልጣን የሚመጡት ባላቸው መልካም ስነምግባር እና በችሎታቸው ተመርጠው ሲሆን ይህ ስልጣን በዘር ሃረግ የሚተላለፍና የእድሜ ልክ ነው::(አቶ ኮራ፣ ሚያዚያ 26፣ 2003 እና አቶ ከበደ፣ ሚያዚያ 23፣ 2003)

እያንዳንዱ የጎሳ መሪ በክንድ ላይ የሚደረግ የብር አምባር ወይም "ቱማ" እንዲሁም በትረ ስልጣን ይይዛል:: በድሮ ጊዜ የጎሳ መሪዎች የሚሆኑ ወንዶች ሲወለዱ በክንዳቸው ላይ የአምባር ምልክት ይዘው ይወለዱ ነበር:: ነገርግን በአንድ ወቅት

የነበሩት ህዝቦች መሪውን ጨምሮ በአምላክ ላይ በማመፃቸው ይህ ምልክት ሲጠፋ ቻለ ከዚህ በኂላ ለዚያ ምትክ ይሆን ዘንድ የብር አምባር ወይም "ቱማ" መደረግ መጀመሩን አቶን በመጥቀስ ማሚቱ ያስረዳሉ::

የኮንሶ የዘር ሃረግ የሚተላለፈው በአባት ዘር ሲሆን የአንድ ጎሳ አባላት የሆኑ ሰዎች እንደ እህትና ወንድም እራሳቸውን ይቆጥራሉ:: በዚህ የተነሳም የእርስ በርስ ጋብቻ የተከለከለና በመካከላቸው የሚፈጠር የግብረስጋ ግንኙነትም የተወገዘ ነው:: የኮንሶ ብሄረሰብ ዘጠኝ ጎሳዎች የራሳቸው የሆኑ አርማዎች ሲኖሯቸው ይህም አንዱ ጎሳ በተከታይ ከሚመጡ ጎሳዎች ጋር ዝምድና የሚፈጥሩ ናቸው::

በኮንሶ ብሄረሰብ የጎሳ መሪዎች እንደሃይማኖት መሪዎች የሚቆጠሩ ሲሆን ህዝቡን የመባረክና የመምከር እንዲሁም የተለያዩ ተግባራትን የማድረግ ስልጣን አላቸው:: አንድ የጎሳ መሪ የሚመገበውን ምግብና መጠጥ ማዘጋጀት የምትችለው ከጎሳው አባላት ውስጥ የምትገኝ ድንግል ሴት ብቻ ናት:: ከዚህ ውጭ በማንኛውም ሰው ሚስቱንም ጨምሮ የሚዘጋጅን ምግብና መጠጥ እንዲቀምስ አይፈቀድም::

ከፖቃላ ቱማው ስር የተለያየ የስልጣን ደረጃዎች ያሏቸው ሹማምንት ያሉ ሲሆን እነዚህም ፖቃላ ሙግላ ወይም "ቱራይታ" እና "ሳራ" የሚባል የማእረግ ስም ያላቸው ናቸው:: "ፖቃላ ሙግላ" የሚባሉት የ"ፖቆላ ቱማ"ው ምክትል ሆነውየሚሰሩ ሲሆን "ሳራ" የሚባሉት ደግሞ  የመሪውን ትዕዛዝ መልዕክት ወደ ታችኛው ማህበረሰብ በማድረስ የመልዕክተኛነት ተግባርን ያከናውናሉ:: ከእነዚህ የተለያየ የስልጣን ደረጃ ካላቸው ሹማምንት በተጨማሪ የማህበረሰቡን ችግሮች በቅርብ ሆነው የሚከታተሉና መፍትሄ የሚያፈላልጉ ሶስት ሸንጎዎች አሉ:: እነዚህም

1. "ቶላ"(የቤተሰብ ጉዳዮችን የሚመለከቱ)
2. "ካንታ"(የጎረቤት ጉዳዮችን የሚመለከቱ)
3. "ፓሌታ"(የአጠቃላዩን ማህበረሰብ ጉዳይ የሚመለከቱ)

ናቸው:: ከእነዚህ ሸንጎዎች በተጨማሪ መንደር ከመንደር በሚጋጭበት አጋጣሚ "መሳያ" ወይም"ዳውራ" የሚል የማዕረግ መጠሪያ ያላቸውና በማህበረሰቡ ዘንድ የሚታወቁ መንፈሳዊ አባቶች እርቅ የማውረድ ተግባር ያከናውናሉ:: እነዚህ አባቶች ግጭት በሚፈጠርበት ወቅት "ሃንሳ" በመባል የሚታወቀውን የዳማከሴ አበባ በእጃቸው በመያዝ በሁለቱ ተፋላሚ መንደሮች መካከል ይቆማሉ:: በዚህ ጊዜ ሁለቱም

ወገኖች የያዙት መሳሪያ በመጣል ለውይይቱ ይቀርባሉ:: ከውይይት በላይ የሆነ እንደሆነ መሃላ ወደሚፈፀምበት ሥርዓት በማምራት በመተማመን ይፈፅማሉ::(የደ/ብ/ብ/ህ/ፕሮፋይል፤ 154)

በመንደሮች መካከል የተፈጠረው ግጭት ከዚህ አልፎ የሰው ህይወት የጥፋበት ከሆነ ደም ማድረቅ አስፈላጊ ስለሚሆን "ዳውራዎች" የሚቹን የፈሰሰ ደም ለማንፃት በሚካሄድ ስነ ሥርዓት የአረጀች ላም በማረድ ደም የማድረቁን ስራ ያካሂዳሉ:: በዚህ ጊዜ ዳውራዎች ሳራዎች እና የሃገር ሽማግሌዎች ምግቡን ከቀመሱ በኂላ የሁለቱም ወገኖች የታረደችዋን ላም ስጋ ይመገባሉ:: ከምግቡ በኂላ የላሟ አጥንት ተሰብስቦ በጠበኞቹ መንደሮች ድንበር መካከል ላይ ይቀበራል:: ይህም የሚሆነው ግጭቱን እርግፍ አድርጎ መተውን ለማመልከት ነው:: ከዚህ በኂላ ዝናቡ ደሙን ሲያጥበው ምድሪቷ ትነፃለች ተብሎ ይታመናል::(Mamitu; 29)

## 3.3 ባህላዊ የጋብቻ ሥነስርዓት

በኮንሶ ብሄረሰብ የተለያዩ የጋብቻ አይነቶች ሲኖሩ ከእነዚህም በተለይ በተጋቢዎች ስምምነት የሚፈፀም ጋብቻ ወይም "ጃላላ" እና በቤተሰብ ስምምነት የሚፈፀም ጋብቻ በማህበረሰቡ ይዘወተራሉ:: ከእነዚህ በተጨማሪም የፖቃላቱማ ጋብቻ እና የውርስ ጋብቻ ወይም "ቁዳ ኢሬታ" በተወሰነ መልኩ በአካባቢው ይፈፀማሉ::

በቤተሰብ ስምምነት የሚፈፀመው የጋብቻ አይነት በተለይ በቀደምት ጊዜያት በስፋት ሲካሄድ የነበረና በአሁኑ ሰዓት ግን እየቀነሰ የመጣ የጋብቻ አይነት ነው:: በዚህ የጋብቻ አይነት ጀማሪዎቹ የሚሆኑት የወንዱ ቤተሰቦች ሲሆኑ የሚታየው የልጅቷ ውበት ሳይሆን የዘር ሃረጓ ነው:: ይህንም የልጅቷ የዘር ሃረግ ከተለያዩ ችግሮች የነፃ መሆኑን ያጣራሉ:: የዘር ሃረጓን ካጣሩ በኂላ ከሴቷ ቤተሰቦች ጋር በሽማግሌዎች አማካይነት በድብቅ ንግግር ይጀምራሉ:: የወንዱ ቤተሰብ የልጅቱን ቤተሰብ ፍቃድ ካረጋገጠ በኂላ ወንዱ(የሚያገባው) ከጓደኞቹ ጋርበመሆን ልጅቱ ከገበያ ስትመጣ ወይም ከሌላ ስራ ስትመለስ መንገድ ላይ በመጠበቅ በመጥለፍ ወደ ቤቱ ይወስዳታል:: ይህን የሚያደርገውም የሚጠበቅበትን ሙሉ ጥሎሽ ሳለመክፈል ሲሆን ልጅቷን ከወሰደ በኂላ የቅርብ ዘመዱ ቤት ይደብቃታል:: ከዚህ በኂላ ወደልጅቱ ቤት በግልፅ ሽማግሌዎች ይልካል::(Yilma; 48)

የ"ጃላላ"ን ጋብቻ ሙሉ በሙሉ የሚወስኑት ሁለቱ ተጋቢዎች ሲሆኑ ይህ ይሳካ ዘንድ ግን የቅርብ ጓደኞቻቸውና ዘመዶቻቸው ድርሻ ያስፈልጋል:: በዚህ የጋብቻ አይነት ልክ እንደ ላይኛው ሁሉ ጠለፋ ያለው ሲሆን ይህ የሚሆነው ግን በልጅቷም ፍላጎት ነው:: ቀድሞ ይዋደዱ የነበሩ ሁለቱ ፍቅረኞች መጋባት ሲፈልጉ ቀን ቆርጠው ይለያያሉ:: በተባለው ቀንና ሰዓትም ወንዱ ጓደኞቹን በመያዝ ቦታው ላይ ይጠብቃታል:: ልጅቱም በቀጠሮው ቦታ ስትመጣ ወንዱ ከነጓደኞቹ ይዘዋት ወደ ቤቱ ይወስዷታል:: በነጋታውም ወላጆቿ ልጃችን ጠፋች ብለው እንዳያስቡ ይነገራቸዋል:: ወላጆቿ ልጃቸው ፈቅዳ ማግባቷን ያረጋግጣሉ:: ከዚህ በኂላ ሽማግሌ ወደ ቤተሰቦቿ ተልኮ ፍቃዳቸው እስካልተረጋገጠ ድረስ በሁለቱ መካከል ምንም አይነት የግብረስጋ ግንኙነት አይፈፀምም:: የቤተሰቧ ስምምነት ከተረጋገጠ በኂላ ሙሽራው ጥሎሽ ይሰጣል::(የደ/ብ/ብ/ህ/ፕሮፋይል፤ 155)

የኮንሶ ብሄረሰብ የሰርግ ሥነስርዓት ተጋቢዎቹ ጥንዶች መጋባታቸውን ለወገኖቻቸውና ለጎረቤቶቻቸው ይፋ የሚያደርጉበት ነው:: በባህሉ መሰረት ሁለት አይነት የሰርግ ሥነስርዓት ሲኖር "ሳርጌታ ጉታ" ወይም ትልቅ ሰርግ እና ሳርጌታ ሻካ ወይም ትንሽ ሰርግ ይባላሉ:: በ"ሳርጌታ ጉታ" ሙሽራው ከሌሎች ጓደኞቹ ጋር በመሆን በፍቃድም ሆነ ያለፍቃድ ልጅቷን ጠልፎ ካስቀመጠበት የቅርብ ዘመዱ ወይም ጓደኛው ቤት ለስድስት ወይም ለሰባት ቀናት ፍየል በማረድ በመብላትና በመጠጣት ያሳልፋሉ:: ሙሽሮች ወደ ሙሽራው ቤት ከተመለሱ በኂላ ጓደኞቹ የተወሰነ ብር በማዋጣት መጠጥ ይገዛሉ:: ሙሽራዋ በበኩሏ ምግብ በማዘጋጀት የሚያግዟትን ዝምድና ያላቸውን ሴቶች ትጠራለች:: ከዚህ በኂላ ለአምስት ተከታታይ ቀናት ሙሽሮቹና አጃቢዎቹ "ጨቃ"(መጠጥ) በመጠጣት እና ዳማ በመመገብ በጭፈራ ያሳልፋሉ:: በአምስተኛው ቀን የሙሽራው ጓደኞችና የሙሽሪት አጃቢዎች ወደቤታቸው ይመለሳሉ:: በዚህ የሰርግ ሥነስርዓት ከሙሽሪት አጃቢዎች በስተቀር ማንም ወላጅ ወይም ዘመድ አይገኝም::(አቶ ኮራ ካራ፣ ሚያዚያ 26፣2003)

ሳርጌታ ሻካ(ትንሹ ሰርግ) ሳርጌታ ጉታ(ትልቁ ሰርግ) ከተፈፀመ በኂላ ባሉት ሶስት ተከታታይ ቀናት የሚደረግ ሲሆን እንደተለየ ሰርግ ወይም እንደ ሁለተኛ ሰርግ ተደርጎ አይወሰድም:: ይህ የሰርግ ሥነስርዓት ምግብና መጠጥ ተዘጋጅቶ ትልቁ ሰርግ በተደረገበት ቦታ ይፈፀማል:: የመጨረሻው ሰርግ ከተደረገ በኂላ ሙሽራዋ ከሶስት እስከ አራት ወራት ድረስ ከቤት አትወጣም:: በእነዚህ ጊዜያት ከወላጆቿ ጋር መገናኘት የማትችል ሲሆን በማንኛውን ማህበራዊ ሁነቶች ላይ አትሳተፍም:: ከሶስት

ወይም አራት ወራት በኂላ ከማር ጋር የተደባለቀ ጨቃ በማዘጋጀት ወላጆቿን ትጋብዛለች:: ከዚህ ስርዓት በኂላ በተመሳሳይ ወቅት ካገቡ ሙሽሮች ጋር በመሆን በመንደሩ ትዞራለች:: በዚህ ጊዜም ዘመዶቿን ቤተሰቦቿንና ጎረቤቶቿን ትጎበኛለች:: በዚህ ወቅት ሙሽራዋ የተዘጋጀ የጥቁር አውራ ፍየል ቆዳ የምታደርግ ሲሆን ድንግል ሆና ካገባች የክብር በትር በእጇ ትይዛለች::

የ"ፖቃላ ቱማ" ጋብቻ በይፋ የሚፈፀም ሳይሆን እጅግ ሚስጥራዊ በሆነ መንገድ የሚፈፀም ነው:: "ቂዳ ኢሬታ" የሚባለው የጋብቻ አይነት የውርስ ጋብቻ ሲሆን ታላቅ ወንድም ሲሞት ታናሹ የሚቹን ሚስት የሚያገባበት የጋብቻ አይነት ነው:: በማህበረሰቡ ባህል ታናሽ የታላቅን እንጂ ታላቅ የታናሽን መውረስ አይቻልም:: የዚህ አይነት ጋብቻ ዋና አላማ የሚቹ ንብረት በባእድ እጅ ገብቶ እንዳይባክንና ልጆቹም እንዳይበደሉ በማሰብ ነው::(የደ/ብ/ብ/ህ/ ፕሮፋይል፤ 156)

## 3.4 ባህላዊ የለቅሶ ሥነስርዓት

የኮንሶ ብሄረሰብ የለቅሶ ሥነስርዓት እንደሚቹ እድሜ ፆታና ማእረግ ይለያያል:: በባህሉ መሰረት ህፃናት ሲሞቱ ለሶስት ተከታታይ ቀናት ብቻ የሚለቀስ ሲሆን ከዚህ በላይ ማዘንና ማልቀስ አይፈቀድም:: በብሄረሰቡ በወጣትነት የእድሜ ክልል ላይ ያለ ሰው ሲሞት ሃዘኑና ለቅሶው መረር የሚልና ለዘጠኝ ተከታታይ ቀናት የሚቆይ ነው:: የቀብር ስርዓቱ የሚፈፀመው በሞተበት ዕለት ሲሆን ይህ የሚሆነውም ሌሎቹ የሚቹን አስክሬን በማየት እንዳይደነግጡና ለሌላው ሰውም ምክንያት እንዳይሆን በማሰብ ነው:: ሚቹ ሲቀበርም ይጠቀምባቸው የነበሩ ቁሳቁሶች አብረው ይቀበራሉ:: ይህም የሚሆነው የሚቹ የሙት መንፈስ ቤተሰቡን እንዳይረብሽ ነው:: ሴቶች በሚሞቱበት ጊዜ የሚታዘነው ለስድስት ተከታታይ ቀናት ነው::(አቶ ከበደ፣ ሚያዚያ 23፣ 2003 እና ወ/ሮ ሃጋየ፣ ሚያዚያ 27፣ 2003)

በማህበረሰቡ የልጅ ልጅ ያዩ ሰዎች ሲሞቱ ብዙ አይታዘንም እንዳውም በመብላትና በመጠጣት "ሻሌታ" በመባል የለቅሶ ዘፈን ይዘፍናሉ:: በዚህም የሚቹ መልካም ስነምግባር እየተነሳ ይወደስበታል:: በጭፈራው ወቅት የሚቹ ዘመዶች ገንዘብ በማዋጣት ለከዋኞቹ ይሸልማሉ:: በክዋኔው መሳተፍ የሚቹን በረከትና እድሜ ያስገኛል ተብሎ ስለሚታመን ከሚቹ የበኩር ልጅና ሚስት በ ስተቀር ሁሉም ይካፈላል:: ሚቹ የሚቀበሩት ሰውነታቸው በቅቤ ተቀብቶ ሲሆን በህይወት ዘመናቸው

ጀግና ከነበሩ "ዋካ" የሚባል ከእንጨት ተጠርቦ የሚዘጋጅ ምስል በመቃብራቸው ላይ ይቆማል:: ( የደ/ብ/ብ/ህ/ፕሮፋይል፣ 156)

በብሄረሰቡ የ"ፖቃላ ቱማ" ሞት ለህዝቡ ቶሎ አይነገርም:: ልክ እንደ ጋብቻቸው ሁሉ ሞታቸውም በሚስጥራዊ ሆኖ ይቆያል:: የጎሳ መሪው ከሞቱ በኋላ ለህዝቡ "ጉንፋን ይዟቸዋል" ይባላል:: በብሄረሰቡ የታወቁ የባህል ህክምና አዋቂዎች የሟቹን አስክሬን የሆድ እቃና አይን ያወጡትና በአይኑ ምትክ የሰጎን እንቁላል ስባሪ ያደርጉበታል:: በተለያዩ ባህላዊ መድሃኒቶችም አስክሬኑ እንዳይበላሽ በማድረግ ከቤት ውጭ ወንበር ላይ በማድረግ ሰው እንዲያየው ይደረጋል:: የሚመጡ ጠያቂዎች ወደ አስክሬኑ እንዳይቀርቡ "ጉንፋን ይዟቸዋል" ስለሚባሉ ቀርበው አያዩም:: የሟቹ የጎሳ መሪ ቀብር እስከ ዘጠኝ አመት የሚቆይ ሲሆን በተለያዩ ተፈጥሯዊ ችግሮች ግን የቀብሩ ስርዓት ቶሎ ሊፈፀም ይችላል:: ሟቹ በሚቀበሩበት እለትም የወራሹ የንግስና ስርዓት ይከናወናል::(የደ/ብ/ብ/ህ/ፕሮፋይል፣ 157)

## 3.5 የእጅ ባለሞያዎች ህይወት

በኮንሶ ብሄረሰብ የተለያዩ የእደጥበብ ውጤቶችን በማምረት የሚታወቁና ከሌላው የሃገራችን ክፍል በተሻለ ጠንካራ ማንነት ያላቸው በማህበረሰቡ አጠራር "ሃውዳ" በመባል ይታወቃሉ::(Watson & Lakew; 246) እነዚህ የማህበረሰብ ክፍሎች ከሌሎቹ ማለትም "ኤቴንታ" ከሚባሉት ቀደም ባሉት ጊዜያት በእጅጉ የተገለሉ የነበሩ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ግን ይህ መገለል በተወሰነ መንገድ ቀንሷል:: የኮንሶ ማህበረሰብ ለሁለት የመከፈሉን ጉዳይ የሚያስረዳ አፈታሪክ ያለ ሲሆን እንደተናጋሪው የአፈታሪኩ አይነትም በተወሰነ መልኩ የተለያየ ቢሆን ተመሳስሎው የጎላ ነው:: ኮንሶ ምድረበዳ በነበረችበት ወቅት የቅል ተክል በጣም ካደገ በኋላ ሁለት ወንድ ህፃናት ተወለዱ:: አንደኛው በእጁ ጤፍ ይዞ ሲወለድ ሌላኛው ደግሞ ሙቁካ(መወርወሪያ) ይዞ ተወለደ:: እነዚህ ህፃናት አደጉ ኮንሶንም ሞሏት:: ጤፍ ይዞ የተወለደው ገበሬ(ኤቴንታ ) ሲሆን መወርወሪያ ይዞ የተወለደው ደግሞ የእጅ ባለሞያ(ሃውዳ) ሆነ የሚል ነው::(Watson & Lakew; 248) ሃውዳዎች ልክ እንደ ኤቴንታዎች ሁሉ በዘጠኙም ጎሳዎች ውስጥ የሚገኙ ሲሆን እንደስራቸው አይነት ወደአምስት ልንከፍላቸው እንደምንችል Watson እና Lakew ያስረዳሉ:: እንዚህም ሱዓ ካላ(ስጋ አራጅ) ኦሃታ(ሸማ ሰሪ) ቱማ(ብረታ ብረት ሰሪ) ኮላታ ቱካ(ቆዳ ሰሪ) እና ኦግዳ(ሸክላ ሰሪ) ናቸው::

የዚህ ጥናት ትኩረት የሚዳስሰው የሸማ: ቆዳ እና ብረታብረት ስራዎችን በመሆኑ ምንምእንኳን በጥቅሉ የእጅ ሞያተኞችን ህይወት ቢዳስስም በዋናነት ግን የእነዚህ ባለሞያዎች ህይወት ያያል::የእጅ ባለሞያዎች ህይወት በተለይ ከ1897 እ.ኤ.አ በፊት በጣም የተገለሉና ምንም አይነት መሬት ያልነበራቸው እንዲሁም ከሌሎች ማለትም ኤቴንታ ከሚባሉት አምራች የማህበረሰቡ ክፍሎች ጋር መብላት መጠጣትና ማንኛውንም ማህበራዊ ግንኙነት ማድረግ የማይፈቀድላቸው እንደነበሩ Hallpike ያስረዳሉ:: ይህ የሆነበትን ምክንያትም ይህ ምሁር ከማህበረሰቡ አመለካከትና ባህል አንፃር ይተነትኑታል::

ኦሃታ ወይም ሸማ ሰሪዎች በማህበረሰቡ ዘንድ ሃውዳ ከሚባሉት አንደኞቹ ናቸው:: እነዚህ ባለሞያዎች በዋናነት ከጥጥና ከክር የሚሰሩ ምርቶችን የሚሰሩ ሲሆን በአሁኑ ወቅትም ታዋቂና ትርፋማ ስራ መሆኑን Watson እና Lakew ይገልፃሉ:: ምርታቸውም በተለያዩ አካባቢዎች ተፈላጊ ሲሆን ከእነዚህ በረና እና ደቡብ ኦሞ አካባቢዎች ተጠቃሽ ናቸው:: የነዚህ ባለሞያዎች የመገለል ሚስጥር ጥጥ በማህበረሰቡ ዘንድ ካለው ቦታ የመነጨ ነው ባይ ናቸው Hallpike:: ጥጥ በኮንሶ ብሄረሰብ እንደ ገደቢስ ይታይ የነበረ ተክል ነው:: የዚህ ምክንያትም ጥጥ የሚበቅልበት ወቅት ደረቅና ውሃ ወይም ዝናብ በሌለበት ጊዜ መሆኑ እንዲሁም ደግሞ ቀለሙ ነጭ መሆኑ ነጭ ቀለም ደግሞ በባህሉ መሰረት ከሞት ጋር የተያያዘና የማይወደድ እንዲሆን አድርጎታል:: በመሆኑም በማህበረሰቡ ዘንድ ይህን መስራት እንደሃጥያት ይቆጠር ነበር እንደውም በተቀደሱ ቦታዎች ይህን ይዞ መገኘት የተወገዘ ነው:: በዚህ ምክንያትም ይህን የተወገዘ ተክልን መስራታቸው እንደዋና መገለያ ምክንያት ሆኗል በማለት Hallpike ያስረዳሉ::

ኮላታ ቱካ(የቆዳ ሰሪዎች) ከሌሎቹ የእጅ ባለሞያዎች ይልቅ የኑሮ ደረጃቸው የወረደና በተለይ በአሁኑ ወቅት ካለው የገበያ መስፋፋት የተነሳ ከተለያዩ አቅጣጫዎች የተለያዩ ቁሶች መግባታቸው በእነዚህ ባለሞያዎች የሚሰሩ ቁሶችንተፈላጊነት በእጅጉ ቀንሶታል:: የእነዚህ ባለሞያዎች ህይወት ከቆዳ ጋር የተያያዘ ሲሆን ቆዳ ደግሞ ከሞት ጋር የሚያያዝ መሆኑና የኮንሶ ማህበረሰብ ደግሞ ሞትን አጥብቆ ስለሚጠላ እነዚህን ባለሞያዎች ሲያገል ችሏል::(Hallpike, 143) ቱማ(ብረታብረት ሰሪ) በአካባቢው እጅግ ተፈላጊ የሚባሉ መሳሪያዎችን የሚያመርቱ ሲሆን በተለይ ደግሞ በጎሳ መዎች የሚደረጉ ጌጣጌጦችን በመስራት ረገድ ከፍተኛ ድርሻ አላቸው::

ይህንንም ከተለያዩ ቦታዎች በሚያስመጧቸው ብረቶችና ሌሎች ጥሬ ቁሶች ይሰሯቸዋል::

በአሁኑ ወቅት የእጅ ባለሞያዎች መገለል እየቀነሰ የመጣ ሲሆን ከሃውዳዎች ውጭ ትርፋማነት ያላቸውን ስራዎች በተለይ የሽማ ስራን ኤቴንታዎችም በስራው ላይ በመሰማራት ላይ ይገኛሉ:: እነዚህ የእጅ ባለሞያዎች ይህን ሞያ የተማሩት ወይም የወረሱት በአብዛኛው ከቤተሰቦቻቸው ሲሆን በአሁኑ ወቅት ግን የተወሰኑት በማየት መሆኑንአቶ ኩሴ ይጠቁማሉ:: እነዚህ የእጅ ባለሞያዎች “ፋልደ” በመባል የሚታወቅ ማህበራዊ ተቋም አላቸው:: ስያሜውንም የኤቴንታንና የሃውዳን መነሻ ከሚተርከው አፈታሪክ ያገኘ ሲሆን ይህም የሃውዳዎች መጀመሪያ የሚባለው ሰው “ፋልደ” ይባል ስለነበረ ነው:: ይህ ተቋም በተለያዩ አካባቢዎች የግንኙነት መስመር ያለው ጠንካራ ተቋም ነው::(Watson & Lakew; 254)

በአጠቃላይ ይህ ምዕራፍ ከሃገረሰባዊ አልባሳት ጋር ዝምድና ያላቸው የኮንሶ ማህበረሰብ አካባቢያዊ እና ማህበረ-ባህላዊ ዳራ ተቃኝቶበታል:: አልባሳት እንደ አካባቢው የአየር ሁኔታ ወይም መልከዓ-ምድራዊ አቀማመጥ ይለያያሉ:: ከዚህ በተጨማሪም እንደ ማህበረሰቡ ባህላዊ እሴቶችም የአልባሳት ሁኔታ በእጅጉ ይለያያል:: በመሆኑም የእነዚህ ገፅታዎች መታየት በአልባሳት ላይ ትንተና ለመስጠት አስፈላጊነታቸው አያጠያይቅም::

# 4. የኮንሶ ሃገረሰባዊ አልባሳት:የቁሳዊ እና ጥበባዊ ገፅታዎች ትንተና

ይህ ምዕራፍ እንደማሳያነት የተወሰዱ የኮንሶ ሃገረሰባዊ አልባሳት ማለትም አልባሳት፣ ጌጣጌጦች እና የፀጉር አሰራር ቁሳዊ እና ጥበባዊ ገፅታ ትንታኔን ይይዛል::

## 4.1 አልባሳት

በዚህ ንዑስ ክፍል አልባሳትን ማለትም ከተለያዩ ቁሶች የሚሰሩና ማህበረሰቡ ሰውነቱን ለመሸፈን ወይም ለሌላ አላማ የሚጠቀምባቸውን ቁሶች ይተነተናሉ:: በኮንሶ ማህበረሰብ የሚገኙ ሃገረሰባዊ አልባሳት በአብዛኛው ማለት ይቻላል ከወገብ በታች የሚለበሱ ናቸው::የኮንሶ አየር ንብረት ሞቃት ነው:: በመሆኑም በስራ ወቅት ከላይ ለብሶ መስራት ስለማይመች በአብዛኛው ከወገብ በላይ ራቁት መሆን ይመረጣል::(አቶ ገልገሎ፣ ሚያዚያ 26፣ 2003፤ አቶ ኮራ፣ ሚያዚያ 26፣ 2003 እና አቶ ከበደ ሚያዚያ 23፣2003) ወይዘሮ ሃጋያ እንደሚገልፁት ከዚህ ምክንያት በተጨማሪ ሴቶች ከወገብ በላይ የማይለብሱበት የራሳቸው ምክንያት አላቸው:: ሴቶች ጡታቸው እያደገ ባለበት ወቅት ከሙቀት ጋር ተደምሮ ልብስ የሚነካው ከሆነ በጣም ያድጋል ተብሎ ይታመናል:: በዚህ ምክንያትም ከላይ ልብስ ማድረግ አይመረጥም:: በዚህ ንዑስ ክፍል የሴቶች የሆኑት ኡዋ፣ ፓሮታ እና ኮራ እንዲሁም በአሁኑ ወቅት የለባሾች ሁኔታ እየቀነሰ ቢመጣም የወንዶች የሆኑት ኮንፋ፣ ጨርፋ፣ ባራቴታ እና ጋቢ በተወሰነ መልኩ ይዳሰሳሉ::

### 4.1.1 ኡዋ

ኡዋ ቀሚስ ማለት ነው:: ይህ የልብስ አይነት ከወገብ በታች ያለውን የሴት ልጅ የሰውነት ክፍል የሚሸፍን ነው:: በአሁኑ ሰዓት ማህበረሰቡ የሚጠቀምበት ኡዋ ከጥጥ፣ ከክር፣ ከአቡጀዲ ወይም ከቦብሊን ጨርቆች የሚሰራ ሲሆን የበፊቱ ግን ከቆዳ የሚሰራ ነበር:: ከቆዳ የሚሰራው ኡዋ ሁለት ክፍሎች አሉት፦ ትሮንዴጋ እና ኡትሮይዳ ተብለውም ይጠራሉ። ትሮንዴጋ "ዙሪያ አልባሽ" ማለት ነው:: ይህ የኡዋ ክፍል ከኋላ በኩል ያለውን የሰውነት ክፍል ይሸፍናል። ትሮንዴጋ የሚሰራበት ቆዳ ተለፍቶና በቅቤ በደንብ ለስልሶ የሚዘጋጅ ነው። ኡትሮይዳ ማለት "አልባሽ" ሲሆን ከትሮንዴጋው ጋር በፊት በኩል የሚደረግ ነው። ትሮንዴጋ ሙሉ በሙሉ

ከወገብ በታች ማልበስ አይችልም:: በመሆኑም ከፊት በኩል የሚቀረውን ክፍተት ኡትሮይዳ ይሸፍነዋል:: ኡትሮይዳ አጠር የማለት ባህሪ ሲኖረው ትሮንዴጋ ደግሞ ረዘም ይላል። ይህም ሴቶች እርሻ ላይ ወይም ሌላ ቦታ ለስራ ሲያጎነበሱ የኋላ ሰውነታቸው እንዳይጋለጥ እና የፊቱ ደግሞ እንዳይበላሽ ለማድረግ ነው።

የኡዋ ለውጥ መታየት የጀመረበት በኡትሮይዳ የመስሪያ ቁስ መሆኑ ይነገራል:: ከቆዳ ይሰራ የነበረው ኡትሮይዳ እየቆየ ሲሄድ በጨርቅ ተተካ። ይህ ከጨርቅ መሆኑ የተለያዩ ጥቅሞችን ከመስጠት አንፃር ተመራጭ አድርጎታል:: ይህም የለበሿን ሰውነት ከመሸፈን ባለፈ ከቆዳ ይልቅ ምቾትን መስጠቱ እንዲሁም ደግሞ ለባሿ በእርሻ ስራ ላይ ምርት ሲሰበሰብ ደቃቅ ነገሮችን ለመያዣነት መጥቀሙ ነው። ይህን አስመልክተው አቶ ኮራ እንዲህ በማለት ያስረዳሉ::

"አብዛኛውን ጊዜ ከቆዳ ይሰራ ነበር ከዚያ ለውጥ እሱ ላይ ነው መምጣት የጀመረው:: ከዚያ ከታች ወይም ከበስተኋላ ቆዳ ከፊት ደግሞ ጨርቅ መሆን ጀመረ አገልግሎቱ ብዙ ነው:: እንግዲህ እንደቀበቶ እሱ ይታጠፍና የሚይዘው ነገር ይኖራል:: አገልግሎቱ አንድ ሴትዬዋን ለመሸፈን ሁለት እርሻ ላይ ስራ ሲሰሩ ምርት ሲሰበስቡ በጣም ደቃቅ ነገሮች ሲሰበስቡ በዚያው ላይ ያደርጋሉ"(አቶ ኮራ ካራ፣ ሚያዚያ 26፣ 2003)

እነዚህ የኡዋ ክፍሎች ከቆዳ ይሰሩ በነበሩበት ሰዓት ለባሾቹ በስራ ላይ ለብሰው ሲሰሩ ሙቀቱ በሚፈጥረው ላብ እንዳይበላሽ ለማድረግና ይህንም ለመከላከል ኦሜራ (ኮኮናይዳ) የሚባልና ከቆዳ የሚሰራ የልብስ አይነት ይጠቀማሉ። ይህ የልብስ አይነት ከቆዳዎች ሁሉ ጠንካራ ነው ከሚባልለት የበሬ አንገት ስር ቆዳ የሚዘጋጅ ሲሆን እንደ ውስጥ ልብስ ያገለግላል:: ይህም ኡዋውን ከተለያዩ አደጋዎች ይጠብቀዋል።

ኡዋ ከቆዳ ይሰራ ከነበረ በኋላ ከጥጥ ከዚያም በአሁኑ ሰዓት ከክር፣ ከአቡጀዲ እንዲሁም ከቦብሊን ጨርቆች እየተዘጋጀ በመምጣቱ የተለያየ አይነት እንዲሆን አድርጎታል። በእነዚህ የጨርቅ ዓይነቶች የሚሰራው ኡዋ ሰፍ እና ረዝም ያለ ነው:: ይህም ዙሪያውን ወጥ በሆነ መልኩ ተሰርቶ በማሰሪያ ይያያዛል:: እንደለባሿ ፍላጎትም አጠር ወይም ረዘም ተደርጎ ይለበሳል:: ከጥጥ፣ ከአቡጀዴና ከቦብሊን ጨርቆች የሚሰራው ኡዋ ከላይና ከታች ጫፉ ላይ ከክር በተሰራ እና የተለያዩ ህብረቀለማት ባለው ጨርቅ ጥለት ይሰራለታል። ኡዋው በሚለብስበት ወቅት ከላይ ያለው ጫፍ ወደ ታች ስለሚታጠፍ ተደራቢ ይፈጥራል። በማህበረሰቡ ዘንድ በአብዛኛው የሚለበሰው ከክር የሚሰራውና በደማቅ ቀለማት የተዋበው ኡዋ ነው:: ይህም አንድም

ደምቆ ለመታየት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በቀላሉ ለቆሻሻ የማይጋለጥ በመሆኑ ለስራ አመቺ ነው::



ምስል 1: ለኡዋ መስሪያነት የተዘጋጁ ከክር የተሰሩ ብትን ጨርቆች

4.1.2. ኮራ

ይህ የልብስ አይነት ከቆዳ የሚሰራ እና ከወገብ ላይ  የሚደረግ ነው:: ኮራ በአንድ በኩል ረዘም ስለሚል የሶስት መዓዘን አይነት ቅርፅ ይሰራል፤ ረዘም ያለው ክፍል በለባሿ ኂላ ይሆናል:: ይህም ሴቶች ከወለዱ በኂላ ከአራስ ቤት ሲወጡ የሚያደርጉት ነው፡፡ ወልዳ የምትወጣ እናት ኮራውን በወገቧ ላይ የምታደርገው ሲሆን  ወንድ የወለደች ከሆነ  ከኮራው ላይ በጥላሸት ወደጎን ይሰመርበታል፡፡ ሴት የወለደች አራስ ደግ ጥላሸቱ ወደታች የተሰመረ ይሆናል፡፡ ይህም አራሷ ከክፋ መንፈስ ለመጠበቅ የሚደረግ ነው፡፡ ምክንያቱም ከአራስ ቤት የምትወጣ ሴት አይን ይበዛባታል ስለሆነም ከክፉ ነገር ራሷን እንድትጠብቅ  ይጠቅማል ተብሎ ይታሰባል፡፡



ምስል 2: ኮራ

### 4.1.3 ፓሮታ

ፓሮታ ከጥቁር አውራ ፍየል ቆዳ የሚዘጋጅ የልብስ አይነት ነው:: ይህ የልብስ አይነት እንደካባ የሚመስል እና ከትከሻ ላይ የሚደረግ ነው፡፡ ይህን የምታደርግ በቅርቡ ሙሽራ የሆነች ሴት ስትሆን በእጇም ኡሌታ ሃምዳ ወይም ኡማ ሃምዳ የሚባል የክበር በትር ትይዛለች፡፡ ይህን መያዟ የድንግልናዋ ምልክት ይሆናት ዘንድ ነው፡፡ ከማግባቷ በፊት ተደፍራም ሆነ ተስማምታ ድንግልዋን ያጣች ሴት በሙሽርነት ጊዜዋ ይህን በትር አትይዝም፡፡ ይህን የክብር በትርም የጎሳ መሪው በመምጣት ቆዳ ላይ አድርጎ "የኔ ልጅ እራስሽን የምትተማመኚ ከሆነ ይህንን በትር ለክብርሽ አንሺው ከሌሎች ጋርም ይዘሽው ዙሪ" ይላታል፡፡ ድንግል የሆነች ሙሽራ በትሩን የምታነሳ ሲሆን ያልሆነች ሙሽራ ግን አትዳርፍም፡፡ ምክንያቱም በማህበረሰቡ እምነት መሰረት ድንግል ሳትሆን ይህን በትር የያዘች ሙሽራ በእርግዝናዋ ጊዜ ከነልጇ ትሞታለች የሚል እምነት በመኖሩ ነው፡፡

ጥቁር ቀለም በኮንሶ ብሄረሰብ በጣም ተፈላጊና ገድ ያለው እድለኛ ተደርጎ እንደሚወሰድ Hallpike በሰፊው ያብራራሉ:: ይህን የቀለም አይነትም በተለይ ዝናብን ካዘለ ጥቁር ዳመና ጋር ያያይዙታል:: ምክንያቱም ዝናብ ለኮንሶ ማህበረሰብ ትልቅ ትርጓሜ አለው፡፡ በመሆኑም ለብዙ ጉዳዮች ጥቁር ቀለም ወይም ጠቆር ያለ ቀለም ተፈላጊ ነው፡፡ ለምሳሌ አራስ ቤት የነበረች ሴት ከአራስ ቤቱ ስትወጣ ጡቷ ላይ ጥቁር ጥላሸትን በመቀባት ትዋባለች፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአብዛኛው ለመስዋዕት የሚቀርቡ እንስሳት ጠቆር ያሉ ናቸው፡፡ ፓሮታ የሚሰራው ደግሞ ከጥቁር አውራ

ፍየል ቆዳ ነው፡፡ ፍየል ለኮንሶ ብሄረሰብ ክብረበዓላት መስዋዕት በሚቀርብበት ጊዜ ለመስዋዕትነት ከሚፈቀዱና ተቀባይነት ካላቸው እንስሳት ውስጥ ይመደባል፡፡

በመሆኑም ፓሮታ ጥቁር መሆኑ ከዳመና ጋር ሲያያዝ ዳመና ደግሞ የዝናብን መምጣት አመላካች እንደመሆኑ መጠን የዚህ ልብስ ሙሽራ በሆነች ሴት መደረግም ልጅቱ ወደፊት ጥሩ ነገር እንደሚገጥማትና ጥሩ ፍሬን እንደምታፈራ የሚያመላክት ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ጥቁር ቆዳ የጥሩ ነገር መምጣትን አመላካች ሆኖ ይታያል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ጥቁር አውራ ፍየል ለመስዋዕትነት የተመረጠ የተቀዳሰ እንስሳ በመሆኑ የለባሿን ክብርና ዋጋ ለማሳየትም ያገለግላል፡፡ በመሆኑም ፓሮታ የምታደርገው ሙሽራ አንድም ግርማ ሞገስንና ክብርን የሚያላብሳት ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ወደፊት እድሏ የተሳካና ጥሩ ፍሬን የምታፈራ የተስተካከለ ህይወት ያላት እንደምትሆን የሚያመለክት ነው፡፡

### 4.1.4 ኮንፍ፣ ጨርፋ እና ባሪቴታ

ኮንፋ ከጥጥ ወይም ከክር የሚሰራ የልብስ አይነት ነው:: ይህ የወንዶች ልብስ በአብዛኛው በሰማያዊ ክር የሚሰራ እና ከጉልበት ከፍ የሚል የልብስ አይነት ነው:: አቶ ገልገሎ ሰንሳን እንደሚሉት "ወጣቶች የሚያደርጉት ኮንፍ መሃሉ ላይ ሻሎታ የሚባል ነገር አለ ከጥጥ የሚሰራ እሱ ይገባበታል"(ሚያዚያ 26፣2003):: ይህም እንደባትሌት የሚገባ ጨርቅ ነው፡፡



ምስል 3: ኮንፋ



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ጨርፍ የሚባለው የልብስ አይነት ከጥጥ የሚሰራ ነው:: ይህ ልብስ ብትን ጨርቅ ሆኖ ዙሪያ የሚያለብስ (የሚጠመጠም) እንደ ሽርጥ ያለ ነው። አቶ ኮራ ካራ ስለዚህ ልብስ ሲናገሩ "ይህ ልብስ በተለይ በዱሮ ጊዜ በወንዶች የሚደረግ በአሁኑ ሰዓት ልክ ሐመሮች እንደሚያገርጉት አይነት ነው ይህ በፊት ነበር የሚደረገው"(ሚያዚያ 26፣ 2003)። ባሬቴታ ከጥጥ (ክር) የሚሰራ ሽማግሌዎች ወይም የጎሳ መሪዎች ራሳቸው ላይ የሚያደርጉት ጨርቅ ነው። ይህም የሽማግሌዎች የክብር መገለጫ ሆኖ ይወሰዳል። ከነዚህ የወንድ አልባሳት በተጨማሪ ጋቢ በማህበረሰቡ ሽማግሌዎች ይለበሳል:: ጋቢ ከጥጥ እና ሃር ክር የሚሰራ ነው ። ይህን የልብስ አይነት ሽማግሎዎች በክብር ሰዓት ማለትም ለእርቅ ሲሄዱ ወይም በሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች ያደርጉታል።




ምስል 4: ጨርፋ

በአሁኑ ወቅት እነዚህ የሃገረሰባዊ አልባሳት ክፍሎች በእጅጉ ከተጠቃሚዎች እየወጡ መምጣታቸውን የተለያዩ መረጃዎች ይጠቁማሉ:: ለዚህም የተለያዩ ምክንያቶች ይጠቀሳሉ:: እነዚህም የዘመናዊ ትምህርት መስፋፋት፣ የንግድ እንቅስቃሴው ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መምጣት፣ የክርስትና እምነት(በተለይ የፕሮቴስታንት እምነት) መስፋፋት እና በአጠቃላይ የዘመናዊነት ፅንሰ ሃሳብ መስፋፋት ናቸው::የዘመናዊ ትምህርት መስፋፋት በአካባቢው ልዩ ልዩ መረጃዎች እንዲገቡ እና የተማሪዎች ወደሌሎች አካባቢዎች መሄድ ደግሞ የተለያዩ የኑሮ ዘይቤዎችን ቀስመው እንዲመጡ አድርጓል:: አቶ ኮራ እንደሚሉት "በተለይ በ1957 አካባቢ ማህበረሰቡ ቆዳ መልበሱን እና ጨሌ ማድረጉን በግዳጅ እንዲቀር የመደረግ ሁኔታ ነበረ::"

በኮንሶ የንግድ እንቅስቃሴ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ይገኛል:: የንግድ እንቅስቃሴው እያደገ መምጣት አንድም ከሌሎች አካባቢዎች ጋር ግንኙነት እንዲኖር ያደረገ ሲሆን በተጨማሪም ለውጭ አገር ቁሳቁሶች መግባት በር ከፍቷል:: በዚህ ምክንያትም የተለያዩ ልባሽ ጨርቆች ወደ አካባቢው በሰፊው መግባት ችለዋል:: ከሃገረሰባዊ አልባሳቱ ይልቅ የእነዚህ ልብሶች እንደልብ መገኘት እና ከዋጋ አንፃርም እርካሽ መሆን ተፈላጊ እንዲሆኑ አድርጓል:: የክርስትና እምነት በአካባቢው መስፋፋት ሌላው የለውጥ ምክንያት ነው:: ከዚህ ጋር በተያያዘ ማህበረሰቡ የሚጠቀምባቸውን አልባሳት በተለይ ጌጦች እንደ እምነታዊ ቁሶች በመወሰዳቸው ከባዕድ አምልኮ ጋር ተወስደዋል::(Shako; 179) በዚህ ምክንያትም የተወሰነው የማህበረሰብ ክፍል እነዚህን ጌጦች መጠቀም አቁሟል::

በኮንሶ ከሚገኙ የተለያዩ የገበያ ቦታዎች መታዘብ እንደሚቻለው የገበያውን ግማሽ ያህል ክፍል የሚሸፍነው የልባሽ ልብሶች ገበያ ነው:: እነዚህ ልባሽ ልብሶች ከሃገረሰባዊ አልባሳቱ ይልቅ በቀላሉ ተማርጠው የሚገኙ መሆናቸው በገንዘብ ረገድም እርካሽ መሆናቸው ከሌሎች ምክንያቶች ጋር ተደማምረው የወንዶችን ሃገረሰባዊ አልባሳት ተፈላጊነት በእጅጉ ቀንሰውት ይታያሉ:: በመሆኑም ማህበረሰቡ በብዛት(በተለይ ወጣቱ) በአካባቢው ከሚታወቀው ቁምጣ ይልቅ ሙሉ ሱሪ ማድረግን ይመርጣል::

## 4.2 ጌጣጌጦች

በኮንሶ ብሄረሰብ የተለያዩ አይነት ጌጦች (በተለይ የሴቶች) አሉ:: እነዚህ ጌጦች እንደየአገልግሎታቸው የተለያዩ ሲሆኑ በዚህ ንዑስ ክፍል የሚተነተኑት ጌጣጌጦችም ትዕምርታዊ ፋይዳቸው የጎሉት ብቻ ነው:: እነዚህ ጌጦች እንደሚደርጉበት የሰውነት ክፍል የተመደቡ ሲሆን እንደማሳያነት የተመረጡትን ጌጣጌጦች ብቻ በመውሰድ ይተነተናሉ::

### 4.2.1 የራስ ጌጦች

በኮንሶ ባህል ራስ ላይ የሚደረጉ የተለያዩ ጌጦች ያሉ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ ፓላ ተጠቃሽ ነው:: ቃርቃሮታ ምንም እንኳን በጆሮና በፀጉር መካከል ቢደርግም ለዚህ ትንተና እንዲመች በማሰብ በዚህ ምድብ ውስጥ ይተነተናል::

ፓላ

ይህ ጌጥ ከሰጎን ላባ የሚዘጋጅና ወንዶች በራሳቸው ላይ የሚደርጉት ነው። የላባው የቁጥር ብዛት (አንድ ወይም ሁለት) መሆን እንደአድራጊው ጀግንነት ይወሰናል። አድራጊው ገዳይ ከሆነ ድርቡን ሲያደርግ ሌሎች ማለትም በማህበረሰቡ ዘንድ ገዳይ የሚያስብሉ እንስሳትን ያልገደሉ ነጠላውን ያደርጋሉ። በኮንሶ ማህበረሰብ ገዳይ ለመባል የሚያበቁ እንስሳት አንበሳ፣ ጎሽ እና ዝሆን ናቸው። እነዚህ እንስሳት በአሁኑ ሰዓት በአካባቢው ባለመኖራቸው ገዳይ ለመሆን የወይጦ በረሃን አቋርጦ ለብዙ ሰዓት መጓዝ ይጠበቅባቸዋል። ይህን ተቋቁሞና አልፎ ግድያውን ጥሎ ለተመለሰ ጀግና በአካባቢው የሚደረግለት ራሱን የቻለ ዝግጅት የሚኖረው ሲሆን ለመለያው ይሆን ዘንድ ድርብ የሰጎን ላባ ወይም “ፓላ” በማድረግ ጀግንነቱን ለህዝብ ያውጅበታል። ገዳይ ለመሆን በመንገድ ላይ ያሉ ለጊዜው ግን ያልገደሉ ወንዶች ደግሞ ነጠላውን ያደርጋሉ። ይህም ወደፊት እኔም ገዳይ በመሆን ጀግንነቴን ለማሳየት በዝግጅት ላይ ነኝ የሚለውን መልዕክት የሚያስተላልፍ ነው። በመሆኑም በኮንሶ ማህበረሰብ ድርብ ፓላ ያደረገ ወንድ ገዳይ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን ነጠላውን ያደረ ደግሞ ገና ያልገደለ ወደፊት ግን ገዳይ የሚሆን መሆኑን የሚያመላክት ነው።



ምስል 5: ፓላ

*ቃርቃሮታ*


ቃርቃሮታ ከእንጨት ይሰራል:: ይህ ጌጥ ቀጠን ያለ እና ሴቶች በፀጉርና በጆሮ መሃል በመሰካት ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚጠቀሙበት ነው፡፡ ይህም ሴቶቹ በስራ ወቅት በሚያልባቸው ሰዓት ላባቸውን የሚጠርጉበት ከመሆኑም በተጨማሪ በስራ ጊዜ ፀጉራቸውን ቢያሳክካቸው ይህን ቁስ ይጠቀማሉ፡፡ ቃርቃሮታ ከዚህ አገልግሎቱ በተጨማሪ በጆሮና በፀጉር መካከል ሲደረግ ውበትን ይፈጥራል፡፡ ለዚህ አይነት አግልግሎቱ በተለይ "ኮሾታ" በመባል የሚታወቀው ከብረት የሚሰራው የቃርቃሮታ አይነት ተመራጭ ነው፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያትም ከብረት የሚሰራ በመሆኑ በቀላሉ ከሩቅ የመታየትና ፀሃይ ሲነካውም የመብረቅረቅ ባህሪ ስላለው ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ጌጥ ከሚሰጠው አገልግሎት በተጨማሪ ለውበት አገልግሎት ይውላል፡፡

4.2.2 የግንባር ጌጦች

በኮንሶ ባህል መሰረት እንደመደረጊያ አጋጣሚው ግንባር ላይ የሚደረጉ የተለያዩ ጌጦች ይገኛሉ:: ከነዚህ ውስጥም *ያጋታታሚ*፣ ስራ ወይም ሚኛ፣ ሻላና ኻለሻ ተጠቃሾች ናቸው፡፡ በመሆኑም በዚህ ንዑስ ክፍል የእነዚህ ጌጦች አካላዊ ገፅታንና ትዕምርታዊ ገፅታ ይተነተናል::

*ያጋታቲማ*

ይህ የጌጥ አይነት ከቀይ ዶቃ ወይም ጨሌ የሚሰራ ነው:: እነዚህ ቀይ ዶቃዎች በአንድ ወጥ በሆነ ጠንካራ ክር ተያይዘው የሚፈጥሩትና ነጠላውን የሚደረግ የጌጥ አይነት ነው፡፡ ይህ ጌጥ የሚደረገው ባሏ በሞተባት ሴት ነው፡፡ ቀይ ቀለም Hallpike እንደሚገልፁት ከደም ጋር የሚያያዝ ሲሆን እንደ አጋጣሚው ከእንስሳት ስጋ ጋር ወይም ደግሞ ከሰው ደም ጋር ተያያዥነት ይኖራል፡፡ ቀይ ቀለም ከስጋ ጋር ሲያያዝ እንደ ጥሩ ተድርጎ የሚወሰድ ቢሆንም አንዳንዴ ግን ከሰው ደም ጋር በሚያያዝበት ጊዜ የመጥፎ አጋጣሚ ወይም የወንድ ልጅ ሞት ምልክት ሊሆን ይችላል፡፡(Hallpike; 152) በመሆኑም በዚህ መሰረት ባሏ የሞተባት ሴት ይህን ማድረጓ የቤቷ ምሰሶ የነበረው ባሏ በሞት መነጠቁንና መሞቱን ከመግለፅ አንፃር ቀይ ቀለም መሆኑ በራሱ ትልቅ አስተዋፅኦ አለው፡፡




ምስል 6: ያጋታቲማ

## ስራ ወይም ሚኛ

ስራ ወይም ሚኛ ከእንሰት የሚሰራና ፀጉር ስር የሚታሰር የግንባር ጌጥ ነው:: ይህንም አግብተው የወለዱ ሴቶች ወልደው ከአራስ ቤት ሲወጡ የሚያደርጉት የጌጥ አይነት ነው። ይህን ጌጥ ማድረግ የሴትየዋን እናት መሆን ከማብሰሩም ባሻገር ውበትን ለመፍጠር የሚያገለግል ነው። አድራጊዋ ወልዳ ስትወጣ አምሮባት እንደወጣች የሚያመለክት ተደርጎ ይወሰዳል።

## ሻላ

ይህ የጌጥ አይነት ከበሬ ቆዳ ይሰራል::ይህ ጌጥ ግንባር ላይ ይደረጋል:: በአሁኑ ሰዓት ይህ የጌጥ አይነት ከቆዳ ሳይሆን ከጥጥ ይሰራል። ከቆዳ የሚሰራው ሻላ ቀጠን ተብለው በሚሰሩ ሶስት ድርቦች የሚዘጋጅ ነው:: የሻላ መደረግ ብቻ ሳይሆን አለመደረግም ትልቅ መልዕክትን ያስተላልፋል። ይህ የጌጥ አይነት የማይደረገው ሀዘን ሲያጋጥም ብቻ ነው። በመሆኑም ይህን ያላደረገ ሰው ሃዘንተኛ እንደሆነ በተመልካቹ ይታወቃል:: በማህበረሰቡ ዘንድ መጥፎ የሆነን ሰው ለመርገም “ለአንተ ሻላ ይነሳልህ” ይባላል “ ስምህን ቄስ ይጥራው” እንደማለት ነው። በመሆኑም የሻላ መደረግ ከውበቱ ባሻገር ከችግር ወይም ከሀዘን ጋር የተያያዘ ችግር አለማጋጠሙንም የሚያሳይ ተደርጎ ይወሰዳል።



ምስል 7: ሻላ

ሃላሻ

ሃለሻ የጎሳ መሪዎች በክብረ በዓላት ወቅት ግንባራቸው ላይ የሚያደርጉት የጌጥ አይነት ሲሆን ሁለት ክፍሎች አሉት:: አንደኛው ክፍል ቀጥ ያለ ሆኖ ጫፉ ላይ ጉብታዎች ያሉት እና ከብረት የሚሰራ ነው:: ይህ ክፍል መሃሉ ክፍት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በአካባቢው ኮይታ ተብሎ ከሚታወቅ ሼል የሚዘጋጅ ነው:: እነዚህን ሁለት ክፍሎች ለማያያዝ ቆዳ ወይም ጨርቅ አገልግሎት ላይ ይውላል:: ይህም ቆዳ ወይም ጨርቅ በሃላሻው የመጀመሪያ ክፍል ባለው ክፍተት በሚዘጋጀው ማሰሪያ በኩል እና በሁለተኛው ክፍል መሃል ባለው ቀዳዳ በማለፍ ግንባር ላይ ለመደረግ እንዲመች ሆኖ ይሰራል:: ሃላሽ ማለት "ክራንቻ" ማለት ነው፡፡

የሃላሻን ትእምርታዊ ትርጓሜ አስመልክተው Hallpike የተለያዩ ጉዳዮችን ያነሳሉ:: እኚህ ምሁር በተለይ የሃላሻን ቅርፅ በተለይ ከወንድነት ጋር በማያያዝ ሰፊ ማብራርያ ስጥተዋል፡፡ የሃላሻን ቅርፅ ቀጥ ካለ የወንድ ልጅ የመራቢያ አካል ጋር ያመሳስሉታል:: ይህንም ለወንድነት ዋና መለያ የሆነውን አካል ከባለቤቱ ወስዶ ማድረግ የጀግንነት ምልክት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ለዚህም ምክንያቱን ሲያስረዱ በጥንት ጊዜ ኮንሶዎች ጦርነት በሚገጥማቸው ጊዜ ጀግንነታቸውን ለማስመስከር የጠላቶቻቸውን መራቢያ አካል ይሰልቡ የነበረ ሲሆን የሰለቡትንም የመራብያ አካል በቀኝ እጃቸው ክንድ ላይ በማድረግ ለህዝቡ ያሳዩ ነበር፡፡ ይህም የጀግንነታቸውና

የጥንካሬያቸው መለያ ተደርጎ ይወስድ ነበር:: በመሆኑም የዚህ ጌጥ መደረግ ጀግንነትንና ከሁሉ የበላይ መሆንን ያሳያል::

ሃላሻ ከዚህ ትርጓሜው በተጨማሪ ለክብረ በዓላት ጊዜ ሲደረግ መዳረጉ የክፉ መንፈስን ሃይል የማጥፋት ሚናውን የሚያሳይ ነው።።ይህም በተለይ የሃላሻው ሁለተኛ ክፍል ካለው ቀለም አንፃር ነው:: ይህ ክፍል ነጭ መሆኑ የነጭ ቀለም ክፉ መንፈስን ከማባረር አንፃር ያለውን ቁርኝት ጋር የሚያያዝ በመሆኑ በክብረ በዓላት ላይ መሪው ማድረጋቸው ይህን ተግባር ለማስፈፀም የሚያገለግል ነው:: (Hallpike; 150 )



ምስል 8: ሃላሻ

4.2.3 የአንገት ጌጦች

በኮንሶ ማህበረሰብ ዘንድ የሚደረጉ የአንገት ጌጦች ሙሉ በሙሉ ማለት ይቻላል ከዶቃ (ጨሌ ነገሮች) የሚሰሩ ሲሆን እንደየዶቃ አይነቶች የተለያዩ ዋጋ ይሰጣቸዋል:: እነዚህ የአንገት ጌጦች በአብዛኛው ዶቃዎቹ ከተገኙ በኋላ በቤት ውስጥ በሽቦ ወይም በክር መሰል ነገሮች በማያያዝ የሚሰሩ ናቸው።። የኮንሶ የአንገት ጌጦች ብዙዎቹ ከእናት ወደ ልጅ ተላልፈው ወይም በስጦታ መልክ የተገኙ ሲሆኑ ብዙዎቹም ከዘር ወደ ዘር እየተላለፉ የመጡ እንደሆኑ ቢርጊታ እና ዲኖታ ያስረዳሉ።። (369).

ጨሚራ እና ጭርዋና

ጨሚራ በመባል የሚታወቀው የአንገት ጌጥ በአብዛኛው በውሃ ሰማያዊ ዶቃዎች የሚሰራ ሲሆን የተወሰኑ ቡናማ ዶቃዎችና ሌሎች አይነት ዶቃዎች ይገቡታል።ውሃ ሰማያዊ ዶቃ ውድ ከሚባሉና ትልቅ ቦታ ከሚሰጣቸው የዶቃ አይነቶች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ (Birrgitta & Dinote, 377) በመሆኑም ይህ የአንገት ጌጥ ውድ ከሚባሉት ውስጥ ይመደባል፡፡ ይህን የአንገት ጌጥ የሚያደርጉት እርጉዝ የሆኑ ሴቶች ሲሆኑ እንደ ክብር የሚቆጠር ነው፡፡ ጨሚራ የሌላት ሴት ስታረግዝ የመግዛት አቅም እንኳን ባይኖራት ካላቸው ሰዎች ተውሳ ታደርጋለች። ምክንያቱም ይህን ማድረግ ክብር በመሆኑ ነው፡፡

ጭርዋና በኮንሶ ማህበረሰብ ካሉ የአንገት ጌጥ ውስጥ በጣም ውድ ከሚባሉት የሚመደብ ነው፡፡ ይህ ጌጥ ከውሃ ሰማያዊ ዶቃዎችና ዥጉርጉር ከሆኑ ዶቃዎች የሚዘጋጅ ነው፡፡ ልክ እንደሌሎች የአንገት ጌጦች ሁሉ የዚህ የአንገት ጌጥ ዶቃዎችም በሽቦ ወይም ሽቦ መሰል ነገር በማያያዝ የሚሰራ ሲሆን ሶስት ድርብ ተደርጎ ይደረጋል፡፡ ይህን የአንገት ጌጥ የሚያደርጉት የጎሳ መሪ ሚስቶች ወይም ደግሞ ባለፀጋ የሆኑ ሴቶች ብቻ ናቸው፡፡ በመሆኑም ይህ ጌጥ ውበትን ከማጎናፀፉ በተጨማሪ ማህበራዊ ደረጃን አመልካችነቱ የጎላ ነው፡፡



ምስል 9: ጭርዋና

ኢላዋ: ይህ የአንገት ጌጥ ከተለያዩ ዶቃዎች የሚሰራ እና ነጠላውን የሚደረግ ነው:: ይህ ጌጥ እርጅናዋ ለደረሰና መንቀሳቀስ ብዙ ለማትችል እናት የሚሰጥ ሲሆን ይህም የማትንቀሳቀስ መሆኗንና ከዚህ በኋላ ያለው ስራዋ ልጅ ማቀፍ ብቻ መሆኑን የሚያመለክት ነው::

4.2.4 የእጅ ጌጦች

ቱማ

ቱማ የሚባለው የእጅ ጌጥ ከብር የሚሰራ ነው:: ይህ ጌጥ ክንድ ላይ የሚደረግ ሲሆን የጎሳ መሪዎች ብቻ የሚደርጉት የጌጥ አይነት ነው። Shako Otto እንደሚገልፁት ይህ የጌጥ አይነት ለምን መደረግ እንደተጀመረ የሚያስረዳ የራሱ አፈ-ታሪክ አለው። በድሮ ጊዜ የጎሳ መሪ የሚሆኑ ሰዎች ሲወለዱ በክንዳቸው ላይ ምልክትን ይዘው የነበረ ሲሆን ገና ከመወለዳቸው መሪ መሆናቸው በግልፅ ይታወቅ ነበር። በአንድ ዘመን የተነሳው የጎሳ መሪና ህዝቡ በአምላካቸው ላይ የማይገባ ስራ በመስራታቸውና በማመፃቸው ግን ይህ ምልክት ጠፍቷል። ከዚያ በኋላ ይህን የተፈጥሮ ምልክት ይተካ ዘንድ የብር ጌጥ ማድረግ ተጀመረ። ይህ ጌጥ የጎሳ መሪው ስያሜም ሆኖ ሲያገለግል ይታያል፦ "ፖቃላ ቱማ" በሚባልበት ጊዜ።

ሙልጋ ወይም ሙግላ፦ ልክ እንደ ቱማ ሁሉ ይህን የጌጥ አይነትም በክንድ ላይ የሚደረግ ሲሆን ከነሃስ የሚሰራ ነው። ይህን ጌጥ ማድረግ የሚችሉት ከጎሳ መሪው (ፖቃላ ቱማው) ዝቅ ያለ ደረጃ ያላቸው ሲሆኑ "ፖቃላ ሙልጋ" ተብለው ይጠራሉ።

4.2.5 የእግር ጌጥ

ሄሮዳ

ይህ የጌጥ አይነት እግር ላይ የሚደረግ ሲሆን ከሰጎን እንቁላል እና ከሰማያዊ ዶቃዎች የሚሰራና እነዚህም በጠንካራ ክር ተያይዘው የሚፈጥሩት ነው። ሄሮዳ ምንም እንኳን ስሙ አንድ ቢሆንም በሚኖሩት የዶቃዎች ብዛትና ነጠላና ድርብ መሆን የተለያዩ ናቸው:: ይህ የሚወሰነው እንደ አድራጊዋ የልጆች አይነትና ፆታ ነው:: የልጅ ልጅ ያየች እናት የምታደርገው ነጠላውን(አንዱን) ብቻ ነው:: ገና የልጅ ልጅ ያላየች ከሆነች ግን ድርቡን ታደርጋለች:: ከዚህ በተጨማሪም እናቶች እንደልጆቻቸው ፆታ የተለያየ አይነት ሄሮዳ ያደርጋሉ።

በባህሉ መሰረት ወንድ ልጆች ያሏት አንድ የብሄረሰቡ አባል ድርቡን ሄሮዳ የምታደርግ ሲሆን በሄሮዳው ውስጥ የሚገኙት የሰማያዊው ዶቃዎቹ ብዛት አስራ ሁለት ይሆናል። ሴት ልጆች ሲኖሯት ደግሞ እንደወንዶቹ ሁሉ ድርቡን የምታደርግ ሲሆን የዶቃዎቹ ብዛት ግን ይለያያል:: ለወንዶች አስራ ሁለት የነበሩት ዶቃዎች ለሴት ልጆች ወደ አራት ይወርዳል:: እነዚህ ስማያዊ ዶቃዎች በአካባቢው "ፑሌዳ" ተብለው የሚጠሩ ሲሆን ውድ ከሚባሉ የዶቃ አይነቶች ውስጥ ይመደባሉ፡ ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው በብሄረሰቡ ለሴት ልጅና ለወንድ ልጅ የሚሰጠውን ቦታ በጌጦቹም እንደሚገለፅ ነው። ከዚህ በተጨማሪ አንድ እናት ልጆቿ ወንዶችም ሴቶችም ከሆኑ ሁለቱንም አይነት ሄሮዳ ደርባ ታደርጋለች::



ምስል 10: ወንድ ልጅ ብቻ ያላት እናት የምታደርገው ሄሮዳ

ሄሮዳው የሚሰራባቸውና ከሰጎን እንቁላል የሚሰሩት ጠፍጠፍ ያሉ ክብ ነገሮች ነጮች ናቸው። ነጭ በብሄረሰቡ የሞት ወይም የመጥፎ ነገር ተምሳሌት ሲሆን ክፉ መንፈስን ለማባረር ወይም ለመከላከልም እንደሚያገለግል Hallpike ያስረዳሉ:: ሄሮዳ "ፑሌዳ" ተብለው ከሚጠሩት ሰማያዊ ዶቃዎች በስተቀር ሙሉበሙሉ ነጭ ነው:: እነዚህ ውድ የሆኑት ዶቃዎች የልጆች ተምሳሌቶች ሆነው የሚመጡ ሲሆን ሌሎቹ በእነዚህ ዙሪያ ያሉት እና ነጭ ቀለም ያላቸው ደግሞ እነዚህን ከተለያዩ ችግሮች የመከላከል ሚና ያላቸው አካላት ሆነው ይመጣሉ። ነጭ ቀለም መንፈስን ለመከላከል የሚያግዝ ነው። በመሆኑም እናት ይህን ስታደርግ ልጆቿ ከክፉ መንፈስ፣ ከአጋንንትና ከመሳሰሉት መንፈሳዊ ጠላቶች ልጆቿን እንዲታደግላት እያደረገች

መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። በመሆኑም ሄሮዳ ከጌጥነቱ ባሻገር መንፈሳዊ የሆኑ ጠንቆችን ለማባረርና ለመከላከል የሚያግዝ ሆኖ ይመጣል። ምክንያቱም ነጭ ከሞት ጋር የተያያዘ ከመሆኑ በተጨማሪ ክፉ መንፈስን ከማባረር ጋር ተያይዞ የሚመጣ እና የሚያገለግል የቀለም አይነት ነው።

## 4.3 የፀጉር አሰራር

የፀጉር አሰራር እንደየባህሉ የተለያዩ መልዕክቶችን ሊያስተላልፉ ከሚችሉና ከባህል ጋር በእጅጉ ቁርኝት ካላቸው በሃገረሰባዊ አልባሳት ውስጥ ከሚመደብ ቁሳዊ ባህል ውስጥ አንዱ ነው:: የፀጉር አሰራር ማህበረሰቡን በዋናነት ከሚገልፁ ቁሳዊ ባህሎች ውስጥ የሚመደብ ሲሆን ማህበረሰብን ለማጥናት አስፈላጊ ባህላዊ ቁስ መሆኑን Rose Weitz ያስረዳሉ:: ለዚህም የሚያቀርቡት ምክንያት ፀጉር ግላዊም ማህበረሰባዊም መሆኑ ነው:: ይህም ማለት ፀጉር በማንም ሰው በቀላሉ ሊታይ የሚችል በመሆኑ ማህበረሰባዊነትን ወይም ህዝባዊነትን ሲይዝ በተፈጥሮ ከአካላችን ጋር የተያያዘ መሆኑ ደግሞ ግላዊነቱን ያጎናፅፈዋል:: ከዚህ በተጨማሪም ፀጉር እንደግለሰቡና እንደ ባህሉ ምርጫ በቀላሉ ሊሰራ የሚችል በመሆኑ ነው::(Weitz; 667)

በኮንሶ ባህል መሰረት የማህበረሰቡ ሴቶች እንደ ደረጃቸው የሚሰሯቸው ሶስት አይነት የፀጉር አሰራሮች አሉ:: እነዚህም "ዳፓ"፣ "ሌሃያ" እና "ካሳራ" ተብለው ይጠራሉ:: እነዚህን የፀጉር አሰራር አይነቶች ምን እንደሚመስሉና ከባህሉ አንፃር ምን እንደሚያስተላልፉ ቀጥለን እንመለከታለን::

### 4.3.1 ዳፓ

ይህ የፀጉር አሰራር ወደታች የሚጎነጎን እና ሶስትዮሽ ነው:: ዳፓ ድፋን(በተለምዶ ግልብጥ እንደሚባለ ው አይነት) ሆኖ ይሰራ:: የማህበረሰቡ የፀጉር አይነት ከርደድ የማለት ባህሪ ያለው በመሆኑ በሚሰራበት ጊዜ ወጣ ይላል:: በተለይ የመሃሉ ከዳርና ዳሮቹ ይልቅ ተለቅ የማለት ባህሪ አለው:: ይህን የፀጉር አሰራር መስራት የሚችሉ ያላገቡ ልጃገረዶችና አግብተውም ያልወለዱ ሴቶች ናቸው። ይህም በተሰሪዎቹና በፀጉር አሰራሩ መካከል ጥብቅ ቁርኝት በመኖሩ ነው:: ሶስት በኮንሶ ባህል ውስጥ በጣም በብዙ ቦታዎች የሚታይ እና ለተለያዩ ጉዳዮችም ማፅኛ ወይም ማረጋገጫ ሆኖ ይገኛል። ይህም ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ መሸጋገርን ማረጋገጫ ወይም ፅኑ

ማድረጊያ መሆኑን የሚያሳይ ነው፤ ለአንድ ነገር ብቁ መሆንን፡፡ በመሆኑም አንድ ለአቅመ ሄዋን የደረሰች ግን ያልወለደች ሴት ለሶስት መሰራቷ ፍሬዋን ለማየት የደረሰችና ብቁ መሆኗን የሚያመለክት ነው፡፡ ይህን ለመረዳት ይረዳ ዘንድ ሶስት ቁጥር በኮንሶ ባህል ያለውን ቦታ በተወሰነ መልኩ ማወቅ ተገቢ ነው፡፡

በኮንሶ ብሄረሰብብ ባህል መሰረት ሶስት ቁጥር በብዙ ቦታዎች የሚነሳ መሆኑን ለማሳየት ጥቂቶቹን እንመልከት:: በኮንሶ ባህል አራስነቷን ጨርሳ የምትወጣ ሴት ሶስት መስመሮች ጡቶቿ ላይ ይሰመራል፡፡ ከዚያም ስትታረስበት የነበረውን ቦታ ለቃ እንድትወጣ ትደረጋለች፡፡ በዚህ ወቅት ሶስት ሰዎች ማለትም እናቷ፣ ድንግል የሆነች ሴትና አያቷ ሆነው ከታረሰችበት ቤት መግቢያ በር በመሄድ ሶስት ነገሮችን ይሰባስሉ:: ሙሽራ የሆነች ሴት ሶስት ጓደኞቿን ለሰርግ ታመጣለች፡፡ ሶስት ወንዶች የሞተውን የጎሳ መሪ (ቁስ) ለሶስት ወር ያክል ይመለከታሉ::

ከእነዚህ ጉዳዮች የሶስት ቁጥርን መደጋገም ሲታይ ሶስት ለነገሮች ማፅኛ ወይም አንድ ነገርን ወደ ሌላ ነገር ለማሸጋገር የሚደረግ ቅድመ ሁኔታን የሚያሳይ ነው፡፡ በመሆኑም ያልወለደች ሴት ለሶስት መሰራት ለቀጣይ ለሚኖራት የእናትነት ህይወት እንደቅድመ ዝግጅት የሚያሳስብ እና ለዚህም ብቁ በመሆን ላይ እንደሆነች የሚያሳይ ነው::

4.3.2 ሴሃያ

ይህ የፀጉር አሰራር አይነት ስድስትዮሽ ሆኖ ልክ እንደ ዳፓ ሁሉ ወደ ታች የሚጎነገን ነው፡፡ ዳፓ ስትሰራ የነበረች ሴት ልጅ ስትወልድ ለሶስት የነበረው ጉንጉን እያንዳንዱ ለሁለት ተከፍሎ ይሰራል፡፡ ይህም ሴሃያ በመባል ሲታወቅ የልጅ እናት መሆናቸውን የሚያመለክት ነው፡፡ ወ/ሮ ሃጋየ እንደሚገልፁት በአካባቢው ይህን የተሰራች እናት መጥፎ ነገር ስትናገርና ስታደርግ ብትታይ “ሴሃያ ከተሰራች በኋላ እንደዚህ ታደርጋለች” በመባል ትገሰፃለች ወይም ትተቻለች፡፡ ይህም አንዷት ሴት ሴሃያ ከተሰራች በኋላ አዋቂ መሆኗና በእንደዚህ አይነት የማይገባ ስራ ላይ መገኘቷ አስነዋሪ መሆኑን የሚገልፅ ነው:: ልጅ መውለድ የአዋቂነት ደረጃ ላይ መድረስን አመላካች ነው:: በመሆኑም እናት የሆነች ሴት ራሷን መጠበቅ እንዳለባትና የተረጋጋች መሆን እንደሚጠበቅባት ያሳያል፡፡

አንዷት ሴት ልጅ ከመውለዷ በፊት ትሰራ የነበረው ሶስት ጉንጉን ወደ ስድስት መከፈሉ የሚያስተላልፈው ራሱን የቻለ ትልቅ መልዕክት አለው:: የሶስት ወደ ስድስት መከፈል ሙሉ የነበረው እሷነቷ ተከፍሎ ዘሯ መብዛቱን የሚያሳይ ነው:: በዚህ የተነሳም የተሰሪዋ ዘር መቀጠሉን ጠቋሚ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ የፀጉር አሰራር ወደ እናትነት መሸጋገርን እና ዘር ማፍራት የሚያመለክት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል::

4.3.3 ካሳራ

አንዷት ስድስትዮሽ የነበረው ጉንጉኗ ከተፈታ በኋላ በሞራ በመቀባት እርስ በእርሱ እንዲያያዝ ተደርጎ ወደኋላ ይለቀቃል፤ ይህም ካሳራ ተብሎ ይጠራል፡፡ ይህ የፀጉር አሰራር ተሰሪዋ የልጅ ልጅ ስታይ የምትሰራው ነው:: በካሳራ የፀጉር አሰራር አይነት ማጌጥ የጀመረች አንዷት ሴት ከዚያ በኋላ ፀጉሯን አትታጠብም፡፡ በመሆኑም ካሳራ ካለመታጠብ እና ከተሰሪዎች የእድሜ ደረጃ ጋር ተያያዥነት አለው::(ወ/ሮ ሃጋየ፣ ሚያዚያ 27፣ 2003) ይህም የራሱ መልዕክት አለው::

በኮንሶ ማህበረሰብ ዝናብ ትልቅ ቦታ ያለው ሲሆን በተለይ የተለያዩ ሃይማኖታዊም ሆነ ማህበራዊ ስነ ስርዓቶች ከተከናወኑ በኋላ በእጅጉ የሚጠበቅ ከመሆኑም በላይ የዝናብ መዝነብ ምድሪቷን ከማንፃት ጋር ይያያዛል፡፡ ዝናብ(ውሃ) ምድሪቷን ያርሳታል፤ ዘርም እንድታበቅልና ፍሬ እንድትሰጥ ምክንያት ይሆናል፤ ለአዲስ ዘርም ያዘጋጃታል:: በዚህ አንፃር ስናየው በውሃ መታጠብ ለሌላ ፍሬ ወይም ዘር መዘጋጀትን ይወክላል፡፡ በመሆኑም ልጅ ያየች ሴት ፀጉሯን አለመታጠቧ አንድም ማርጀቷን የሚያመላክት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ከዚያ ጊዜ በኋላ ፍሬ ማፍራት እንደማትችል የሚያሳይ ነው:: በኮንሶ ባህል መሰረት የልጅ ልጅ ያየች ሴት ከባሏ ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈፀም አይፈቀድላትም:: በመሆኑም ይህን የማህበረሰቡን ገፅታ በዚህ የፀጉር አሰራር ማወቅ ይቻላል:: ይህን የተሰራች ሴት የሴትነት ሚናዋ(ማለትም ልጅ የመውለድ) ያበቃ እንደሆነ የሚገልፅ ነው::

በአጠቃላይ በኮንሶ ባህል መሰረት ሴቶች እንደደረጃቸው ራሳቸውን በእነዚህ ሶስት የፀጉር አሰራር አይነቶች ይገልፃሉ:: በማህበረሰቡ ህይወት ውስጥ ፀጉር ትልቅ ቦታ አለው:: ማንኛውም ሰው ሃዘን ካልገጠመው በስተቀር ሙሉ በሙሉ መላጨት አይፈቀድም:: በመሆኑም በኮንሶ ባህል መሰረት የፀጉር መኖር ብቻ ሳይሆን አለመኖርም የሚያስተላልፈው መልዕክት አለ:: ሃዘን ባጋጠመ ጊዜ ባሏ የሞተባት ሴት ፀጉሯን ሙሉ በሙሉ ትላጫለች፡፡ ይህም ሁሉ ነገሯ የሆነውን ባሏን ማጣቷን

የሚያመለክት ነው። እነዚህ የፀጉር አሰራር አይነቶች በአሁኑ ሰዓት እየተለወጡ እና እየጠፉ ይገኛሉ። ከዘመናዊ ትምህርት መስፋፋት ጋር በተያያዘ የሚከሰቱ ሁኔታዎች ለዚህ ትልቅ ድርሻ አላቸው። የተለያዩ የፀጉር አሰራር አይነቶች መብዛት ባህላዊ የሆኑት እንዲዋጡ አድርጓል ማለት ይቻላል።

## 5. የኮንሶ ሃገረሰባዊ አልባሳት ማህበራዊ ፋይዳ

ይህ ምዕራፍ የኮንሶ ሀገረሰባዊ አልባሳት በሚይዙት ትዕምርት አማካይነት በሚያስተላልፉት መልእክት የሚገለፁትን ማህበራዊ ፋይዳዎች ይዳስሳል። ይህም በተለይ በFleming የትኩረት አቅጣጫዎች ውስጥ አምስተኛው በሆነው አገልግሎት ላይ ያተኩራል:: በዚህም አስቀድሞ ቁሱ ከተሰራበትና በግልፅ የሚታየው አገልግሎትን(Intended Function) ከማየት ባሻገር ቁሱ ከዚህ ተግባሩ በተጨማሪ ቁሱ ከተገኘበት የባህል ገፅታዎች አንፃር ሲታይ የሚሰጠውን አገልግሎትንም(Unintended Function) ያጠቃልላል:: የኮንሶ ሀገረሰባዊ አልባሳት በማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸው ማህበራዊ ፋይዳ በአምስት ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር ሲሆን በዚህ መሰረትም የኮንሶ ብሄረሰብ ሃገረሰባዊ አልባሳት በዋናነት ዕድሜን የመግለፅ፣ ማህበራዊ ደረጃን የማሳወቅ፣ ክፉ መንፈስን የመከላከል፣ እናትነት የማሳየትና ማህበራዊ ሁነቶችን የማሳወቅ ፋይዳ አላቸው። እነዚህ ጉዳዮች እንደሚከተለው ይተነተናሉ።

### 5.1 ዕድሜን መግለፅ

ሃገረሰባዊ አልባሳት ከሚያስተላልፉት መልዕክት አንዱ የለባሹን የእድሜ ሁኔታ ማሳየት ነው:: በኮንሶ ብሄረሰብ ሃገረሰባዊ አልባሳት በጉልህ ከሚያሳዩት የተለያዩ ፋይዳዎች ውስጥ አንዱ ዕድሜ ነው በተለይ ደግሞ የእድሜ መግፋት ወይም ማርጀት:: ይህንንም በተለይ በወንዶች አልባሳት፣ በሴቶች የፀጉር አሰራርና ጌጣጌጦች ውስጥ በጉልህ ይታያል። ይህ ጉዳይ እንዴት እንደተገለፀ የተለያዩ የሃገረሰባዊ አልባሳት አይነቶችን እንደማሳያነት በማቅረብ እንደሚከተለው ይተነተናሉ::

እርጅና በኮንሶ ሃገረሰባዊ አልባሳት የሚገለፅ አንዱ የእድሜ ደረጃ ነው:: ይህ የአገላለፅ ሁኔታ እንደ ለባሾቹ ፆታ በተለያየ መልክ ነው:: በሃገረሰባዊ አልባሳት የሚታየው የወንዶች የእርጅና ሁኔታ ከክብር ጋር በተያያዘ መልኩ ነው:: ምክንያቱም ወንዶች እድሜያቸው ሲገፋ የሚያደርጓቸው አልባሳት የእድሜ ሁኔታ ከማሳየቱ በተጨማሪ የክብር መግለጫ ሁነው ይወሰዳሉ:: የሴቶችን የእርጅና ሁኔታ በኮንሶ ሃገረሰባዊ አልባሳት እንዴት እንደተገለፀ ስናይ ከወንዶች የተለየ ነው:: ሴቶች እድሜያቸው በሚጨምር ጊዜ የሚያደርጓቸው ባህላዊ ቁሶች ከልዩ ልዩ ማህበራዊ ሁኔታዎች መገለልን የሚያሳዩ ናቸው::

ይህን ሁኔታ ከሚያሳዩ የብሄረሰቡ የፀጉር አሰራር ውስጥ "ካሳራ" በመባል የሚታወቀውን የፀጉር አሰራር አንዱ ነው:: በምዕራፍ አራት እንደተገለፀው ይህን የፀጉር አሰራር የሚሰሩ ሴቶች የልጅ ልጅ ያዩ ናቸው። በመሆኑም ይህን የፀጉር አስራር የምትጠቀም ሴት ይህን መስራት መጀመሯ ከሌሎች ጉዳዮች በተጨማሪ እድሜዋ እየገፋ መሆኑንና ያረጀች እንደሆነች እንዲሁም የመውለድ ደረጃዋ ያለፈ መሆኑን የሚያመለክት ነው። ስለዚህም ማህበረሰቡ በዚህ የፀጉር አስራር መሰረት የሴቶች የዕድሜ ሁኔታ ምን እንደሆነ በቀላሉ ማወቅ ይችላል።

"ባራቴታ" በመባል የሚታወቀውና ወንዶች ራስ ላይ የሚያደርጉት ጨርቅ ሌላው የእድሜ ሁኔታን ከሚጠቁሙ ሃገረሰባዊ አልበሳት ውስጥ አንዱ ነው። ይህን የልብስ አይነት የሚጠቀው ወንዶች አንድም እድሜያቸው የገፋ አልያም በክብር ሰዓት ነው። በመሆኑም ይህን ልብስ በማህበረሰቡ ዘንድ በእርጅና ማማ ላይ ያሉ ሰዎች የሚያደርጉት በመሆኑ የተጠቃሚዎችን የእድሜ ሁኔታ በግልፅ አመላካች ሆኖ ይታያል። ከዚህ በተጨማሪም ጋቢ በሽማግሌዎች የሚደረግ ሃገረሰባዊ ልብስ ሲሆን በተለይ ሽማግሌዎች ለእርቅ ሲሄዱ የሚያደርጉትና የሚያዘወትሩት በመሆኑ ዕድሜ አመላካችነቱ የጎላ ነው።

ሌላው ከኮንሶ ሃገረሰባዊ አልባሳት ውስጥ ዕድሜን አመላካች ጌጥ "ኢላዋ" በመባል የሚታውቀው ነው። ይህ የአንገት ጌጥ እርጅናዋ ለደረሰ እናት የሚሰጥ ሲሆን ከተሰጣት (መጠቀም ከጀመረች) በኋላ እንደልቧ መንቀሳቀስ እንደማትችል ለማሳየት ሲሆን ከዚህ በኋላ የሚጠባቅባት ልጆችን(የልጅ ልጆቿን) መንከባከብና ማቀፍ ነው። በመሆኑም ይህን ጌጥ የሚያደርጉት ሰዎች በእርጅና ጎዳና ላይ ያሉና እንደልባቸው የማይንቀሳቀሱ አሮጊቶች ናቸው:: ስለዚህ ይህ ጌጥ የተጠቃሚዎችን የዕድሜ ሁኔታ በጉልህ ያሳያል:: ከዚህ በተጨማሪም "ሞዳታ" የጆሮ ጌጥ እርጅናን አመላካች ሆኖ እናገኘዋለን። ይህን ጌጥ የሚያደርጉ ሰዎች ከሶስት በላይ የወለዱና በአብዛኛው ወደ እርጅና እየሄዱ ያሉ ሴቶች ናቸው።

በኮንሶ ማህበረሰብ ዘንድ እርጅናን ከሚያሳዩ የተለያዩ ሃገረሰባዊ አልባሳት በተጫማሪ ወጣትነትን የሚጠቁሙም የተለያዩ አልባሳት ይገኛሉ። ከነዚህ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ባይሆንም እንኳን በተወሰነ ጎኑ "ዳፓ" የሚባለው የፀጉር አስራር አይነት ይጠቀሳል:: በምዕራፍ አራት በሰፊው እንደተገለፀው ይህን የፀጉር አሰራር አይነት የሚሰሩት ያላገቡ ወይም ደግሞ ያልወለዱ ሴቶች ናቸው። ከዚህ መገመት

እንደሚቻለውም በአብዛኛው ይህን የፀጉር አሰራር የሚሰሩ ሴቶች ወጣቶች ናቸው፡፡ በመሆኑም ወጣትነት ከዚህ የፀጉር አሰራር ጋር ተያይዞ የሚመጣና ይህን አመላካችም ሆኖ ይታያል፡፡ ሌላው ወጣትነትን ከሚገልፁ ጌጦች ውስጥ "ኮልባ" የተሰኘውን የጆሮ ጌጥ ይጠቀሳል:: ይህን ጌጥ የሚጠቀሙ ለአቅመ ሄዋን የደረሱ ሴቶች ናቸው፡፡ ይህም በአብዛኛው የወጣቶች ማጌጫ ወቅት በመሆኑ ለውበት የሚጠቀሙበት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ይህ ጌጥ የሚያደርጉትን የእድሜ ደረጃ የሚያሳይ በመሆኑ ዕድሜን ከሚያመላክቱ ሃገረሰባዊ አልባሳት አንዱ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

## 5.2 ማህበራዊ ደረጃን ማሳየት

ሃገረሰባዊ አልባሳት ከሚያሳዩ ጉዳዮች ሌላው ማህበራዊ ደረጃንና የሃብት ደረጃን ነው:: በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚታየውን የኑሮ ደረጃዎች አልባሳት ቁልጭ አድርገው በማሳየት ይታወቃሉ:: ማህበራዊ ደረጃን ማሳየት ሲባል በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን ማህበራዊ ልዩነት ማለትም የሃብት የስልጣንና የመሳሰሉትን ልዩነቶች የሚያጠቃልል ሲሆን  የኮንስ ማህበረሰብ ሃገረሰባዊ አልባሳትም በያዙት ትዕምርት ከሚያስተላልፉ መልዕክት አንደኛው ጉዳይ ነው ይህን ልዩነት ማሳየት፡፡ ይህም በተለይ በጌጣጌጦች ላይ ጎላ ብሎ ይታያል፡፡ ይህ ንዑስ ክፍልም የኮንሶ ብሄረሰብ ማህበራዊ ደረጃ በአልባሳቱ አማካኝነት እንዴት እንደተገለፀ የሚያሳይ ነው፡፡

በኮንሶ ብሄረሰብ ባህላዊ የአስተዳደር ስርዓት መሰረት ከፍተኛ ስልጣን ያለው "ፖቃላ ቱማ"ው ሲሆን ይህም የጎሳ መሪው ነው፡፡ ይህ የጎሳ መሪ ከሌሎች  የሚለይበት "ቱማ" የተባለ ክብር የሚሰራና ክንድ ላይ የሚደረግ ጌጥ ያደርጋል:: ይህን ጌጥ የሚያደርገው የጎሳ መሪው የሆነው "ፖቃላ ቱማ" ብቻ ነው፡፡ ይህም ጌጥ ስልጣኑ ከማንም በላይ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ክንድ ላይ የሚደረግ ጌጥ የአድራጊውን የስልጣን ደረጃ ምንነት ይገልፃል:: ከፖቃላ ቱማ በታች ያሉት መሪዎች ደግሞ "ሙግላ" የሚባልና ከነሃስ የሚሰራ በክንድ ላይ የሚደርግ ጌጥ ያደርጋሉ፡፡ ይህም ስልጠናቸው ከሌላው ህዝብ በላይ ከፖቃላ ቱማው በታች መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ እነዚህ በክንድ ላይ የሚደረጉ ጌጦች የሁለቱን ማለትም የፖቃላ ቱማን እና የፖቃላ ሙልጋውን የስልጣን ደረጃ ከመለየታቸው በላይ ማህበረሰቡ በቀላሉ ስለማንነታቸው ያደረጉትን ጌጥ ብቻ በማየት እንዲለዩ የሚያስችል አቅምን ይፈጥራሉ::

ከነዚህ ባህላዊ ጌጦች በተጨማሪ በኮንሶ ማህበረሰብ ዘንድ ማህበራዊ ደረጃን ከሚጠቁሙ ጌጦች መካከል አንዱ ነው፦ "ሃላሻ"፡፡ "ሃላሻ" ግንባር ላይ የሚደረግ የጌጥ አይነት ነው፡፡ ይህ ጌጥ በጎሳ መሪው ብቻ የሚደረግ እና በተለይ የተለያዩ መንፈሳዊ ጉዳዮች በሚፈፀሙበት ጊዜ የሚደረግ ሲሆን ይህም በሚፈፀመው ስነስርዓት ላይ መሪነቱን የሚያሳይ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም አድራጊው በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን ከፍ ያለ የስልጣን ደረጃ የሚያመለክት ነው፡፡ በምዕራፍ አራት ላይ እንደተገለፀው ሃላሻ ከወንድ ልጅ የመራቢያ አካል ጋር የተያያዘና ይህም የአድራጊውን ሃያልነት ጀግንነት ለመግለፅ የሚያገለግል መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡



ምስል 11: ሃላሻን ያደረጉ የጎሳ መሪ

በኮንሶ ብሄረሰብ አንበሳ፣ ዝሆን ወይም ጎሽ የገደለ ሰው "ገዳይ" ተብሎ የሚጠራ ሲሆን ይህ ገዳይም ለክብሩና ለዝናው መግለጫ ይሆንለት ዘንድ "ፓላ" ተብሎ የሚጠራ ሁለት የሰጎን ላባ በራሱ ላይ ያደርጋል፡፡ እነዚህን ሁለት የሰጎን ላባ በራሱ ላይ የሰካ ሰው ጀግና መሆኑንና ገዳይ መሆኑን ማህበረሰቡ ይረዳለታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አንድ የሰጎን ላባ የሚያደርግ ወንድ ደግሞ ገዳይ ለመሆን የተዘጋጀ ነገር ግን እስከአሁን ያልገደለ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

ሌላው ማህበራዊ ደረጃን ከሚያሳዩ  የኮንሶ ሃገረሰባዊ አልባሳት መካከል "ጭርዋና" አንዱ ነው። ይህ የአንገት ጌጥ በጣም ውድ በመሆኑ የሚያደርጉት ሰዎች አንድም የታዋቂ ሰው ሚስቶች ወይም የጎሳ መሪ ሚስቶች እንዲሁም በኢኮኖሚ ደረጃቸው ከፍ ያሉ ሴቶች ናቸው። በመሆኑም ይህን የአንገት ጌጥ የምታደርግ ሴት በተመልካቹ ልቦና ስለምንነቷ በቀላሉ ታሳውቃለች:: በአጠቃላይ እነዚህ ሃገረሰባዊ አልባሳት በማህበረሰቡ መካከል ያለውን የማህበራዊ ደረጃ ልዩነት በማሳወቅ በተመልካቹ እና በለባሹ መካከል መግባባትን ይፈጥራሉ::

## 5.3 ክፉ መንፈስን መከላከል

በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ መጥፎ ነገሮች እንዳይገጥሙና የተደላደለ ኑሯቸው እንዳይበረዝ ወይም ደግሞ የተስተካከለ እንዲሆን ለማድረግ የሚረዱ ልዩ ልዩ ነገሮችን በመጠቀም ክፉ ብለው የሚያስቡትን መንፈስ ለመከላከል ይሞክራሉ:: ይህን ከሚያደርጉባቸው ነገሮች ውስጥ ሃገረሰባዊ አልባሳት ይጠቀሳሉ:: በኮንሶ ማህበረሰብም ይህ አይነቱን ተግባር በሃገረሰባዊ አልባሳት ውስጥ ይታያል። ነጭ ቀለም በባህሉ መሰረት የሞት ምልክት ተደርጎ እንደሚወሰድ ሁሉ ለክፉ መንፈስ መከላከያና ማባረሪያም ሆኖ ያገለግላል። ይህንን ፋይዳ ከያዙት ሃገረሰባዊ ጌጣጌጦች መካከል ሄሮዳ  አንዱ ነው:: "ሄሮዳ"  ነጭ ቀለም ባላቸው ከሰጎን እንቁላል በሚሰሩ እና በሰማያዊ ዶቃዎች የሚሰራ መሆኑን በምዕራፍ አራት ተመልክተናል። ይህ ጌጥ የሚደረግበት ምንም እንኳን ለማጌጥ ወይም እናትነትን ለመግለፅ ቢሆንም ተጨማሪ ተግባርንም የያዘ ነው:: ሄሮዳ ልጆችን ከክፉ መንፈስ ለመጠበቅ የሚረዳና በዚህም የተከላካይነት ተግባርን የማስፈፀም ፋይዳ ያለው ሆኖ እናገኘዋለን:: ሰማያዊ ዶቃዎቹ(ፐሌዳ) በነጮቹ ተከበው ይታያሉ:: በመሆኑም እንደ "ፐሌዳ" (ሰማያዊ ዶቃዎች) ውድ የሆኑት ልጆቻቸው ወደፊት መጥፎ ነገር እንዳይገጥማቸው ለማድረግና ይህን የሚያደርገውን ክፉ መንፈስ እንዳይቀርባቸው ለመከላከል የመርዳት ፋይዳ አለው ተብሎ ይታመናል።

ሌላው ክፉ መንፈስን የመከላከልና የማጥፋት ፋይዳ ያለው "ሃላሻ" ነው:: Hallpike እንደሚያስረዱት ሃላሻ ለክብረ በዓላት ጊዜ የሚደረግ ሲሆን በተለይ መስዋዕት በሚቀርብበት ጊዜ መስዋዕት አቅራቢው ቁስ ክፉ ነገሮች እንዲወገዱ ለማድረግ ከሚረዱት ውስጥ አንዱ ሃላሻ ነው:: የሃላሻው ሁለተኛ ክፍል ነጭ መሆን ለዚህ ተግባሩ እንደዋነኛ ምክንያትነት የሚነሳ ነው ምክንያቱም ነጭ ክፉ መንፈስን



ምስል 12: ወንድና ሴት ልጆች ያሏት እናት የምታደርገው ሄሮዳ

“ስራ” ወይም “ሚኖ” የሚባለው የግንባር ጌጥ ሌላው እናትነትን የሚያመለክት ነው። ይህ ጌጥ የሚደረገው ያገቡ ሴቶች ወልደው ከአራስ ቤት ሲወጡ ሲሆን የበለጠ ለመዋብ የሚጠቀሙበት ነው። በመሆኑም ይህን አድርጋ የምትታይ ሴት በቅርቡ የተገላገለች የልጅ እናት እንደሆነች ይታወቃል።

ልክ እንደ ስራ ሁሉ “ኮራ” በመባል የሚታወቀው ሃገረሰባዊ ልብስም አንዲት ሴት ወልዳ ከአራስ ቤት ስትወጣ የምታደርገው ነው። ይህን የምታደርግ ሴት የልጅ እናት የሆነች መሆኗንና በቅርቡ የተገላገለች እንደሆነች ማወቅ ይቻላል። ከዚህ በተጨማሪም እናቲቱ የወለደችው ሴት ወይም ወንድ መሆኑንም ያሳውቃል። በመሆኑም ከእናትነቷ በተጨማሪም የልጇ ፆታ ምን እንደሆነም ይጠቁማል።

## 5.5 ማህበራዊ ሁነቶችን መጠቆም

ማህበራዊ ሁነቶች ሲባል በሰው ልጅ ህይወት ውስጥ የሚከሰቱ የተለያዩ አጋጣሚዎችን ማለትም ሀዘን፣ ሰርግ እና የመሳሰሉትን የሚያጠቃልል ነው። በኮንሶ ማህበረሰብ እነዚህን ማህበራዊ ሁነቶች ለማሳወቅ ሃገረሰባዊ አልባሳቱ የራሳቸው የሆነ ትልቅ ሚና ይጫወታሉ። በኮንሶ ባህል መሰረት ቢጫ የሃዘን ቀለም ተደርጎ ይወሰዳል። አንድ ሰው ሲሞትም “አይባት” የሚባል ዛፍ ቅርፊት ተዘፍዝፎ ጨርቅነት ያላቸውን ልብሶች ይነከራሉ። እነዚህ የተነከሩት ልብሶችም ወደ ቢጫነት ይቀየራሉ። በመሆኑም የሃዘን መግለጫ ተደርጎ ይወሰዳል። በባህሉ መሰረት አባት ሲሞት

ለማስወገድ ይረዳልና፡፡ በመሆኑም ይህ ጌጥ ከጌጥነቱና የስልጣን ደረጃን ከማሳየቱ በተጨማሪ በክብረ በዓላት ወቅት ሃይማኖታዊ ስርዓቶች በሚፈፀሙበት ጊዜ ይህ ጌጥ ከተለያዩ ቁሶች ጋር ሆኖ ይህን ተግባር እንደሚወጣ ይታመናል፡፡

## 5.4 እናትነትን ማሳየት

ሃገረሰባዊ አልባሳት በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚፈጠሩ የተለያዩ ክስተቶችንም ሆነ ሁነቶችን የማሳየት ብቃት አላቸው:: መዋለድ በሰው ልጅ የኑሮ ሂደት ውስጥ ዋነኛው ነው፥ የሰው ልጅ ዘር መቀጠያ መንገድ በመሆኑ:: እናትነትም ከዚህ ጋር ተያይዞ ይመጣል:: ይህ ፀጋ በኮንሶ ብሄረሰብ ሃገረሰባዊ አልባሳት ከሚገለፁ ጉዳዮች አንዱ ነው፡፡ አንዲት ሴት ወደ እናትናት ስትሸጋገር ለሶስት የተሰራ የነበረው ፀጉሯ ለሁለት ለሁለት ተከፍሎ ለስድስት ይሰራል፡፡ ለሶስት የነበረው ለሁለት መከፈሉ የእናቲቱን የዘር መብዛትና የዘር መቀጠል የሚያሳይ ነው፡፡ በመሆኑም ሴሃያ የተሰራች ሴት እናት መሆኗ ወይም ልጅ እንዳላት የሚያመለክት ነው፡፡ በዚህም ማንም የማህበረሰብ አባል ይህን አይቶ የተሰሪዋን እናትነት ማወቅ ይችላል፡፡ እናትነት በልጅ ብቻ ሳይሆን በልጅ ልጅም ይገለፃል:: ይህን ጉዳይ ካሳራ ተብሎ በሚጠራው የፀጉር አሰራር አይነትም ይስተዋላል:: የልጅ ልጅ ያየች እናት ጉንጉን የነበረው ፀጉሯ ተፈቶ ወደ ካሳራ ይለወጣል:: ይህም የልጅ ልጅ ማየቷን ጠቋሚ ነው::

“ሄሮዳ” ሌላው እናትነት የሚገለፅበት የጌጥ አይነት ነው፡፡ በኮንሶ ማህበረሰብ ሄሮዳ በእናቶች የሚደረግ ጌጥ ነው:: ነጠላው ሄሮዳ የልጅ ልጅ ባየች እናት ሲደረግ ድርቡ ደግሞ ልጅ ያላት ለአቅመ አያት ግን ባልደረሰች እናት ይደረጋል:: ይህ የእግር ጌጥ እናትነትን ብቻ ሳይሆን የልጆቹንም ፆታ በግልፅ ያሳያል:: በዚህም ሄሮዳው አራት ሰማያዊ ዶቃዎች ያሉት ከሆነ የአድራጊዋ ልጅ ሴት ስትሆን የዶቃዎቹ ብዛት አስራሁለት ከሆነ ደግሞ የወንድ ልጅ እናት መሆኗ ይታወቃል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ እናትየው ወንድ እና ሴት ልጆች ካሏት ሁለቱን አይነት ታደርጋለች::



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

የልጆች ፀጉር የሚላጭ ሲሆን ሴቶች (በተለይ ያገቡ) ፁጉራቸውን ሳይላጩ አልፎ አልፎ ቡጭቅ ቡጭቅ ያደርጉታል። ይህ የመላጨት ጉዳይ ልጅ ለሞተባት እናት አይሆንም፣ ልጆች ሲሞቱ ይህ አይደረግምና።

በኮንሶ ባህል ባኗ የሞተባት ሴት ፀጉሯን ሙሉ በሙሉ ትላጫለች  ግንባሯ ላይም ያጋቲቲማ የሚባል ቀይ ቀለም ያለውን ጌጥ ታደርጋለች:: ሌሎች ጌጦችንም ታወልቃለች::ይህም በህይወቷ አለኝ የምትለውን ሰው ማጣቷንና በከባድ ሃዘን ውስጥ መሆኗን ያመለክታል። በሃዘን ጊዜ “ሻላ” ተብሎ የሚጠራው የግንባር ጌጥ ይነሳል። ያዘነ ሰው ይህን ጌጥ አያደርግም ለዚህም ነው በአንድ ሰው ስራ የተናደደ ሰው ሲራገም “ሰዎች ያደርጉት ሻላ ይነሳልህ /ይነሳልሽ” የሚሉት::(አቶ ገሲሞ፣ ሚያዚያ 24 2003) ይህ የሚያመለክተውም ሰዎች “ሻላ” የተባለውን ጌጥ ካነሱ የሞተ ሰው እንዳለና ሀዘን ላይ እንደሆኑ ነው። በመሆኑም የሻላ ጌጥ መነሳት ሌላ የሃዘን ምልክት ነው ይህም የጌጦች መደረግ ብቻ ሳይሆን አለመደረግ ወይም መነሳትም በማህበረሰቡ ዘንድ ተግባቦትን የመፍጠር ትልቅ ትዕምርታዊ ፋይዳ እንዳለው ያሳያል፡ ፡ በማህበረሰቡ ዘንድ ከሴት ይልቅ ወንድ ሲሞት የሃዘኑ ጉዳይ ይስተዋላል። ይህም በማህበረሰቡ ለወንዶች የሚሰጠውን ከፍ ያለ ቦታ ያሳያል። በባህሉ መሰረት የዘር ሃረግ የሚቆጠረው የወንድ (የአባት) ብቻ መሆኑ ለዚህ ሃሳብ እንዳማገገር ይመጣል::

ሌላው በኮንሶ ማህበረሰብ ውስጥ ከሚከሰቱ ማህበራዊ ሁነቶች ውስጥ በሃገረሰባዊ አልባሳቱ የሚገለፀው የሙሽርነት ጊዜ ነው:: በኮንሶ በአንድ ወቅት ያገቡ ሴቶች ተሰብስበው ሙሽርነታቸውን የሚያሳዩ አልባሳትን አድርገው ይዞራሉ። በመሆኑም “ፓሮታ” ተብሎ የሚጠራውን ከጥቁር ፍየል ቆዳ የሚዘጋጀውን ልብስ ያደረገች አንድ ሴት የቅርብ ሙሽራ እንደሆነች ማንም አይቶ ይለያታል። ከዚህ በተጨማሪም “ኡሌታ ሃዳ” የሚባል የክብር በትር በእጇ ከያዘች ማህበረሰቡ “አሃ ይቺ ሙሽራ ድንግልናዋን ጠብቃ የኖረች ናት”  ለማለት የሚያስችል ተግባቦትን የሚፈጥር ነው። ይህን የክብር በትር ያልያዘች ሙሽራ በማህበረሰቡ ዘንድ “ባለጌ ናት” ተብላ ትወቀሳለች። በመሆኑም እነዚህን ሃገረሰባዊ አልባሳት አድርገው የሚታዩ ሴቶች የሙሽርነት ጊዜያቸው እንደሆነ ማህበረሰቡ በቀላሉ ያውቃል። ይህም ሃገረሰባዊ አልባሳት በማህበረሰቡና በለባሹ መካከል ቃላዊ ባልሆነ መንገድ ተግባቦትን የመፍጠር አቅማቸው ከፍተኛ መሆኑን አመላካች ነው።

በስፋት መካሄድ፤ የክርስትና በተለይ የፕሮቴስታንት እምነት መስፋፋት እንዲሁም የዘመናዊ ትምህርት ቤቶች መስፋፋት ዋነኞቹ ናቸው::

የኮንሶ ሃገረሰባዊ አልባሳት በዋናነት ከሚሰጡት አገልግሎት በተጨማሪ በባህሉ ከሚታዩ የተለያዩ ገፅታዎች አንፃር ሲታዩ በሚያስተላልፉት መልዕክት አማካኝነት የተለያዩ ማህበራዊ ፋይዳዎችን ይሰጣሉ:: በዚህ መሰረትም በማህበረሰቡ እድሜን በማሳወቅ፣ በተለያየ መልኩ በአካባቢው ህብረተሰብ ውስጥ ያሉትን የተለያዩ ማህበራዊ ደረጃዎች በማሳየት፤ ከክፉ መናፍስት በመጠበቅ፤ እናትነትን በመግለፅ እና በማህበረሰቡ የዕለት ተዕለት ህይወት ውስጥ የሚከሰቱ የተለያዩ ማህበራዊ ሁነቶችን በማሳወቅ ትልቅ አስተዋፅዖ አላቸው::

## ዋቢ መፃህፍት


ሰይድ ይማም ፤"በከሚሴ ከተማ ዙሪያ በሚገኙ ገጠር አካባቢዎች የወጣት ወንዶችና ሴቶች አለባበስና አጊያጊያጥ"፤የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነፅሑፍ ትምህርት ክፍል፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2002 ዓ.ም።(ያልታተመ)

አያል አድማሱ ፤"የጎጃም አካባቢ የአልባሳት ስያሜ"፤ የባችለር ዲግሪ ማሟያ ጥናት፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነፅሑፍ ትምህርት ክፍል፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1992ዓ.ም።(ያልታተመ)

ዐቢዩ አስማማው ፤"የአርጎባ ብሄረሰብ የቤት ውስጥ መገልገያና የማጌጫ ቁሶች በአማራ ክልል ደቡብ ወሎ ዞን አርጎባ ልዩ ወረዳ"፤ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፤የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነፅሑፍ ትምህርት ክፍል፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2000ዓ.ም።(ያልታተመ)

ዋልተንጉስ መኮንን ፤"የሽመናና የጥልፍ ትውፊት በአክሱም"፤ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነፅሑፍ ትምህርት ክፍል፤ 2000ዓ.ም።(ያልታተመ)

ውብሸት አሰፋ ፤"የወይዛዝርት አልባሳትና ጌጣጌጥ ስሞች በአማራው ክልል"፤ የባችለር ዲግሪ ማሟያ ጥናት፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነፅሑፍ ትምህርት ክፍል፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1972ዓ.ም።(ያልታተመ)

የኔአለም አረዶ ፤"የአርሲ ሴቶች ጌጣጌጥ ጥናት በኮኮሳና ገደብ ሀሰሳ ወረዳዎች" ፤የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነፅሑፍ ትምህርት ክፍል፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2000ዓ.ም።(ያልታተመ)

የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ክልል ባህል ቢሮ፤ <u>የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ፕሮፋይል፤</u> 1999ዓ.ም።

ያሬድ ተፈራ ፤"በሰቆጣና በአርገሌ ገጠራማ ወረዳዎች የሴቶችና የወንዶች የአለባበስና የአጊያጊያጥ ማህበራዊ እሴቶች"፤የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነፅሑፍ ትምህርት ክፍል፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2000ዓ.ም።(ያልታተመ)

ፈቃደ አዘዘ፤ የሥነ_ቃል መምሪያ፤ አዲስ አበባ፤ ኢትዮ ጥቁር ዓባይ አታሚዎች፣ 1999ዓ.ም።

Birgitta Kimura & Dinote Kusia Shenkere. "Beads in Konso, Southern Ethiopia". Proceedings of the 16th International Conference of Ethiopian studies. Ed. Svein Ege & others. Trondheim, 2009; pp.369-381.

Bronner, Simon J. Concepts in the study of Material aspects of American Folk Culture. Online resource.

Danesi, Marcel. Messages, Signs, and Meanings: A Basic Textbook in Semiotics and Communication Theory. 3rd ed. Toronto. Canadian Scholars' Press Inc; 2004.

Entwistle, Joanne & Elizasbeth Wilson. "Introduction".Body Dressing. Oxford. Berg; 2001.

Fleming, E. McClung. "Artifact Study: A Proposed Model" Winterthur Portfolio. The University of Chicago Press. Vol. 9; (1974), pp. 153-173.

Glassie, Henry. Material Culture. Blomington and Indianapolis. Indiana University Press; 1999.

Gracia, Maria Inglessis. "Communicating through Clothing: the meaning of Clothing Among Hispanic Women of different levels of Acculturation".(unpublished diss.) College of communication; Florida State University, 2008.

Hallpike, C.R. The Konso of South Western Ethiopia: A Study of The Values of A CushticPeople. Oxford. Clarendon Press; 1972.

Kaiser, Susan B. The Social Psychology of Clothing: Symbolic Apperances in

Context. 2nd ed. New York. Macmillan publishing company, 1990.

Klem, Peri. "Shaping the future, wearing the past: Dress and the decorated Body Among the Afan Qallo Oromo in East Hararghe, *Ethiopia"*. University of California. 2002. (Unpublished)

Mamitu Yilma. "Some Aspects of the Status of Women Among the Konso of Southwest Ethiopia." Department of Social Anthropology. Addis Abeba University, 2002. (Unpublished)

Michael ,John. "Material culture". Folklore: An Encyclopedia of Beliefs, Customs, Tales,Music and Art. USA. Thomas A. Green(ed.). ABC-CLIO Inc.,(1997);145-151.

Oestigaard, Terje. "The World as Artifact: Material culture & Archaeology." Material Culture & Other Things: Post-diciplinary Studies in the 21th Century. Gotaic. series C, no. 61, 2004.

Prown, Jules. "Mind in Matter: An Introduction to Material Culture Theory and Method." Interpreting Objects and Collections. Susan M. Pearce(ed.). routledge;(1994), 67-75.

Sebesta, Judith L. " Weavers of Fate: Symbolism in the Costume of Roman Women". http://beach.ksu.edu/curricula/photo-curriculum/pdfs/material-culture.pdf

Shako Otto. "Traditional Konso Culture and The Missionary Impact". Annales d'Ethiopie. Vol.20. annee(2004), 149-180.

Sims, Martha C. and Martine stephen. Living Folklore: an Introduction to the study of People and Their Tradition. Logan, Utah. Utah state University Press, 2005.

Sintayahu Kidanie "Traditional Cloth- Making and its Dynamics in post Libration Addis Ababa: Weaving among the Dorze of Siromeda". Department of cultural studies. Addis Ababa University: 2010. (unpublished)

Svenssor, Tom. "Clothing in the Arctic: A means of protection, a statemeint of Identity." Arctic. Vol. 45, no. 1; March (1992), pp. 62-73.

Tilley, Christopher. "Interpreting Material Culture". Interpreting Objects and Collections. Susan M. Pearce(ed.). routledge;(1994), 67-75.

Twigg, Julia. "clothing, Age and the Body: a critical review".Ageing and Society. United Kingdom. Cambridge university press. (2007), 285-305.

Watson, Elizabeth & Lakew Regassa. "Konso". Living on the Edge: Marginalised Minorities of Craftworkers & Hunters in South Ethiopia. Dena Freeman & Alula Pankhurst(ed.). Department of Sociology & Social Administrtion. Addis Abeba University, 2001.

Weitz, Rose. "Women and Thier Hair: Seeking Power through Resistance and Accommodation." Gender And Society. Sage Publications, Inc Vol. 15, No. 5(oct. 2001), 667-686.

Wilson, Kathryn. "Costume, Folk" ". Folklore An Encyclopedia of Beliefs, Customs, Tales, Music and Art. Thomas A. Green(ed.). USA. ABC-CLIO Inc., (1997); 145-151.

Woodward, Ian. Understanding Material Culture. Los Angles: SAGE publication, 2007.


Yilma Sunta. "The Role and Status of Women in the Food System of the Konso

Southwest Ethiopa." Department of Social Anthropology. Addis Abeba University, 2002. (unpublished)

Yoder, Don. "Folk Costume". Folklore and Folklife: An Introduction. Richard Dorson(ed.). Chicago; University of Chicago, 1972.

Zufan Fikre "Traditional Cloth- Making in Kutaber of south Wollo". Department of Documentary Linguistic. Addis Ababa University, 2010.(unpublished)

አባሪ 1




ምንጭ፦ከ US-AID ስዕላዊ መግለጫ, 2007

አባሪ 2

## ቁልፍ የመረጃ አቀባዮች

| ተ.ቁ. | ስም | ፆታ | እድሜ | ድርሻ | መረጃ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ኮራ ካራ | ወ | 70 | በሃገረሰባዊ አልባሳት የበፊት እና አሁን ያሉበትን ደረጃ በስፋት የገለፁ | በኮንሶ ማህበረ-ባህላዊ ገፅታ ዙሪያ አዋቂነትን ያተረፉ እና በዚህም እስከ ውጪ ሃገራት በመሄድ የተለያዩ ገፅታዎችን ያስተዋወቁ |
| 2 | ወ/ሮ ሃጋየ ቱሮ | ሴ | 60 | በተለይ በጌጣጌጦች ዙሪያ ሰፊ ማብራሪያ የሰጡ | |
| 3 | አቶ ከበደ ገለቱ | ወ | 28 | በሃገረሰባዊ አልባሳት ዙሪያ ገለፃ የሰጡ እና በረዳትነት ያገለገሉ | በባህል እና ቱሪዝም ቢሮ ባልደረባ እና በቢሮም በሃገረሰባዊ አልባሳት ዙሪያ የመረጃ ማሰባሰብ ስራን ያከናወኑ |
| 4 | አቶ ገሲሞ ገሰሰ | ወ | 30 | በሃገረሰባዊ አልባሳት ዙሪያ ገለፃ የሰጡ | በባህል እና ቱሪዝም ቢሮ ባልደረባ እና በቢሮም በሃገረሰባዊ አልባሳት ዙሪያ የመረጃ ማሰባሰብ ስራን ያከናወኑ |
| 5 | አቶ ገልገሎ ሰንሳን | ወ | 65 | ሃገረሰባዊ አልባሳትን በተለይ አልባሳትን እና የፀጉር አሰራርን በተመለከተ መረጃ የሰጡ | |
| 6 | አቶ ኩሴ አርካይዶ | ወ | 30 | ጌጣጌጦችን በተመለከተ መረጃ የሰጡ | የጌጣጌጥ ባለሞያ |
| 7 | አቶ ሳጎያ ካሹቴ | ወ | 45 | ሃገረሰባዊ አልባሳትን በተመለከተ ማብራሪያ የሰጡ | የአልባሳት ባለሞያ |

# ማረጋገጫ

ይህ ጥናት የኔ ወጥ ስራ (Original work) መሆኑን እና በጥናቱ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን መረጃዎች ምንጭ በትክክል የጠቀስኩ መሆኑን አረጋግጣለሁ።

ስም አፀዱ ደረጋል

ፊርማ

ማስረከቢያ ቀን 13/11/2003 ዓ.ም